አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ስነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሀ ግብር

# በእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ስለ ሴቶች የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ይዘት ትንተና

በ

ምህረት እባቡ

አማካሪ

የወንድወሰን አውላቸው (ዶ/ር)

ግንቦት 2011 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# በእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ስለ ሴቶች የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ይዘት ትንተና

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ስነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሀ ግብር

በኢትዮጵያ ስነ-ጽሑፍና ፎክሎር ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

ምህረት እባቡ

ግንቦት 2011 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ ቋንቋዎች ጥናት ጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ስነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሀ ግብር

# በእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ስለ ሴቶች የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ይዘት ትንተና

በ

ምህረት እባቡ

በኢትዮጵያ ስነ-ጽሑፍና ፎክሎር ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

ግንቦት 2011ዓ.ም

<u>የፈተና ቦርድ አባላት</u>

1. የአማካሪ ስም፡- --------------------------------------ፊርማ ----------------
2. የውስጥ ፈታኝ ስም፡- ------------------------------ ፊርማ ----------------
3. የውጭ ፈታኝ ስም፡- ------------------------------- ፊርማ ---------------

# ምስጋና

ለጥናቱ አቅጣጫ በማሳየትና በማረም ይህን ቅርጽ ይዞ እስኪወጣ ድረስ እገዛ ያደረገልኝን አማካሪዬ ዶ/ር የወንድወሰን አውላቸው አመሰግነዋለሁ፡፡ የምፈልገውን መረጃ በመስጠት ከተለያዩ መረጃ ሰጪዎች ጋር በማገናኘት አስፈላጊውን ትብብር ላደረጉልኝ የእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ሰራተኞች በሙሉ ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡


ከዚህ በተጨማሪ በሁለት ዙር የመስክ ሥራዬ ያለ አንዳች ማቅማማት በቂና ዝርዝር መረጃዎችን በማቀበል ይህን ጥናት ሙሉ እንዲሆን ላደረጋችሁልኝ የእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ነዋሪዎችና መረጃ አቀባዮቼ ከፍ ያለ ምስጋና ይገባችኋል፡፡

በአጠቃላይ ጥናቱ የተሳካ እንዲሆን ከጎኔ በመሆን በሀሳብና በእውቀት ለረዳችሁኝ ጓደኞቼ እና ቤተሰቦቼ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት በእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ስለ ሴቶች የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮችን ይዘት ትንተና ላይ ያተኮረ ሲሆን የትናቱ ዋና ዓላማም ስለ ሴቶች የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮችን ይዘት በመተንተን በማኅበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ሚና እና በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚደርስባቸውን ባህላዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ ማሳየት ነው፡፡ለጥናቱ ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎች በቀዳማይና በካልዓይ የመረጃ ምንጮች ተሰብስቧል፡፡ ለዚህ ጥናት በዋናነት መረጃ ለመሰብሰብ ጥቅም ላይ የዋለው ቀዳማይ መረጃ ምንጮች ቃለ መጠይቅ እና የቡድን ውይይት ናቸው፡፡ በቃለ መጠይቅና በቡድን ውይይት የተሰበሰቡትን መረጃዎች እንደ አስፈላጊነታቸው እንደ መረጃ ሰጪዎች ፍላጎት በመቅረፀ ድምፅ፣ በፎቶና በማስታወሻ ደብተር መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡አጥኚው ለዚህ ጥናት የተመረጠው አይነታዊ ምርምር ሆኖ መዋቅራዊ አገልግሎታዊ እና እንስታዊ ንድፈ ሀሳቦችን መሰረት በማድረግ ትንተናው ተካሄዷል፡፡ የምርምሩ አቀራረብም በገላጭና በተንታኝ የምርምር ዘዴ ይዘት ትንተና ላይ ተመስርቷል፡፡ ጥናቱ በእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ካሉት 34 የገጠርና 4 የከተማ ቀበሌዎች ውስጥ በ4 ቀበሌዎች ላይ የተወሰነ ሲሆን መረጃውም ከ8 የቡድን ውይይት የመረጃ አቀባዮችና ከ22 የቃለ መጠይቅ የመረጃ አቀባዮች ተሰብስቧል፡፡የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ ሚና፣ ክፋትና ደግነት፣ ሞኝነትና ብልህነት፣ ከሀዲነትና ታማኝነት እንዲሁም ፈሪነትና ጀግንነት በተመለከተ 125 ምሳሌያዊ ንግግሮች ተሰብስበው በጥናቱ የተተነተኑት 100 ዎቹ ናቸው፡፡ ከመረጃ ትንተናው መረዳት እንደሚቻለው በእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ስለ እናት የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች አብዛኞቹ በአዎንታ የተገለፁ ሲሆን የተወሰኑት ደግሞ በአሉታ መገለፃቸው የአካባቢው ማኅበረሰብ ለእናት ያለውን ከበሬታ ያሳያል፡፡ ስለ ሚስት የተነገሩት ምሳሌያዊ አነጋገሮች የተገለፁት ሴት ለባሏና ለቤቷ አስፈላጊ መሆኗን የሚያወሱ በአዎንታ የተገለፁ ቢኖሩም ለወንዱ ካላቸው አስፈላጊነት አንፃር የተቃኙ እንጂ የራሳቸውን ኑሮ ከመምራት አንፃር የተገለፁ አይደሉም፡፡ከዚህም ባሻገር ለባል የማይበጁና የሚከሰኩሱ እንዲሁም ያለ ባል መኖር የማይችሉ ተደርገው የተሳሉ ናቸው፡፡ በተጨማሪም ሴትን እንደ ልጅ አድርጎ በመቀበል በክል የተዛባ አመለካከት መኖሩ በትንተናው ከተገለፁ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ማየት ተችሏል፡፡ ከኢኮኖሚያዊ አንፃር ሴቶች የወንዶች ጥገኛ ተደርገው ተቀርፀዋል፡፡በምሳሌያዊ አነጋገሮቹ እንደታየው ሴቶች የባሎቻቸውን ኢኮኖሚ የሚያቃውሱ፣ ምንም ሳይሠሩ የሚበሉ ተደርገው ተገልፀዋል፡፡ በቤተሰባዊ ሕይወት ውስጥ ሴቶች የጎላውን ድርሻ የሚወስዱ ቢሆንም ሕፃናትን ተንከባክበው ማሳደጋቸው፣ ለባሎቻቸው፣ ለልጆቻቸውና ለራሳቸው የሚሆን ምግብ ማዘጋጀታቸው እንደ ቀላል ነገር በመቁጠርና ሥራ ፈት አድርጎ በማየት ወንዱ ብቻ ለቤተሰቡ አሳቢና ተቆርቋሪ በመሆን የአካባቢው ማኅበረሰብ ግንዛቤ የተሳሳተ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡

## በአማራ ብሔራዊ ክልል በምስራቅ ጎጃም ዞን የእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ካርታ



# ሙዳዬ ቃላት

## በእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ማህበረሰቡ የሚናገሯቸው ቃላት

ሌማት = በሰርግ ጊዜ ሰዎች የሚያመጡት ምግብ

መቀነት = አርበ ጠባብ ሆኖ ከፈትልና ከሌላ ነገር የሚሰራ የሴቶች የወገብ መታጠቂያ

ማፈሪያ = የሚሰራቸው ስራዎች ጥሩ ያልሆነ ሰው የሚሰደበው የስድብ አይነት ነው

ምንደኛ = ደሞዝተኛ

ቆሞቀር = እድሜዋ የሄደ ባል ያላገባች ሴት

ቆጥ = በአራት ባላ እና በአግዳሚ አጣና የተሰራ ረዘም ያለ አልጋ

በረት = የከብቶች ማደሪያ

በኩር = የመጀመሪያ ልጅ

በትረኛ = ተደባዳቢ/ ዱለኛ

ነሁላላ = ጅል፣ ነገላ፣ነፈዝ፣ ሞኝ፣ቂል፣እንከፍ፣ፈዛዛ፣ ነሆለልማለትነው

አሀው = አሀው የግዕዝ ቃል ሲሆን ወንድም ማለት ነው

እንስራ = ከሸክላ የሚሰራ ባህላዊ የውሀ መቅጃ

ኩሸት = አንድን ነገር ከነባራዊ ሁኔታው አግዝፎ ማሳየት / ግነት

ካራ = ቢለዋ

ያመረቅዛል= ያገረሻል/ ተመልሶ ወደነበረበት ይመለሳል

ይከጅላታል= ይመኛታል/ ያስባታል

ዲቃላ = በህጋዊ መንገድ ሳይጋቡ የተወለደ ልጅ

ድቁስ = በርበሬ ተፈጭቶ የተለያዩ ቅመማ ቅመም ተጨምሮበት ለእንጀራ መብያ የሚያገለግል

ጉልላት = የቤት ቁንጮ

ጉትቻ = የሴቶች የጆሮ ጌጥ

ጋለሞታ = አግብታ የፈታች

ጌታ = ባለ ፀጋ ወይም ሀብታም

ጽርሀ አርያም = ጽርሀ አርያ ማለት የግዕዝ ቃል ሲሆን የሰማይ ደጅ ማለት ነው

ፍቁራን = ፍቁራን ማለት የግዕዝ ቃል ሲሆን የሚዋደዱ/የሚስማሙ ማለት ነው

# ማዉጫ

ርዕስ

ገፅ

ምስጋና ........ i
አጠቃሎ ........ ii
የእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ካርታ ........ iii
ሙዳዩ ቃላት ........ iv
ማውጫ ........ v
ምዕራፍ አንድ ........ 1
መግቢያ ........ 1
1.1የጥናቱ ዳራ ........ 2
1.2የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 3
1.3የጥናቱ ዓላማዎች ........ 3
1.3.1 የጥናቱ ዓብይ ዓላማ ........ 3
1.3.2 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች ........ 4
1.4 የምርምር ጥያቄዎች ........ 4
1.5የጥናቱ አስፈላጊነት ........ 4
1.6የጥናቱ ወሰን ........ 5
1.7የጥናቱ ዘዴ ........ 6
1.7.1 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ........ 6
1.7.1.1. ቃለመ ጠይቅ ........ 6
1.7.1.2. የቡድን ውይይት ........ 8
1.7.1.3. መጠይቅ ........ 8
1.7.1.4. የአጥኚው ስነ ምግባር ........ 9
1.7.2. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ........ 10
1.7.3. የናሙና አመራረጥ ........ 10

1.8. ለጥናቱ የተደረገ ቅድመ ዝግጅትና የመስክ ክንውን ................................ 11
1.9. በመረጃ አሰባሰብ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች እና መፍትሔዎቻቸው..........13
1.9.1. ያጋጠሙ ችግሮች ................................................................ 13
1.9.2. የተወሰዱ መፍትሔዎች ........................................................ 14
ምዕራፍ ሁለት.................................................................................... 15
ክለሳ ድርሳናት .............................................................................. 15
2.1 ፅንሰ ሀሳባዊ ቅኝት ................................................................. 15
2.2 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት.................................................................. 18
2.2.1 መዋቅራዊ አገልግሎታዊ ንድፈ ሀሳብ (Structural Functional Theory) ................................................ 19
2.2.2 እንስታዊ ንድፈ ሀሳብ (Feminist theory).21
2.2.3 ክዋኔ.................................................................. 23
2.2.4 አውድ ................................................................ 23
2.3 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........................................................... 25
ምዕራፍ ሦስት .................................................................................. 30
የእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ አጠቃላይ ገፅታ..................................... 30
3.1 የእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ስያሜ ............................................ 30
3.2 የእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ የመሬት አቀማመጥ እና የአየር ንብረት 32
3.3 የእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ መሰረተ ልማት .................................... 33
3.4 የእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ማኅበራዊ ሕይወት .............................. 34
ምዕራፍ አራት .................................................................................. 36
ስለ ሴቶች የተነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ይዘት ትንተና.............................................36
4.1 የሴቶችን ቤተሰባዊ ዝምድና የሚገልፁ ምሳሌያዊ ንግግሮች .....................36
4.1.1 እናትነትን የሚያንፀባርቁ ምሳሌያዊ ንግግሮች ...................37
4.1.2 ስለ ሚስት የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች .........................39
4.1.3 ስለ ሴት ሕፃናት የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች .................45
4.2 ሴቶች ከኢኮኖሚ አንፃር ያላቸውን ሚና የሚጠቅሱ ምሳሌያዊ ንግግሮች ...48
4.3 የሴቶችን ማኅበራዊ ሚናን በተመለከተ የተነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ........50

4.4 ከክፋትና ከደግነት አንፃር የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ..........................54
4.5 የሴቶችን ሞኝነትና ብልህነት የሚያሳዩ ምሳሌያዊ ንግግሮች .55
4.6 ከፈሪነትና ከጀግንነት በተመለከተ ስለ ሴቶች የተነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች.57
4.7 ከከሀዲነትና ከታማኝነት አንፃር የተነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች...................59
4.8 የሴቶችን ገንዘብ ወዳድነት የሚጠቁሙ ምሳሌያዊ ንግግሮች.....................60
ምዕራፍ አምስት...................................................................................... 62
ማጠቃለያና ይሁንታ .................................................................................. 62
5.1 ማጠቃለያ ............................................................................. 62
5.2 ይሁንታ.................................................................................. 65
ዋቢ ፅሑፎች ............................................................................................ 67
አባሪዎች ................................................................................................. 70
አባሪ 1. ስለ ሴቶች የተነገሩ የምሳሌያዊ ንግግሮች ስብስብ .................................... 70
አባሪ 2. የመረጃ አቀባዬች ፕሮፋይል ..................................................... 75
አባሪ 3. ለተማሪዎች የተዘጋጀ የጽሑፍ መጠይቅ ................................................ 77
አባሪ 4. የቁልፍ መረጃ አቀባዬች የፎቶ ናሙና..................................................... 78
አባሪ 5. ለቃ መጠይቅ የተዘጋጀ መጠይቅ ........................................................ 80

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

ስነ ቃል በፎክሎር ውስጥ ከሚጠኑት ጉዳዮች አንዱ ነው፡፡ ተረት፣ እንቆቅልሽ፣ቃል ግጥም፣ ምሳሌያዊ ንግግር፣ሌጀንድ (አፈ ታሪክ) ጥንትም የነበሩ ዛሬም ያሉ ናቸው፡፡ የስነ ቃልን ተግባር በጥቅሉ መናገር ነገሩን ማቃለል መስሎ ሊታይ ይችላል ፈቃደ (1991 ፣16)፡፡ ስነ-ቃል ከፎክሎር ዘወጎች ውስጥ አንዱና ዋነኛው ነው፡፡ ምሳሌያዊ ንግግር ደግሞ ከስነ-ቃል ዘርፎች ውስጥ ተጠቃሽ ነው፡፡ ምሳሌያዊ ንግግር በመነገር ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል የሚተላለፍ ሲሆን የራሱ የሆነ የመከወኛ አጋጣሚ ያለው ከዋኝና ታዳሚ የሚይዝ የስነ-ቃል ዘርፍ ነው፡፡ ምሳሌያዊ ንግግሮች የማህበረሰቡን ታሪክ፣ ባህልና የኑሮ ዘይቤን የሚያንፀባረቁ ናቸው፡፡

እነብሴ ሳርምድር ወረዳ ማኅበረሰብ ባህሉን፣እምነቱን፣ ስሜቱን፣ምኞቱንና ፍላጎቱን የሚያንፀባርቅባቸው የተለያዩ ስነ-ቃሎች አሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ ተረት፣ ምሳሌያዊ ንግግር፣ የሥራ ግጥሞች፣ የእረኞች ግጥም፣ አፈታሪክ. . . ወ.ዘ.ተ የሚጠቀሱት ናቸው፡፡ እነዚህ የተለያዩ ስነ ቃሎች የእነብሴ ሳር ምድር ወረዳን ማኅበረሰብ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ያንፀባርቃሉ፡፡ይህ ጥናትም ያተኮረው በእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ስለ ሴቶች የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ላይ ነው፡፡ ጥናቱ የአካባቢው ማኅበረሰብ ስለ ሴቶች በምሳሌያዊ ንግግር አማካኝነት ምን መልእክት እንደሚያስተላልፉ፣ የማኅበረሰቡን ምኞትና ፍላጎት፣ አጠቃላይ የአካባቢውን ማኅበረሰብ የሕይወት ልምድ ምን እንደሚመስል በጥልቀት አሳይቷል፡፡

ምሳሌያዊ ንግግር በተለያዩ ማኅበራዊ አጋጣሚዎች ወይም ዓውዶች ላይ የሚከወን ቃላዊ ፈጠራ ሲሆን የአንድን ማኅበረሰብ ባህል፣ወግና ልማድ እንዲሁም ታሪክ ማስተላለፊያ እና ልዩ ልዩ ክስተቶችን የሕይዎት መልኮችን መግለጫ ኪነ ጥበብ ነው፡፡

ይህ ጥናት በአምስት ምዕራፎች የተከፈለ ሲሆን በመጀመሪያው ምዕራፍ የጥናቱ ዳራ፣የጥናቱ አነሳሽ ችግር፣ የጥናቱ አላማ፣የጥናቱ ወሰን፣የጥናቱ አስፈላጊነት፣የጥናቱ

የምርምር ጥያቄዎች፣የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ፣የመስክ ክንውን እና በጥናቱ ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሄዎችን ይዟል፡፡

ሁለተኛው ምዕራፍ ፅንሰ ሀሳባዊ ቅኝት፣ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት እና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት የያዘ ሲሆን ምዕራፍ ሦስት ለጥናቱ የተመረጠው ወረዳ አጠቃላይ ገጽታ የወረዳው ስያሜ፣የመሬት አቀማመጥና የአየር ንብረት፣መሰረተ ልማት እና ባህላዊና ማኅበራዊ ሕይወት አካቶ ይዟል ፡፡

ምዕራፍ አራት ስለ ሴቶች የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ይዘት ምን እንደሚመስል ከቤተሰባዊ ዝምድና ፣ኢኮኖሚ፣ማኅበራዊ ሚና፣ ክፋትና ደግነት፣ ሞኝነትና ብልህነት፣ ከሀዲነትና ከታማኝነት እንዲሁም የሴቶችን ገንዘብ ወዳድነት የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ተተንትኗል፡፡ መጨረሻው ምዕራፍ ደግሞ የማጠቃለያ፣ የይሁንታ ሀሳብ፣ ዋቢ ፅሑፎች እና አባሪዎችን የያዘ ነው፡፡

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ይህ ጥናት የሚያተኩረው በእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ በሚገኙ ማኅበረሰቦች ስለ ሴቶች የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ላይ ነው፡፡ የእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ዋና ከተማ የሆነችው መርጡለማርያም በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በምስራቅ ጎጃም ዞን የምትገኝ ሲሆን ከአዲስ አበባ 364 ኪ.ሜ ከክልሉ ዋና ከተማ ባህር ዳር 182 ኪ.ሜ እንዲሁም ከዞኑ ከደብረ ማርቆስ 195 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ትገኛለች፡፡ እነብሴ የክርስትና መዲና ከመሆኗ በተጨማሪ በኢትዮጵያ በሁለተኛ ደረጃ ቤተ ክርስቲያን የታነፀባት ወረዳ ናት፡፡ በወረዳው ውስጥ 95% የሚሆነው የአካባቢው ማኅበረሰብ በግብርና የሚተዳደር ሲሆን ቀሪው 5% የሚሆኑት በተለያዩ የሥራ መስኮች (በመንግሥት ሥራ ፣ በንግድ፣ በሽመና እና በአንጥረኝነት) ሥራ ላይ ተሰማርተዉ ይገኛሉ፡፡

ወረዳዋ 34 የገጠር ቀበሌዎች እና 4 የከተማ ቀበሌዎች አሏት፡፡ እነዚህ የገጠር ቀበሌዎች የተለያዩ መልካምድራዊ አቀማመጥ ያላቸው ሲሆን የአየር ንብረቱም ደጋ፣ ወይና ደጋ፣ ቆላ እና ውርጭ ነው፡፡

የእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ማኅበረሰብ አያሌ ቁሳዊ እና ባህላዊ መገለጫዎች አሉት፡፡ ማኅበረሰቡ እምነቱን፣ ምኞቱን፣ ደስታውን፣ ሀዘኑን ወ.ዘ.ተ የሚገልፅባቸው የርካታ ስነ ቃላዊ ሀብቶች ባለቤት ነው፡፡ ከነዚህ የስነ ቃል ሀብቶች ምሳሌያዊ ንግግር አንዱ ነው፡፡ በዚህ ጥናት የተፈተሹት ሴቶችን የተመለከቱ ምሳሌያዊ ንግግሮች ናቸው፡፡ የሴቶችን ታማኝነትና ክህደት፣ ሞኝነትና ብልህነት፣ ፈሪነትና ጀግንነት፣ ማህበራዊ ሚና ወ.ዘ.ተ መሰረት አድርገው በአውንታና በአሉታ መንገድ ስለ ሴቶች የተነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮችን በመሰብሰብ በይዘታቸው ላይ ትንታኔ ተሰጥቷል፡፡

## 1.2 የጥናቱን አነሳሽ ምክንያት

በርዕሰ ጉዳዩ ላይ እንዳጠና ያነሳሳኝ ምክንያት እነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ትውልድ ቦታየ ስለሆነ እዚያ በነበርኩበት ጊዜ ሴቶችን የሚመለከቱ ምሳሌያዊ ንግግሮች ሲነገሩ እየሰማሁ የኖርኩ ስለነበር እና በተማርኩት ትምህርት መሰረት ጉዳዩን ለማጥናት ካለኝ ጥልቅ ፍላጎት ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የተጠኑ ጥናቶችን ስፈትሽ በዞኑ እንዲሁም በወረዳው ከዚህ በፊት ስለ ሴቶች የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ላይ የተሠራ ጥናትና ምርምር አለመኖሩ ነው፡፡

## 1.3 የጥናቱ ዓላማዎች

### 1.3.1 የጥናቱ ዓብይ ዓላማ

- የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ስለ ሴቶች የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮችን በይዘታቸው መተንተን ማሳየት ነው፡፡

### 1.3.2 የጥናቱ ዝርዝር አላማዎች

ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡

- በማኅበረሰቡ ውስጥ ሴቶች ከወንዶች ጋር ያላቸውን ትስስር ማሳየት፡፡

- የምሳሌያዊ ንግግሮችን ተስተላልፎ በማን፣ እንዴት እና ለምን እንደሆነ መግለፅ፡፡
- ስለ ሴቶች የሚነገሩ ምሳሌዊ ንግግሮች በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚያበረክቱትን አስተዋፅኦ መግለፅ፡፡
- ስለ ሴቶች የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች በማኅበረሰቡ ውስጥ ያላቸው አሉታዊ ገፅታ ማሳየት ነው፡፡

## 1.4 የምርምር ጥያቄዎች

የጥናቱን  አላማ ከግብ ለማድረስ የሚከተሉት ጥያቄዎች በጥናቱ ይመለሳሉ፡፡

- በእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ስለ ሴቶች የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ይዘት ምንድን ነው?
- ሴቶች በማኅበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ድርሻ በመግለፅ ረገድ የምሳሌያዊ ንግግሮች ሚና ምንድን ነው?
- በእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ስለ ሴቶች በአዎንታ የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ያላቸው ማኅበራዊ ጠቀሜታ ምንድን ነው? የሚሉ ጥያቄዎች በዚህ ጥናት ውስጥ የሚመለሱ የምርምር ጥያቄዎች ናቸው፡፡

## 1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት

በእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ስለ ሴቶች የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ይዘት ትንተና ላይ ያተኮረው ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ያስገኛል ተብሎ ይታሰባል፡፡

- ስለ ሴቶች በሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች አማካይነት የማኅበረሰቡን ባህል፣ ወግና ልማድ ለማያውቁለማሳወቅ ይጠቅማል፡፡
- የሴቶችን ጉዳይ ለሚከታተሉ አካላትና ስለ ስርዓተ ፆታ ጥናት ለሚያደርጉ ተመራማሪዎች የተወሠነ መረጃ ይሰጣል፡፡
- ሴቶች በማኅበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ሚና እና የሚደርስባቸውን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ ለማሳየት ይጠቅማል፡፡

- ጥናቱ በቃል እየተወራረሱ የመጡ ምሳሌያዊ ንግግሮችን በጽሑፍ የያዘ ስለሆነ በሰነድነት ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በአማራ ክልል በምስራቅ ጎጃም ዞን በእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ላይ ያተኮረ ሲሆን በውስጡ ካሉት 34 የገጠር ቀበሌዎች እና 4 የከተማ ቀበሌዎች ውስጥ በ3 የገጠር ቀበሌዎች እና በ1የከተማ ቀበሌ ላይ የተወሰነ ነው፡፡ ከ4 ቀበሌዎች ውስጥ ሁለቱ ወይና ደጋ፣ ሁለቱ ቆላ እና ውርጭ ናቸው፡፡ እነዚህ 4 ቀበሌዎች የተመረጡት በአየር ንብረታቸው ነው፡፡ ስለሆነም ጥናቱ ያተኮረው በ4 ቀበሌዎች በተለያዩ አጋጣሚዎች ስለ ሴቶች የሚነገሩ አዎንታዊና አሉታዊ ምሳሌያዊ ንግግሮች ላይ ነው፡፡ ምሳሌያዊ ንግግሮች የሚነገሩበት አጋጣሚ ሥራን፣ ፀባይን፣ ሙያን፣ እውቀትን፣ ኢኮኖሚን፣ ጀግንነትን፣ ታማኝነትን መሰረት ያደረገ ነው፡፡የዚህ ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ በዋናነት ቃለ መጠይቅ እና የቡድን ውይይት መረጃ ተሰብስቧል፡፡ ቃለ መጠይቅ በዋናነት የተመረጠበት ምክንያት ተጨባጭ የሆኑ መረጃዎችን በአካል ተገኝቶ የእድሜ ባለፀጋ ከሆኑት ለመገንዘብ የተሻለ በመሆኑና ተጠያቂዎቹ ማንበብ መጻፍ የማይችሉ ሊኖሩ ስለሚችሉ የሚነረውን በትክክል ማስታወሻ ለመያዝ አመቺ በመሆኑ ነው፡፡ ገላጭ የምርምር ዘዴን በመጠቀም ስለ ሴቶች የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ተተንትነዋል፡፡ ከናሙና አመራረጥ አንፃር አላማ ተኮር ናሙና ዘዴ በመጠቀም መረጃ አቀባይዮች በመምረጥ ጥናቱ ተካሂዷል፡፡

## 1.7 የጥናቱ ዘዴ

በዚህ ክፍል ለጥናቱ ግልጋሎት የዋሉ የመረጃ አይነቶች፣ መሰብሰቢያ ዘዴዎች፣ የናሙና አመራረጥ ዘዴዎች፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ቁሶችና አጥኚው ስለተከተላቸው የምርምር ስነ ምግባሮች ተዳሰውበታል፡፡

### 1.7.1 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

ለዚህ ጥናት ተግባር ላይ የዋሉት ቀዳማይና ካልአይ የመረጃ ምንጮች ናቸው፡፡ ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች ምሳሌያዊ ንግግሮች በሚነገሩበት ማኅበራዊ ዓውድ በክዋኔው የተሳተፉትን በመጠየቅና በመመልከት ስለሴቶች የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች የተሰበሰቡበት ሂደት ነው፡፡ ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮች ሴቶችን በተመለከተ የተሰሩ ጥናታዊ ጽሑፎች፣ የምሳሌያዊ ንግግር መፃሕፍትና ከኢንተርኔት የተገኙ መረጃዎች የተጠቃለሉበት ነው፡፡ በዚህ ጥናት መረጃ የሚሰበሰበው በዋናነት በቃለ መጠይቅና በቡድን ውይይት ነው፡፡ በእነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተሰበሰበውን መረጃ በየፈርጁ ለማደራጀት በገለፃ ስልት ተተንትኗል፡፡

ለዚህ ጥናት መነሻ የሚሆኑ መረጃዎችን ለማሰበሰብ በዋነኛነት ጥቅም ላይ የዋሉት ቃለ መጠይቅና የቡድን ውይይት ናቸው፡፡

### 1.7.1.1 ቃለ መጠይቅ

ቃለ መጠይቅ ለመረጃ አቀባዮች ጥያቄ በማቅረብ መረጃ የሚሰበሰብበት ዘዴ ነው፡፡ በዚህ ጥናትም ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ሆኖ አገልግሏል፡፡ ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ከጽሑፍ መጠይቅ የሚለየው አጥኚው ከተጠኚው ጋር ፊት ለፊት በመገናኘት ቃል ምልልስ በማድረግ ነው፡፡ "ቃለ መጠይቅ የመረጃ አቀባዮችን እውቀት፣ አመለካከት፣ እምነት፣ ስሜትና ፍላጎት ምን እንደሚመስል ለማወቅ ይጠቅማል"Goldstien (1964፣ 104)፡፡

ይህ ጥናት አይነታዊ ምርምር የተጠቀመ እንደመሆኑ መጠን ከሚጠቀምባቸው የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች ውስጥ አንዱ ቃለ መጠይቅ ነው፡፡ በዚህም መሰረት በእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ከሚገኙ 34 የገጠር ቀበሌዎችና 4 የከተማ ቀበሌዎች መካከል 3 ገጠር ቀበሌ (በርላይ፣አምባላይ እና ደምበዛ ቀበሌ) እና 1 ከተማ ቀበሌ ላይሚካኤል ተመርጠዋል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ስለ ሴቶች የሚነገሩ ምሳሌያዊ አነጋገሮች በሁሉም ቀበሌዎች ተመሳሳይ በመሆናቸው ነው፡፡ በነዚህ በተመረጡ የገጠርና የከተማ ቀበሌዎች 22 መረጃ ሰጪዎች ተመርጠው ቃለ ምልልስ ተካሂዷል፡፡ ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው በእድሜ ስብጥር፡-

- ከ15-30 = ወ-2 ሴ-5 ድ-7
- ከ31-45 = ወ-5 ሴ-6 ድ-11
- ከ46 በላይ = ወ-2 ሴ-2 ድ-4 ናቸው፡፡

መረጃ ሰጪዎች የተመረጡት በኢላማ ናሙና (Purposive) ዘዴ ነው። ምክንያቱም ምሳሌያዊ አነጋገሮች የማስታወስና በአውዱ የመጠቀም ችሎታና እያስታወሱ ማቅረብ ከሰው ሰው ይለያያልና በማህበረሰቡ ውስጥ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች በአስታራቂነትና ነገር አዋቂነት ላይ ባላቸው ችሎታ የተመረጡ ናቸው። በመስክ ቆይታም፣ ሴቶችን የተመለከቱ በአሉታና በአውንታ የተነገሩ 125 ምሳሌያዊ ንግግሮች ተሰብስበዋል።

በቃለ መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ ምሳሌያዊ ንግግሩ ሲነገር የነበሩ ሰዎችን ወይም ተሳታፊዎችን በመጠየቅ የተሰበሰበ ነው። ቃለ መጠይቅ ሲዘጋጅ በሁለት መንገድ ነው። እነሱምነ ፃና ዝግ ቃለ መጠይቅ ሲሆኑ የዚህ ጥናት መረጃ የተሰበሰበው በነፃ ቃለ መጠይቅ ነው። ነፃ ቃለ መጠይቅ በአብዛኛው ጥያቄዎች በወረቀት ተጽፈው ላይዘጋጁ ይችላሉ። ተመራማሪው ጉዳዩ በአዕምሮው ወይም በጥያቄ ወቅት ሊነሱ ይገባቸዋል የሚላቸውን ነጥቦች ብቻ በወረቀት በማስታወሻ ይዞ ከተጠያቂው ጋር በሚያደርገው ውይይት ጥያቄዎችን እያነሳ ማብራሪያ እየጠየቀ መረጃ ይሰበስባል። ስለዚህ በዚህ ዘዴ ጠያቂም እንደችሎታው ጥያቄዎችን ከአዕምሮው እያፈለቀ የመጠየቅ፣ ተጠያቂዎችም ያላቸውን አስተያየት፣ አመለካከት፣ ዝንባሌ … የመግለፅ ነፃነት አላቸው። ከዚህም የተነሳ በርካታ ጥልቅ መረጃዎችን መሰብሰብ ይቻላል ያለው (2001፣ 185-186)። መረጃ በሚሰበሰብበት ጊዜ በእድሜም በፆታም በማሰባጠር ተመሳሳይ ጥያቄዎችን የተለያዩ ሰዎችን በመጠየቅ የመረጃዎችን ትክክለኛነት ማወቅ ይቻላል።

በአጠቃላይ ቃለ መጠይቅ ለመረጃ አቀባዮች ጥያቄ በማቅረብ መረጃ የሚሰበሰብበት ዘዴ ነው። በዚህ ጥናትም ቃለ መጠይቅ ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ በመሆን አገልግሏል። ይህ የመረጃ መሰብሰያ ዘዴ ከፅሁፍ መጠይቅ የሚለየው ጠያቂው ከተጠያቂው ጋር ፊት ለፊት በመገናኘት ቃለ ምልልስ ስለሚያደርግ ነው።

#### 1.7.1.2 የቡድን ውይይት

ቡድን ተኮር ውይይት የሚካሄደው በጥናቱ ዙሪያ በቂ መረጃ ሊኖራቸው ይችላል ተብሎ የሚታሰቡ ሰዎችን በመውሰድ በሚነሳው ጥያቄ ዙሪያ በቡድን በመሆን እየተወያዩ መረጃ እንዲሰጡ በማድረግ ሲሆን ተሳታፊዎቹ እስከ 12 ሊደርሱ ይችላሉ ያለው

(2001፣197)። ይህ ዘዴ ከቃለ መጠይቅ የሚለየው ዋናው ነጥብ በርካታ ሰዎች በአንድ ጊዜ መሳተፋቸው እና አጥኚው የአወያይነትን ሚና ወስዶ ተወያዮች ከጥናቱ ይዘት እንዳያፈነግጡና ግልፅ ያልሆኑ ሀሳቦችን እንዲብራሩ ማድረግ መቻሉ ነው።በቃለ መጠይቅ እና በምልከታ ያልተገኙ መረጃዎችን እና ሌላ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት በተተኳሪ ቡድን በመወያየት የመረጃውን ትክክለኝነት በማረጋገጥ አስፈላጊውን መረጃ ለመሰብሰብ ያስችላል።

ለቡድን ውይይት በናሙናነት የተመረጡ ሰዎች ስምንት ሲሆኑ ሁሉም መረጃ በማቀበል ደረጃ  የጎላ ድርሻ ነበቸው። የቡድን ውይይቱ የተደረገው ለሁለት ጊዜ በደምበዛና በበርላይ ቀበሌ ነው።
የተመረጡትም ከአራቱም ቀበሌዎች ሁለት ሁለት ተሳታፊዎች ሲሆን አምስቱ ሴቶች ሲሆኑ ሶስቱ ደግሞ ወንዶች ናቸው። ምክንያቱም ይህ ጥናት ዋና ትኩረቱ በእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ስለ ሴቶች የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ይዘት ትንተና  ላይ ነው። በናሙናነት የተመረጡት ሁሉም መረጃ አቀባዮች በኢላማ ናሙና ዘዴ ነው።

### 1.7.1.3 መጠይቅ

መጠይቅ በዚህ ጥናት ውስጥ በመረጃ መሰብሰቢያነት የዋለው መረጃ ሰጪዎች ምሳሌያዊ አነጋገሮች በጽሑፍ እንዲሰጡ ነው። በዚህ ስልት መረጃዎች መሰብሰብ የተቻለው በተመረጡ ቀበሌዎች ውስጥ በሚገኙ ሁለት ትምህርት ቤቶች አማካይነት ነው።

ከተመረጡ ቀበሌዎች ውስጥ ባሉት የበርላይ እና የአብርሀ ወ አፅብሀ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ተማሪዎች ከቤተሰቦቻቸው ሴቶችን በተመለከተ የሚነገሩ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ጠይቀው በጽሑፍ እንዲያመጡ ተደርጎ 40 ያህሉ ተማሪዎች ምሳሌያዊ አነጋገሮች ያመጡ ሲሆን፣ ከርዕስ ጉዳዩ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው 28ቱ ምሳሌያዊ ንግግሮች ለጥናቱ ተመርጠዋል።

በጠቃላይ ለጥናቱ ከተመረጡ ቀበሌዎች በቃለ መጠይቅ፣ በቡድን ውይይትና በመጠይቅ ለጥናቱ ዓላማ ወሳኝ ናቸው ተብለው የታመነባቸው 125 ያህል ምሳሌያዊ አነጋገሮች ተመርጠዋል። እነዚህም በአባሪ የተያያዙ ሲሆን በትንተናው ተካተዋል።

### 1.7.1.4 የአጥኚው ስነ ምግባር

አንድ አጥኚ የሚፈልገውን መረጃ ለማግኘት የሚጠናው ማኅበረሰብ በመምስል ባህሉንና አኗኗሩ ማክበር አለበት፡፡ ከዚህም በላይ ስለራሱ ማንነት፣ ስለጥናቱ አላማና ስለህጋዊነቱ ለተጠኚው አካል ማሳወቅ ከአጥኚው የሚጠብቅ የምርምር ስነ ምግባር ነው፡፡ በዚህም መሰረት አጥኚው ከሚማርበት ተቋም እና ጥናቱ ከሚሠራበት ወረዳ ሥራ አስፈፃሚ የተፃፈለትን የትብብር ደብዳቤ ጥናቱ በሚያካሄድበት ቦታ መረጃ ለሚሰጡ አካላትና ለሀገር ሽማግሌዎች በመስጠትና ዓላማውን በግልፅ በማስረዳት ከመረጃ አቀባዮች ጋር መልካም የሆነ ግንኙነት ፈጥሯል፡፡

አጥኚው ከመረጃ ሰጪዎች ጋር እንደተገናኘ ማንነቱን፣ የሚማርበት ተቋምና የመጣበትን ዓላማ በግልፅ በማስረዳት መረጃ ሰጪዎቹ የተፈለጉበት ዓላማን በግልፅ በማስረዳት አስፈላጊውን መረጃ በመሰብሰብ የመስክ ስራውን በአግባቡ ማከናወን ተችሏል፡፡ መረጃ ሰጪዎችም የሰጧቸው መረጃዎች ለዚህ ጥናት ብቻ በመረጃነት እንደሚያገለግሉ በመግለፅ ምስጢራዊነቱ የተጠበቀ እንደሆነና ስማቸው እንዲጠቀስ የማይፈልጉትን እንደማይገለፅ ማረጋገጫ ተሰጥቷል፡፡

### 1.7.2 የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

አንድ ተመራማሪ ልዩ ልዩ ዘዴዎችን በመጠቀም መጠነ ሰፊ፣ ውስብስብ፣ ያልተደራጀና ያልተቀናጀ መረጃ ይሰበስባል፡፡ ይህ ጥሬ መረጃ ትርጉም በሚሰጥ መልኩ ተደራጅቶ፣ ተጠቃሎ፣ ተተንትኖ እና ተተርጉሞ ካልቀረበ ለአንባቢውም ሆነ ለራሱ ለተመራማሪው የሚያስተላልፈው መልዕክት ግልፅ አይሆንም (ያለው 2001) ፡፡ የተዘጋጀውን መረጃ አጠቃሎ ለማቅረብ እና ትርጉም ለመስጠት በተገቢው መንገድ ሊተነተን ይገባል፡፡ ለዚህ ጥናት ጥቅም ላይ የዋለው የመረጃ መተንተኛ ዘዴ እንደ አስፈላጊነቱ ገላጭና ተንታኝ ዘዴነው፡፡

በመስክ የተሰበሰበው 125 ምሳሌያዊ ንግግር ሲሆን በገለፃ ስልት የተተነተኑት 100 ምሳሌዊ ንግግሮች ናቸው፡፡

በዚህ ጥናት ገላጭና ተንታኝ ዘዴን መጠቀሙ በእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ስለ ሴቶች የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች በአውዳቸው በመሰብሰብ ይዘታቸው ምን እንደሚመስል በመተንተን ማሳየት ነው፡፡ጥናቱ የተነሳበት አላማ ከርዕሰ ጉዳዩ አንፃር በአንድ በተወሰነ ቦታ የተመረጠን ምሳሌያዊ ንግግር በመተንተን ወደ ግኝት ማምጣት ስለሆነ የዚህ የመስክ ሥራ የምርምር አካሄድ በዋናነት ተንታኝ የምርምር አካሄድን የተከተለ ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ ገላጭ የምርምር አካሄድ ተጠቅሟል፡፡

### 1.7.3 የናሙና አመራረጥ

ናሙና በልዩ ልዩ ምክንያቶች የተነሳ የጥናቱን አካላይ አባላት በሙሉ በመውሰድ በጥናታችን ተሳታፊ ለማድረግ ሳንችል ስንቀር ወይም ማሳተፍ አስፈላጊ ሳይሆን ሲቀር ነገር ግን አጠቃላዩን ብንወስድ ልናገኝ እንችላለን ብለን የምናስበውን መረጃ ሊሰጡን የሚችሉ ሰዎችን ሥርዓታዊና ተጠይቃዊ መንገድን በመከተልመርጠን በጥናታችን እንዲካተቱ እና መረጃ እንዲሰጡን የምናደርገው የጥናቱ አካላይ ውስን ክፍል ነው፡፡

የናሙና አመራረጥ ዘዴ የጥናቱን አላማ መሠረት ያደረገ ነው፡፡ስለሆነም ለዚህ ጥናት ጥቅም ላይ የዋለው የናሙና ዘዴ ወሳኝ የናሙና ዘዴ ነው፡፡ ወሳኝ የናሙና ዘዴ ተመራማሪው የራሱን ልምድ፣ እውቀትና ግላዊ ግምገማ መሰረት በማድረግ የጥናቱን ተሳታፊዎች ይመርጣል፡፡ መረጣውን ለማካሄድ የጥናቱን አካላይ አጠቃላይ ባህሪ በሚገባ ማወቅና መገንዘብ የጥናቱን አካላይ አባላትን ብመርጥ የምፈልገውን መረጃ ሊሰጡኝ ይችላሉብሎ በመወሰን የፈለገውን አካል መምረጥ ይቻላል፡፡ መረጃ አቀባዮችም ከአራቱም ቀበሌዎች ሁለት ሁለት አጠቃላይ ስምንት ለቡድን ውይይት ተመርጠዋል፡፡ እነዚህ ቀበሌዎች የተመረጡበት ምክንያት ስለ ሴቶች የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች በሁሉም አካባቢ ተመሳሳይ ስለሆነ እና ሁሉንም ቀበሌዎች የሚወክሉትን ነው፡፡

## 1.8 ለጥናቱ የተደረገ ቅድመ ዝግጅትና የመስክ ክንውን

አንድን የምርምር ስራ ለመስራት በመጀመሪያ የተቀናጀ ዕቅድ ያስፈልጋል፡፡ በመስክ ስራ ላይ የተለያዩ ችግሮች ሊገጥሙን ስለሚችሉ እነዛን ችግሮች የምንፈታበትን መንገድ ማስቀመጥ አስፈላጊ ነው፡፡ ለዚህ ጥናት የሆኑ የተደረጉ ዝግጅቶችም እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

ለጥናቱ የሚሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ወደ መስክ ከመሄዴ በፊት ስለ እነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ማኅበረሰብ ታሪክ ፣ ባህል መልካዓምድራዊ አቀማመጥ እና የተፈጥሮ ሀብቶች የተፃፉ ፅሑፎችን፣ መፅሃፎችን እና መፅሄቶችን እንዲሁም ስለ አካባቢው የሚያውቁ ሰዎችን በመጠየቅ መረጃዎችን ለማሰባሰብ ሞክሬያለው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ጥናቱን ከተፈለገው ግብ ለማድረስ የተለያዩ መረጃዎችን ለመሰብሰብ አጋዥ የሚሆኑ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን የፎቶ ካሜራ፣መቅረፀ ድምፅና የተለያዩ የፅህፈት መሳሪያዎችን ለማዘጋጀት ተችሏል፡፡

ይህ ጥናት ወደ ሚሰራበት ቦታ የተደረገ ጉዞና የመስክ ቆይታ እንደሚከተለው ነው፡፡ በተዘጋጀው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ከመስክ መረጃ የምሰበስብበት ጊዜ እየተቃረበ በመሆኑ ለቃለ መጠይቅና ለተተኳሪ ቡድን ውይይት መነሻ የሚሆኑ ጥያቄዎችን እና መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚያስፈልጉ የፎቶ ካሜራና መቅረፀ ድምፅ እንዲሁም የተለያዩ የጽህፈት መሳሪያዎችን በማዘጋጀት ጥር 20 ቀን 2011 ዓ.ም የመጀመሪያ የመስክ ጉዞዬን አደረኩ፡፡

ጥር 20 ቀን 2011 ዓ.ም ሰኞ ዕለት ከአዲስ አበባ 365 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ወደ ምትገኘው መርጡለማሪያም ጉዞዬን ቀጠልኩ፡፡ ለአስተርዮ ማሪያም ከሚሄዱ መንገደኞች ጋር የሆድ የሆዳችንን እየተጨዋወትን ከቀኑ 10፡15 ሰዓት ላይ መርጡለማሪያም ደረስኩ፡፡ ማክሰኞ ጠዋት ከባህልና ቱሪዝም ቢሮ በመሄድ ከሀላፊው ጋር ተደዋድዬ ስለነበር መረጃ አቀባዮቼን ለማግኘትና መረጃ ለመሰብሰብ ሚረዱኝን ሰዎች አድራሻ እና ደብዳቤ ሰጥተውኛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የመጣሁበትን ጉዳይ እና የጥናቱን ዓላማ በአግባቡ በማስረዳት ስለ ሴቶች በተነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች የተሰሩ ጥናቶች እና በፎቶና

በቪዲዮ የተቀመጡ መረጃዎችን ለማግኘት ብሞክርም ምንም ዓይነት የተደራጀ መረጃ እንደሌለ የክፍሉ ኃላፊ ገለጹልኝ፡፡ ነገር ግን ስለ ሴቶች የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች የሚያውቁትን አንዳንድ መረጃዎች በቃልና በፅሁፍ የምፈልገውን መረጃ መሰብሰብ ችያለሁ፡፡

በማግስቱ ረቡዕ ጥር 22 ቀን 2011 ዓ.ም ጥናቱ ወደሚደረግበት በርላይ ቀበሌ በመሄድ የመጣሁበትን ጉዳይ እና የጥናቱን ዓላማ ለቀበሌው ሽማግሌዎች ለአቶ ቦጋለ ታፈሰ እና ለአቶ አንባው አካሉ ካስረዳሁ በኋላ ስለ ሴቶች በአዎንታና በአሉታ የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮችን መሰብሰብ ችያለሁ፡፡ ሽማግሌዎችን ላደረጉልኝ ትብብር በማመስገን ከእነሱ ጋር ተጨማሪ ሴቶችን ለቃለ መጠይቅ እና ለቡድን ውይይት በመምረጥ የተሳካ ዉሎ አሳልፌያለሁ፡፡ ከዚህ በመቀጠል ዓርብ ጥር 24 ቀን 2011 ዓ.ም የእድሜ ባለፀጋ እናቶችን፣ ለጥናቱ የሚሆነውን መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ የሆኑ፣ ስለ ሴቶች የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ለመግለፅ ከሌሎች የተሻለ ችሎታ ያላቸው መረጃ አቀባዮችን ከሽማግሌዎች ጋር በመምረጥ ቃለ መጠይቅ በመጠየቅ በመቅረፀ ድምፅ እና ማስታዎሻ በመያዝ የምፈልገውን መረጃ መሰብሰብ ችያለሁ፡፡

እሁድ ጥር 26 ቀን 2011 ዓ.ም በደምበዛና አምባላይ ቀበሌ ከቀበሌው የግብርና ባለሙያ ጋር በመሄድ የመጣሁበትን ጉዳይ እና የጥናቱን ዓላማ ለቀበሌው ሽማግሌዎች ለአቶ ከቤው ታረቀኝ፣ ለአቶ ይበልጤ መንግስት እና ወይዘሮ ትዕግስት ማሙዬ ካስረዳሁ በኋላ በቃለ መጠይቅ ስለ ሴቶች በአዎንታና በአሉታ የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮችን ለምን እንደሚነገሩ መሰብሰብ ችያለሁ፡፡

ለጥናቴ አስፈላጊ የሆኑትን መረጃዎች የሰበሰብኩት በአራቱም ቀበሌዎች በመሄድ በቃለ መጠይቅ እና በቡድን ውይይት ነው፡፡የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን በመጠቀም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት መረጃዎችን እስከ የካቲት 12 ቀን 2011 ዓ.ም ከሰበሰብኩ በኋላ ወደ አዲስ አበባ በመመለስ የሰበሰብኳቸውን መረጃዎች በአንድ በማድረግ ማሰባሰብ ችያለሁ፡፡ የሁለተኛው ዙር የመስክ ክንውን ያደረኩት ከመጋቢት 02 እስከ 12 / 2011 ዓ.ም ድረስ በተመረጡት አራት ቀበሌዎች በመጀመሪያው ዙር መረጃዎች በቃለ መጠይቅ፣ በቡድን ውይት እና በመጠይቅ መሰብሰብ ችያለሁ፡፡

## 1.9 በመረጃ አሰባሰብ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሔዎቻቸው

ይህ ጥናት በአብዛኛው በመስክ ሥራ ላይ የተመሰረተ እንደመሆኑ መጠን የተወሰኑ ችግሮችን መጋፈጥ የግድ ነው፡፡ ለወደፊት ለሌላ ተመራማሪ መረጃ ይሆናሉ ያልኳቸው ዋና ዋና ችግሮችና መፍሔዎቻቸውን እንደሚከተለው እገልፃለሁ፡፡

### 1.9.1 ያጋጠሙ ችግሮች

በመስክ ሥራ ክንውን ወቅት ከጋጠሙኝ ችግሮች አንዱና ዋነኛው የትራንስፖርት አለማግኘት ነው፡፡ ምክንያቱም መረጃ ለመሰብሰብ ዓርብ ማለትም 22/06/2011 ዓ.ም ቀን ጀምሮ ስለነበር ወደ ቀበሌዎች ለመሄድ መኪና ባለማግኘቴ ባለንብረቶች በገበያ ቀን ካልሆነ ትርፍ መጫን ስለማይቻሉ ለመሄድ ፍቃድኛ አለመሆናቸው ነው፡፡ የእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ የመንገድና ትራንስፖርት ሀላፊ ለስምሪቱ መኪና በየቀበሌዎች እንዲመደብ ትዕዛዝ ቢሰጡም እንኳ ባለ መኪናዎች በተለያየ ምክንያት ሰበብ በመፍጠር ወደ ቀበሌዎች አለመሄዳቸው ችግር ገጥሞኛል፡፡

በመስክ ቆይታየ እንደተመለከትኩት የእነብሴ አካባቢ ማኅበረሰብ ገበሬዎች ስለሆኑ አብዛኛውን ጊዜ በማኅበራዊ ሕይወት ጉዳዮችን የሚከውኑት በበዓላት ነው፡፡ምሳሌያዊ ንግግሮችን በሚናገሩበት ጊዜ በመቅረፀ ድምፅ ለመቅረፅና ማስታወሻ ለመያዝ ሙከራ በማደርግበት ጊዜ ፍቃደኛ ያለመሆን ችግር ገጥሞኝ ነበር፡፡

በበርላይ ቆርሽ ቀበሌ መረጃዎችን በቃለ መጠይቅ በምሰበሰብበት ጊዜ ጥያቄ ጠይቄ መቅርፀ ድምፅና ማስታወሻ ደብተር ለመጠቀም ስሞክር የተስማሙትን ሀሳብ በመቀየር ትክክለኛውን መልዕክት ለመስጠት ፍቃደኛ ያለመሆን ችግር አጋጥምኛል፡፡ እንዲሁም በደሞበዛ ቀበሌ አብዛኛውን ጊዜ ከውጭ የሚመጡ ሰዎች ምንም ነገር ሲፈልጉ ለአካባቢው ማኅበረሰብ መረጃ አቀባዮች በርከት ያለ ብር ስለሚከፍሏቸው እኔንም በተመሳሳይ ብር እንድከፍላቸው በመጠየቅ ችግር አጋጥምኛል፡፡

### 1.9.2 የተወሰዱ መፍትሄዎች

መረጃ አሰባሰብ ወቅት የትራንስፖርት ችግር ምክንያት የተፈጠረውን ክፍተት እስከ 2፡00 ሰዓት የሚሆነውን ቅርብ ቦታ በእግሬ በመሄድ ከ2፡00 ሰዓት በላይ ርቀት ያላቸው ቀበሌዎች ደግሞ በባህላዊ መጓጓዣ ማለትም በፈረስ በመጠቀም መረጃ መሰብሰብ ችያለሁ፡፡

መቅረፀ ድምፅና በማስታወሻ በምይዝበት ጊዜ ፍቃደኛ ያለሆኑትን የቀበሌውን ግብርና ሀላፊ በመወሰድ ማኅበረሰቡ ለተማረና ለባለሥልጣን ሰው ትልቅ ክብር ስላላቸው የእኔን ዓለማ በመግለፅ መረጃውን በቀላሉ መሰብሰብ ችያለሁ፡፡ መረጃ ለመስጠት ከፍተኛ ገንዘብ የጠየቁኝን መረጃ አቀባዮች የጥናቱን ዓላማ በማስረዳትና በማሳመን ጥናቱ ቢጠና ለእነሱ የሚሰጠውን ጥቅም በመግለፅና ተማሪ እና የወረዳው ተወላጅ መሆኔን በመግለፅ ስራ ፈተው ለእኔ መረጃ የሰጡበትን የምሳ አበል 100 ብር በቀን እንደምሰጥ በመስማማት የምፈልገውን መረጃ መሰብሰብ ችያለሁ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳናት

ይህ ምዕራፍ ከጥናቱ ጋር  በቀጥታም ባይሆን በተዘዋዋሪ ተያያዥነት ያላቸው ስራዎች የተዳሰሱበት ሲሆን ስለ ሴቶች ከሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ጋር ግንኙነት ያላቸውን ነው፡፡

### 2.1 ፅንሰ ሀሳባዊ ቅኝት

ሰዎች ምሳሌያዊ ንግግሮችን በንግግራቸው መሀል ጣልቃ እያስገቡ ምሬታቸውን፣ ምኞታቸውን፣ ሀዘናቸውንና ደስታቸውን ስለ ህይወት ያላቸውን አመለካከት ያንፀባርቁበታል፡፡ በተጨማሪም ቅሬታቸውን የሚያሳውቁበት አስነዋሪ ተግባራትን የሚነቅፉበት እኩይ ተግባራትን የሚያንቋሽሹበት ሰናዩን ደግሞ የሚያወድሱበት በአጠቃላይ ማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ በሚደረጉ ክዋኔዎች ላይ ሂስ የሚሰጥበት መገለጫ ነው፡፡

ምሳሌያዊ አነጋገሮች ለሀሳብ መቋጫ ማጠናከሪያና ግልፅ ማድርጊያ የሚያገለግሉ እጥር ምጥር ያሉ አገላለፆች ናቸው፡፡ ምሳሌያዊ አነጋገሮች የማኅበረሰቡን አሻራ ይዘው የሚነሱ እንደመሆናቸው መጠን በማኅበረሰቡን ውስጥ የሚያደረጉትን እንቅስቃሴዎች መሰረት በማድረግ የሚመሰረቱ ናቸው በመሆኑም የምሳሌያዊ አነጋገሮች ፍች ለመረዳት የተነገሩበትን አውድ በውል ማውቅ አስፈላጊ ይሆናል በተጨማሪም ምሳሌያዊ አነጋገሮች የማህበረሰቡን ወግና ልማድ እንዲሁም ባህሉን መሰረት በማድረግ የሚፈጠሩ እንደመሆናቸው መጠን ምስጢራቸውና አገባባቸውን በውል ለመገንዘብ የፈለቁበትን ማህበረሰብ ወግና ልማድ እንዲሁም ባህል ማወቅና በውል መገንዘብ አስፈላጊ ነው፡፡

ምሳሌያዊ አነጋገሮች እንደሌሎቹ  የስነቃል አይነቶች በተወሰነ ቦታና ጊዜ የሚነገሩ አይደለም፡፡ እንደ ሰርግ ዘፈን ወይም እንደ ለቅሶ ሙሾ የተለየ አጋጣሚ እንዲከሰት አይፈልጉም፡፡ ነገርግን በሰዎች የዕለት ተዕለት ንግግር ጣልቃ እየገቡ እንደየ ርዕስ ጉዳዩና እንደየተናጋሪው ችሎታ ሀሳብን የሚያጠናክሩ፣ የሚያጎሉና ይበልጥ የሚያብራሩ

ናቸው፡፡ በዚህም ሴቶች በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ሚና ምን እንደሚመስል በአውንታና በአሉታ ምልክ ይገልፃሉ፡፡ከዚህ ነተጨማሪ ሽማግሌዎች የተጣሉ ሰዎችን ለማስታረቅ ሽምግለና ሲቀመጡ ነገሩን ፈር ለማስያዝ ይጠቀሙበታል፡፡

ይሁን እንጂ ሁሉም ምሳሌያዊ ንግግሮች ጠቃሚ መልዕክት የሚያስተላልፉ ናቸው ለማለት ያስቸግራል፡፡ በተለይ የሴቶች እኩልነት ባልተረጋገጠበት ሁኔታና ሴቶች የወንድ ጥገኛ ተደርገው በሚታዩበት ማህበረሰብ ውስጥ የሚፈጠሩ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ይህንኑ የሚያንፀባርቁ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ምሳሌያዊ አነጋገሮች የማህበረሰቡ አመለካከት ነፀብራቅ ናቸው፡፡ በሴቶች ላይ ያተኮሩ ምሳሌያዊ ንግግሮችን ማጥናት ህብረተሰቡ ስለሴቶች ያለው አመለካከት ለመረዳትና በጎው አስተሳሰብ የሚዳብርበትን ክፉው ደግሞ የሚወገድበትን ስልት ለማበጀት ይረዳል፡፡

ምሳሌያዊ ንግግር የአንድ ቋንቋ ተናጋሪ ሀብት ብቻ አይደለም፡፡ በሁሉም የቋንቋ ተናጋሪ ሕብረተሰብ ውስጥ ይገኛል፡፡ በሁሉም ማኅበረሰቦች ቋንቋ ውስጥ ስለሚገኝ በተለይ ተጎራብተው በሚገኙ የቋንቋ ተናጋሪ ማኅበረሰቦች ዘንድ ተወራራሽነት የሚያሳበት አጋጣሚ አለ (ጌታሁን አማረ 1947፣)፡፡ እንዲህ አይነት ባህሪ ስላለውም በቀላሉ ከአንድ ቋንቋ ወደ ሌላ ቋንቋ በመዛመት ስር መስደድ ይችላል፡፡ በዚህ ሳቢያ ተመሳሳይነት የሚታይባቸውን ምሳሌያዊ ንግግሮች በሁሉም ተጎራባች በሆኑ ማህበረሰቦች ቋንቋዎች ውስጥ ማግኘት የተለመደ ነው፡፡

ምሳሌያዊ ንግግሮች እጥር ምጥን ያሉ የማኅበረሰቡን የእለት ከዕለት የሕይዎት እንቅስቃሴን የሚያሰዩበ ጊዜና በድንበር የማይወሰኑ በጥንታዊም በዘመናዊም በተማረውም ባልተማረውም ማህበረሰብ የሚዘወተሩ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ምሳሌያዊ ንግግሮች በማህበረሰቡ ውስጥ በስፋት የሚታወቁ ወግና ልማድን ለማሳየት የተዘጋጁ ምጥን ቅመሞች ናቸው፡፡

ምሳሌያዊ ንግግሮች በአለም ላይ ከተለያዩ ባህሎች ውስጥ በህዝቦች አኗኗር ላይ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡ እነዚህም ምሳሌያዊ ንግግሮች በውይይቶች አፅንኦት ለመስጠት እና የተለያዩ ማህበራዊ ህግጋትን ለመግለፅ ያገለግላሉ፡፡ በዚህም ፆታ ተኮር ፍች ይዘው ይገኛሉ፡፡ እንደ Chilisa (2012፣133) ገለፃ ምሳሌያዊ ንግግር ከትውልድ ወደ ትውልድ

የሚሸጋገር ማህበረ-ባህላዊ ክስተቶችን፣ የማህበረሰብን ባህሪያት፣ ክንውኖች ለመግለፅና ለማብራራት የምጠቀምበት መሣሪያ ነው፡፡

Akiriga (2003፣110) ምሳሌያዊ ንግግሮች የህዝቦች ተሞክሮ እና የህይወት ልምድ ስብስቦች ሲሆኑ ጥቂቶችም በአስቸጋሪ መንገድ የተፈጠሩ የህብረተሰቡ ሀብቶች ናቸው በማለት ይገልፃል፡፡ከዚህ በተጨማሪም ምሳሌያዊ ንግግሮች ከዘወትራዊ ወይም ከተለመደው ቋንቋ ይልቅ ሀሳብን በጥልቀት በማስተላለፍና ምስል ከሳች ናቸው፡፡

Miruka(1994፣44-45) ምሳሌያዊ ንግግር ቅልብጭ ያለ ግን ሙሉ በሙሉ ምስጢራዊ ሀሳብ የያዘ፣ በማህበረሰቡ ቅቡል ሆኖ እውነታና ጥበብን ለመግለፅ የሚገለገልበት ነው፡፡ከዚህ በተጨማሪም Miruka ምሳሌያዊ ንግግሮች ቃላዊ ናቸው፡፡ በቃል ከትናንት ወደ ዛሬ ከዚያም ወደ ነገ ይተላለፋሉ፡፡የሰውን ልጅ ባህሪይ ለመግራት አውቅና የተሰጣቸውና የእውነት ማንፀሪያ ተደርገውም ይወሰዳሉ፡፡ በአጠቃቀማቸው በርካታ አውዶች ውስጥ ያገለግላሉ፡፡ የማዝናናት፣ የማስተማር፣ የማስጠንቀቅ/የመምከር . . . አገልግሎት የሚሰጡ ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል የሚተላለፉ ናቸው በማለት ይገልፃል፡፡

ምሳሌያዊ ንግግሮች በጥቂት ቃላት የሚቀርቡ፣ አሉታዊ እና አዎንታዊ መልዕክት የሚያስተላልፉ ናቸው፡፡ማህበረሰቡ በምሳሌያዊ ንግግሮች አማካኝነት ጥሩ የሰሩትና በአውንታ በመቀበል ሲያበረታቱ ማህበረሰቡ የማይፈልጋቸውን በአሉታ ምሳሌያዊ ንግግሮች በመንቀፍ ሴቶችን ያስተምራሉ፣ ያጠናክራሉ፣አጠቃላይ ማህበራዊ ህይወታቸው ምን እንደሚመስል የሚገልፁበት መንገድ ነው፡፡

## የምሳሌዊ ንግግሮች ባህሪያት

- **ተለዋዋጭነት**፡- ምሳሌዊ ንግግሮች ተለዋዋጭ ናቸው ሲባል አንድ ምሳሌያዊ ንግግር መልዕክቱ ሳይለወጥ አንድን ቃል በሌላ ቃል በመተካት በተለየ አገላለፅ መናገር ነው፡፡ ለምሳሌ ኑሮ ካሉት መቃብር ይሞቃል የሚለውን በሌላ ጊዜ

የኑሮነረ አስከፊነት ለመግለፅ እንደዘመኑ ኑሮ ካሉት ፍሪጅም ይሞቃል በማለት መቃብር በፍሪጅ ተለውጧል፡፡

- **እምቅነት**፡- ምሳሌያዊ ንግግሮች በባህሪያቸው እምቅ ናቸው ሲባል በተወሰኑ ቃላት ብዙ መልዕክት ማስተላለፍ ስለሚችሉ ነው፡፡
- **ውስንነት**፡- ምሳሌያዊ ንግግሮች ልክ እንደ ስድ ፅሑፍ የተንዛዛ አይደለም በቃላት የተወሰነ ነገር ግን ብዙ መልዕክት የያዘ ነው፡፡

ሥርዓተ ፆታ ሲባል የእንግሊዝኛውን Gender ለማለት ነው፡፡ሥርዓተ ፆታ፣ ከስነ ሕይወታዊ ደንብ ውጭ በሆነ መልኩ በማኀበራዊ ምደባ (Social stratification) ምክንያት የምናገኘው ወንድነት ወይም ሴትነት ነው፡፡ይህንኑ ሃሳብ Reeves እና Baden (2000፣30) ሥርዓተ ፆታ ማለት የሰው ልጅ ስነ ሕይወታዊ ባህሪ በባህል ዋጋ ተሰጥቶትና ተፈክሮ በማኀበረሰቡ ለሴትነት ወይም ለወንድነት የሚያበቃ መስፈርት የሚበጅበት ሥርዓት ነው ሲሉ ይገልጹታል፡፡

አንስታዊ ንድፈ ሀሳቦች አቀንቃኞች እንደሚሉት "የስነ ፅሑፍ ትልቁ ግብ መሆን ያለበት ይብዛም ይነስም ውጫዊ እውነታ ለሁላችንም እኩልና ያልተዛባ ታማኝ አቅርቦት ማምረት መቻል ነው" Moi, T. (1985፣45)፡፡

በአጠቃላይ የሴትነት ጥናቶች በጨቋኝ እና ነፃ አውጪ የባህል ቅርሶች ግጭት ተጋላጭ የመሆን እድላቸው የበዛ ነው፡፡ የስርዓተ ፆታ አጥኚዎች ትልቁ የጥናት ትኩረታቸው ስነ ፅሁፋዊ፣ ፖለቲካዊና ተዛምዷዊ የሆኑ ባህላዊ መፅሐፎች የስነ ፆታ ክፍፍሎሽ በሴቶቹ ላይ ምን ተፅዕኖ አሳድሯል የሚል ነው፡፡ሌሎች ሁነቶች እንዳሉ ሆኖ ሴቶች የባህል እንቅፋቶች ናቸው ወይም የሴቶች ስብስብ በባህል ውስጥ የተለየ ተደርጎ ይታያል፡፡

## 2.2 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት

በፎክሎር ዘርፍ ከሚጠኑት የስነ-ቃል ዘርፎች ውስጥ አንዱ ምሳሌያዊ ንግግር ነው፡፡ ጥናቱ የተዳሰሰበት ንድፈ ሀሳብ፣ ፅንሰ ሀሳብ፣ ክዋኔና አውድ ተካቷል፡፡

ስነቃል የፎክሎር አንዱ ዘርፍ አንደመሆኑ መጠን ይህን ዘርፍ ለማጥናት የሚረዱ ብዙ አይነት ንድፈ ሀሳቦች አሉ፡፡ ሆኖም ሁሉም አይነት ንድፈ ሀሳቦች በጥናቱ አስፈላጊ ባለመሆናቸው ይበልጥ ለጥናቱ ትንተና የሚያግዙና ጠቀሜታ ያላቸውን ንድፈ ሀሳቦች መምረጥ የጥናቱ አቅራቢ ሚና ይሆናል፡፡

በዚህም መሰረት በዚህ ጥናት የተመረጡት structural functional (መዋቅራዊ አገልግሎታዊ) እና feminist (እንስታዊ) ንድፈ ሀሳቦች ናቸው፡፡

### 2.2.1 መዋቅራዊ አገልግሎታዊ ንድፈ ሀሳብ (Structural functional Theory)

መዋቅራዊነትን ከፎክሎር አንፃር ለመግለፅ የሞከረው ሰለሞን ፎክሎር በሚለው መፅሐፉ፣ ገጽ 74 መዋቅራዊነት በሚለው ንዑስ ርዕሱ ውስጥ በሚከተለው መንገድ ይገልጸዋል፡፡

“የመዋቅራዊነት (ንድፈ ሐሳብ) በተረቶች፣ በሚቶች፣ በኤፒኮች፣ በሥርዓተ ከበራዎች፣ በእምነቶችና በሌሎች ሎሮች ውስጥ ያለውን መዋቅር (Structure) በማሳየት ላይ ያተኮረ ነው፡፡ … መዋቅራዊነት የፎክሎር ንድፈ ሀሳብ በተለያዩ አገራት የሚገኙ ሎሮችን በመሰብሰብ በውስጣቸው ያለውን የሁነቶች ቅደም ተከተል፣ የቅርጽ፣ የድግግሞሽ፣ የአደራረስ (composition)፣ጭብጥ፣ ገፀ ባህርይ አሣሣል፣ የታሪክ፣ የድምጽ፣ የሀረጋት፣ የአረፍተ ነገር፣ የክወና ወዘተ ተመሳስሎዎችን የሚያሳይ ነው፡፡

በፎክሎር የሚጠናው የሰው ልጅ ሕይወት ነው፡፡የሕይወት ገጠመኙ፣ አመለካከቱ፣ ባህሉ፣ እንዲሁም ልማዱ ሲሆን እነዚህ ጥበብ በተሞላበት ዘይቤ የሚያስተላልፍበት የራሱ የሆነ መንገድ አለው ይህም sims and stephens እንዲህ ይገልፀታል፡፡

> `folklore is informally learned unofficial knowledge about the world, ourselves, our communities, our beliefs, our cultures and our traditions, that is expressed creatively through words, music, customs, actions, behaviors and materials. It is also the Interactive,

dynamic process of creating, communicating and performing as we share that knowledge with other people (C.sims martine stephem 2008).

መዋቅራዊ አገልግሎታዊ ንድፈ ሀሳብ የተመረጠበት ምክንያት የሰው ልጅ የተለያዩ ገጠመኞቹ አመለካከትና ባህሉ በተለያየ ሁኔታ ሲያንፀባርቅ ይኖራል። እነዚህ ሁኔታዎች የሚያንፀባረቁበት መንገዶች ግን እንደ የማኅበረሰቡና ባህሉ የአኗኗር ሰርዓትና የእድገት ደረጃው የተለያየ መሆኑ በዘርፍ ጥናት ያደረጉ ምሁራን ይገልፃሉ። በመሆኑም የተለያየ መዋቅር ፈጥሮ እምነቱን፣ እሳቤውን፣ የህይወት ፈልስፈናውን ያራምዳል።

"ሰው ከመሬትና ከሌሎች ገፀ ተፈጥሮዎች ጋር ከሚያደርጋቸው ትግሎች፤ ከቦታ ቦታ ከሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎችና የስደት ጉዞዎች፣ በኃይለኛና በደካማ ግዛቶች መካከል ከሚደረጉጦርነቶች፣ በግጦሽ መሬትና በውኃ ጉድጓድ ሰበብ ከሚነሱ ግጭቶች የሞትንና የሕይወትን በአጠቃላይ የመኖርን ምስጢር ለማወቅ ከሚደረጉ ጥረቶች የሚመነጩ ናቸው። እነዚህ ስነቃሎች በሰው ልጆች በወንድና በሴት፣ በሰውና በእንስሳ መካከል በሚፈጠሩ ግንኙነቶች የሰው ልጅ እንግዳ ለሆኑ የተፈጥሮ ገፅታዎች ካለው አመለካከትና ሥርዓትን ለመፍጠር ከሚያደርገው መፈጨርጨር የሚፈጠሩ ናቸው"(ዘሪሁን አሰፋው 1996፣ 20) ።

ከላይ በተጠቀሰው መልክ የተፈጠሩ ስነቃሎች ዛሬ ላይ ቆመን ለመተንተን አሁን ያሉበትን ሁኔታና (situational context) ከአከዋወን ናቸው። (performance) ጋር አጣምረን ከተናገሩበት ማኅበረሰብ ጋር እያስተያየን መተንተን የምሳሌያዊ አነጋገሮች አንድምታና ጠቀሜታ እንድንረዳ ያስችለናል።

ቋንቋ ከባህል ጋር የተዋሐደና በተግባቦት ወቅትም ያሉ የቋንቋ አጠቃቀም የማኅበረሰቡ የኑሮ ደረጃን ያሳያል። በመሆኑም በቋንቋ ላይ የሚደረግ ስነመዋቅራዊ ጥናት ማኅበረሰቡን የተደራጀበትና የተዋቀረበት ሁኔታም ያሳያል። በተለይ የኢኮኖሚ ደረጃው ዝቅተኛ በሆነ ሀገር ውስጥ የፆታ አወቃቀሩም ቢሆን በእኩልነት ላይ ያልተመሰረተ

በመሆኑ በማኅበራዊ ሕይወታቸው ውስጥም ያላቸው ተሳትፎ የተለያየ መሆኑን ያሳያል፡፡

ለምሳሌ አብዛኞቹ ምሳሌያዊ አነጋገሮች የወንዶች የበላይነት የሚያጎሉ የወንዶችን ጥንካሬ እና አስተዋይነት የሚያንፀባርቁ የተቀደሱና የቤተሰብ ምሳሶ ተደርገው ይሳላሉ፡፡ በተቃራኒው ደግሞ በምሳሌያዊ አነጋገሮች ውስጥ ሴቶች ለማሕበረሰቡም ሆነ ለቤተሰባቸው የሚያበረክቱት ፋይዳ የተዘነጋ ይመሰላል፡፡ ደካማ የወንድ ጥገኛና የቤተሰብ ተጨማሪ ሸክም ተደረገው ተገልፀዋል፡፡ እንዲህም ሆኖ ሴቶች በምሳሌያዊ አነጋገሮች ውስጥ እንዲህ ተደርገው ቢገለፁም ለዘመናት አሜን ብለው ተቀብለው ከመኖር ማኅበረሰቡን የተዋቀረበትና ያመነበትን ልምድ ከመከተል ውጪ አማራጭ አልነበራቸውም፡፡ ምክንያቱም ማኅበረሰቡ በራሱ እምነትና አተያይ ለፈጠረው መዋቅር ተገዢ በመሆኑ ነው፡፡

በሀገራችን በተለያዩ ብሄሮች ባህል ላይ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ከሆነ ሁሉም ብሄረሰቦች የራሳቸው የሆነ የሰርግና የለቀሶ ስርዓት፣ ባህላዊ የእርቅ ስርዓት፣ የአመጋገብና የአዘገጃጀት ስርዓትና ለስርዓቶቹም ተቀባይነነት ያለው ደንብ ያላቸው በመሆኑ ስርዓቱና ደንብ ከሚፈቅደው ውጪ መፈፀም መዋቅሩ ተጠብቆ ከትውልድ ትውልድ ይተላለፋል፡፡

### 2.2.2 እንሰታዊ ንድፈ ሀሳብ (Feminist Theory)

ሌላው በዚህ ጥናት ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለው እንስታዊ ንድፈ ሀሳብ (feminist theory) ሲሆን ለዚህም ሥርዓተ ፆታን እኩልነት ይቃረናሉ ከተባሉ ምሳሌያዊ አነጋገሮች በስተጀርባ ያለውን እውነት ተንትኖ ለማሳየት የሚያግዝ በመሆኑ ነው፡፡ እንስታዊ ንድፈ ሀሳብ የሴቶችን እኩልነትና ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን ለማስፈን ያለመ የፓለቲካ እንቅስቃሴ ነው በተለይ እንደኛ ላሉ በኢኮኖሚ እጅግ ኋላቀር በሆኑ ሀገሮች ሴቶች ከወንዶች ጋር ሲነፃፀሩ ሰብዓዊ መብታቸው የተሸራረፈባቸው፣ የወንድ ጥገኛ እንዲሆኑ ተደርገው የተጨቆኑ የኢኮኖሚ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ የተደረጉና በአጠቃላይ ለብዝበዛ የተጋለጡ ናቸው በሚል መነሻ ሀሳብነት የተቀነቀነ ንድፈ ሀሳብ ነው፡፡

ይህ ንድፈ ሀሳብ በተለይ የቆየው ልማድ የሴቶችን ሰብዕና ዝቅ የሚያደርግና ከወንዶች ጋር እኩል መብት እንዳይኖራቸው ያደረገ በመሆኑ ይህንን ለማስቀረት የሚሰራበት ነው፡፡ በዚህ እምነት አቀንቀኞች መካከል የተወሰኑ ልዩነቶች የሚስተዋሉ ሲሆን ለልዩነቶች ምክንያም ደግሞ ለስርአተ ፆታዊ አድሎ መነሻው ምክንያቱ ምንድ ነው? እንዴትስ መፍታት ይችላል? የሚል እንደሆነ (ብርሀኑ 2006፣40) ጠቅሷል፡፡

ለዚህ መልሳቸው የሚመነጨው ደግሞ ከሚከተሉት ርዕዮተ አለምና የፓለቲካ ስርዓት አንፃር ነው፡፡ አንዳንዶቹ የኢኮኖሚ ሁኔታ በማስተካከል ሴቶች የራሳቸው ገቢ እንዲኖራቸው በማድረግና ከወንዶች ጥገኝነት በማላቀቅ ችግሩን መፍታት ይቻላል የሚል አቋም ያላቸው ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ የወንድና የሴት እኩልነት እንዳይኖር ያደረገው ባህሉ በመሆኑ ግለሰባዊ ግንኙነት በማሻሻል እንደሆነ ያምናሉ (madson 2000)፡፡ ከዚህ ጥናት ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያለው ቲዎሪ ባህላዊ እንስታዊ ቲዎሬ ነው ፡፡ የዚህ ንድፈ ሀሳብ አቀንቃኞች እንደሚያምኑት ከሆነ ለስርዓተ ፆታ ልዩነቱ በየባህሉ ውስጥ ለሴትና ለወንድ የተሰጠው ሚዛናዊ ያልሆነ ሰብዕና ነው የሚል ነው፡፡

በሀገራችን በሚነገሩ ስነቃሎች በተለይም ምሳሌያዊ አነጋገሮች ውስጥም ይህ ሁኔታ ይስተዋላል፡፡ በመሆኑም የወንዶች ገፅታ ከፍ ማድረግና የሴቶች ገፅታ ዝቅ መደረጉ የማኅበረሰቡ ጥቅም ጎድቶታል በሚል የዚህ ፅንስ ሀሳብ አራማጆች ይከራከራሉ፡፡ይህንን ጥቅም ለማስመለስ የሴቶች ገፅታና ሚና ጎልቶ መታየትና መውጣት አለበት ይላሉ፡፡ የዚህ ፅንስ ሀሳብ አራማጆች የወንድና የሴት ስራ ብሎ ባለመከፋፈልና ሴትነት ከሴቶች ዕይታ አንፃር በመቃኘት ችግሩን ማስወገድ ይቻላል ይላሉ፡፡

የዚህ ጥናት ትኩረት በሥርዓተ ፆታ ላይ እንደመሆኑ መጠን ከእንስታዊ ፅንሰ ሀሳብ አንፃር መቃኘቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ ጥናቱ በተካሄደበት ማኅበረሰብ ውስጥ ባለ መዋቅር ውስጥ ከፆታ ጋር በተያያዙ የሴትነትና የወንድነት አስተሳሰብና ውክልና ወደ ትክክለኛ አስተሳሰብ እንዲመጣ ለማድረግ ንድፈ ሀሳብ ተገቢና ወሳኝ ነው፡፡

### 2.2.3 ክዋኔ

ክዋኔ ለፎክሎር ጥናት መሰረት የሆነና መልዕክቱን ከነሙሉ ለዛው ከትውልድ ትውልድ ለማስተላለፍ ዋና መንገድ ነው፡፡ ስለሆነም ከዋኙ አንድን ነገር በሚከውንበት ጊዜ ለታደሚዎች የሚተላለፈውን መልዕክት ከሚከወንበት መቼት ጋር አጣምሮ ማየት አለበት፡፡ ዘሪሁን (1992) ፡፡ ማንኛውም ዓይነት ስነ ቃል በከዋኙ አማካኝነት በአንድ ማህበራዊ አጋጣሚ ወይም የመሰብሰቢያ ምክንያት በተሳታፊዎች ፊት የሚነገር፣ የሚተረት ወይም የሚዜምና በድርጊት የሚቀርብ እንጂ እንደ ስነ ፅሑፍ በአንድ ደራሲ ተደርሶ በወረቀት ተፅፎ የሚነበብ አይደለም፡፡

Sims and Stephen (2005፣ 26) ''The performance approach helped to establish the core of the discipline as the study of artistic expression in groups and specific contexts''. ክዋኔ በአንድ አውድ ውስጥ በቡድንም ይሁን በተናጠል የሚታየውን ጥበብ ለመመርመር እንዲሁም የከዋኙን እና የታዳሚውን ግንኙነት በግልፅ ለማሳየት የሚያስችል ነው፡፡

የክዋኔ የመከወኛ አጋጣሚ የተለያየ ሊሆን ይችላል፡፡ የከዋኙ ማህበራዊ ሕይወት ስነ ቃሉ የሚከወንበት ጊዜና ቦታ፣ ስነ ቃሉ የሚከወነው ቡድናዊና ተናጠላዊ የመሆንና ያለመሆን የመሳሰሉት የክዋኔ የመከወኛ አጋጣሚዎች የተለያዩ መሆናቸውን ማወቅ ይቻላል፡፡

### 2.2.4 ዓውድ

አውድ በፎክሎር ጥናት ውስጥ የክዋኔ ገፅታነው ፡፡ የክዋኔውን መቼት፣ በክዋኔ ወቅት ጥቅም ላይ የዋሉ ቁሳቁሶችን፣ የከዋኙንና የታዳሚውን ግንኙነት የሚያጠቃልል ነው፡፡ አንድ የፎክሎር አጥኚ የሚያጠናውን ጉዳይ በደንብ ለመተርጎም አውዱን በሚገባ መረዳት ሲችል ነው፡፡ አውድ በቃል ግጥም ጥናት ውስጥ አስፈላጊ ነው፡፡ እንደ Okpewho (1992፣ 105) ገለፃ አውድን በሶስት ከፍሎታል፡፡

የገጣሚው/የከዋኙ ሰብዕና፡- እንደ ግለሰብ ከዋኙ ይዞት የቀረበውን ጭብጥ በሙሉ ያመለክታል፡፡ ይኸውም የግል ሙያዊ ዝንባሌ፣ የቤተሰቡ ዳራ /background/ እና የከዋኙ ተሞክሮ እንዲሁም በሙያ ዘርፍ የወሰዳቸው ስልጠናዎች ለክዋኔው ከፍተኛ አስተዋፅኦ አላቸው፡፡የክዋኔው ትዕይንት፡-ከላይ የተዘረዘሩት የከዋኙ ሰብዕናዎች በአንድ ላይ ሆነው በቃላዊ ስነ-ፅሁፍ ክዋኔ ተገቢ አውድ ይሰጡታል፡፡ ይህ ማለት በእያንደንዱ የክዋኔ ትዕይንት/ድባብ አማካኝነት ከከዋኙ አንደበት የሚወጡት ወይም የሚነገሩት ጭብጦች የክዋኔውን አውድ ይፈጥራሉ፡፡ማህበራዊ ወይም ባህላዊ አካባቢ፡- ከቃል ግጥሞች አውድ ውስጥ አንዱና ዋነኛው ማህበራዊ አካባቢ ሲሆን ቃል ግጥም ከሚሰጠው አገልግሎት መካከል ስነ ቃል ለአንድ ማህበረሰብ ደስታን የሚሰጥ ሲሆን ማህበረሰቡን ከስራ ጫና እና ጭንቀት ይገለግላል፡፡

Okpewho (1992፣ 118) ስለ አውድ ምሁራን የተለያዩ አከፋፈልን ቢጠቀሙም አብዛኞችን ሊያስማማ የሚችል የBauman (1986፣ 363) ሀሳብ ነው፡፡ Bauman አውድን ባህላዊ አውድ እና ማኅበራዊ አውድ በማለት ከፍሎታል፡፡ማኅበራዊ ዓውድ በውስጡ ማኅበራዊ መዋቅሮችን እና ማኅበራዊ ግንኙነቶችን ይይዛል፡፡ ማኅበራዊ አውድን በጥልቀት ለመመርመር እንዲያስችል Bauman (1986፣ 363) ላይ እንደገለፀው ማኅበራዊ አውድን በ6 ንዑሳን ክፍሎች ከፍሏቸዋል፡፡

ተቋማዊ አውድ(Institutional context) ፡- እርስ በእርስ ከተሳሳሩ ባህሪዎች እና ማህበራዊ አለባዊያን የተገነባ ለአንድ ዐቢይ ዓላማ የተመሰረት ተቋም ነው፡፡የፍቺ አውድ(Conext meaning)፡- የቀረበውን ቴክስት የማኅበረሰቡ አባላት ምን አይነት ትርጉም እንደሚሰጡት የምንመርምርበት ነው፡፡ የተግባበት ዓውድ(context of cultural domain)፡- የፎክሎር ዘውግ ከሌላ አይነት ፎክሎር ጋር እንዴት ይዛመዳል? የሚለውን አብይ ጥያቄ ይመልሳል፡፡ማኅበራዊ መሰረት(Social base)፡- ፎክሎርን የፈጠረው ምን አይነት ህዝብ እንደሆነ የምንረዳበት ነው፡፡ግለሰባዊ አውድ (Individual context)፡- ከዋኙ የሚከውነውን ጥበብ ከማን፣ እንዴት እና ለምን እንደተማረው የምንረዳበት አውድ ነው፡፡ሁኔታዊ አውድ(context of situation)፡-አንድ የፎክሎር ክዋኔ

በሚከወንበት ጊዜ የሚፈጠሩ ማኅበራዊ እና ግለሰባዊ አጋጣሚዎችን ይመለከታል በማለት Bauman ገልፃል፡፡

በአጠቃላይ አንድ ክዋኔ የሚመለከተው ድርጊቱን ማን ፈፀመው? ምን ተፈፀመ? ለምን ተፈፀመ? ለማን ቀረበ? እና ድርጊቱ መቼና የት ተከወነ? የሚሉትን ጥያቄዎች ክዋኔ የሚያጠቃልላቸው ነገሮች ናቸው፡፡እነዚህ ፎክሎርን በአውድ ለማጥናት የሚያስችሉ ሲሆኑ የሚጠናውን ርዕሰ ጉዳይ ምንነት ገልፀው የሚያሳዩ ናቸው፡፡በጥናቱ የምሳሌያዊ ንግግርን ክዋኔ የምመለከተው በእነዚህ መሰረት ነው፡፡

ዓውድ ማለት የአንድን ማኅበራዊ አጋጣሚ የሚከወንበትን አጠቃላይ ሁነት ማለት ሲሆን ፎክሎሩ የሚከወንበትን መቼት፣ የከዋኙና የተሳታፊው ማንነት፣ የድርጊት ቅደም ተከተል፣ የክዋኔው ህግጋትን እና የታዳሚውና የከዋኙን ማህበራዊና ስነ-ልቦናዊ ሁኔታ አጠቃሎ የሚያይዝ ነው በማለት Finnegan (1977 ፣ 126) ገልፃለች::

## 2.3 የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

ከዚህ ጥናት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው የታተሙና ያልታተሙ የመመረቂያ ፅሁፎች እና ጆርናሎችን ለማግኘት ጥረት ቢደርግም ይህ ጥናት ከተሰራበት ቦታና ርዕስ ጉዳይ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን ማግኘት አልተቻለም፤ይሁን እንጂ በተወሰነ መልኩ የሚቀራረቡ የተለያዩ ጥናታዊ ፅሁፎች ተቃኝተዋል፡፡ ስለሆነም ከዚህ ጥናት ጋር በዘውግ ተያያዥነት ያላቸው ጥናትና ምርምሮች ስራን እና ማህበራዊ ህይወትን መሰረት አድርገው የማህበረሰቡን ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ስነ ልቦናዊ ጉዳዮችን በማሳየት በተለያየ ይዘት የቀረቡ ናቸው፡፡

አስቻለው ቢልልኝ (2012) “Female Disempowerement: Some expressions in Amharic” በሚል ርዕስ ጥናት አካሂዷል፡፡ የጥናቱ አላማ የአማርኛ ምሳሌያዊ ንግግሮችን እና አባባሎችን ከሴቶች አንፃር መመርመር ነው፡፡ይህን አላማ ከግብ ለማድረስ የተጠቀመው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ተሳትፏዊ ምልከታ እና የራሱን ችሎታ በመጨመር መረጃ ሰብስቧል፡፡ በተጨማሪም ሰነድ ፍተሻን በሁለተኛ የመረጃ ምንጭነት ተጠቅሟል፡፡ በዚህ መሰረት የተገኘው መረጃ ተተንትኖ ሴቶች የበታች፣ ወሬኞች፣

ጥገኞች፣ . . . ናቸው፡፡ የተወሰኑ ሴቶች ራሳቸው የወንዶችን የበላይነት እንደሚቀበሉት በጥናቱ ተደርሶበታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሴቶች ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተሳትፏቸው በማህበረሰቡ ውስጥ ዝቅተኛ መሆኑን ጥናቱ አመላክቷል፡፡

የአስቻለው ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ፣ በተጠናበት ጊዜ እንዲሁም ትኩረቱ ከአማራ ክልል ውስጥ በደሴ እና በመረሣ ላይ መሆኑ ልዩነት አለው፡፡ ስለ ሴቶችን የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች መዳሰሱ ያመሳስላቸዋል፡፡

መስፍን መሰለ (2002) "ስለ ሴቶች በተቃርኖ የሚነገሩ የአማርኛ ምሳሌያዊ ንግግሮች" ሴቶችን በሚመለከት የአማርኛ ምሳሌያዊ ንግግሮች የተገለፀው የኅብረተሰብ አመለካከት ምን እንደሆነ ማጤን፣ ስለ ሴቶች በምሳሌያዊ ንግግር የተንፀባረቀውን አመለካከት ምን እንደሆነ መመርመር እና በኅብረተሰቡ ውስጥ ሥር ሰደው ያሉት የተሳሳቱ ግንዛቤዎች የሚቃኑበትን መንገድ ለመጠቆም መሞከር የዚህ ጥናት አላማዎች ናቸው፡፡ ሴትን በአሉታዊ የሚገልፁትን ምሳሌያዊ ንግግሮች ብቻ በማጥናት ህብረተሰቡ ስለ ሴት ልጅ ያለውን አመለካከት እንዲህ ነው ብሎ ማጠቃለል ተገቢ አይደልም፡፡ ሴትን በተመለከተ በአውንታዊነትና በአሉታዊነት የሚነገሩትን እንዲሁም ወንድ ላይ የሚያተኩሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች በቀጥታም ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ስለ ሴት ምን እንደሚናገሩ ከልዩ ልዩ ባህላዊ ጉዳዮች ጋር በማገናዘብ ማጥናት የጥናቱን ውጤት ሚዛናዊ ያደርገዋል በማለት ገልጧል፡፡ ሴት ልጅ በማህበረሰቡ ውስጥ ያላትን ባህላዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታን ለመረዳት ያስችላል፡፡ ከዚህ በላይም የሚያጋጥማትን እንቅፋት በማስወገድ ወደ ተሻለ ደረጃ እንድትደርስ ለመረዳት ትክክለኛ አማራጭነው በማለት ግኝቱን አስቀምጧል፡፡ የመስፍን ፅሑፍ ጠንካራ ጎን ሴቶች በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ጉዳዮች የሚያጋጥማቸውን እንቅፋት በማስወገድ ወደ ተሻለ ደረጃ እንዲደርሱ ትክክለኛ አማራጭ እንዲይዙ ሙከራ መደረጉ ነው፡፡

የመስፍን መሰለ ፅሑፍ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳሰለው ስለ ሴቶች በአውንታና በአሉታ መልክ የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ላይ ትኩረት ማድረጉ ሲሆን ልዩ የሚያደርገው ጥናቱ የተሰራበት ቦታ ነው፡፡

ብርሀን አሰፋ (2009)"በተረቶች ውስጥ የታዩ የሥርዓተ ጾታና የሥልጣን ኢፍትሃዊ መስተጋብሮች" በሚል በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂውማኒቲስ የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ ለአማርኛ ቋንቋ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር በፎክሎር ለፍልስፍና ዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት ተደርጎል።

ጥናቱን ለማካሄድ ግላዊና አካዳሚያዊ ገጠመኞች የገፉት ሲሆን እነዚሁ አነሳሽ ምክንያቶች በተረቶች ውስጥ የታዩ የሥርዓተ ጾታና የሥልጣን ኢፍትሃዊ መስተጋብሮች እንዴት ተሰናስለው እንደቀረቡ በዝርዝርና በጥልቀት ማሳየት የጥናቱ ዓቢይ ዓላማ ነው። ሥርዓተ ጾታዊ አድልዎ ሰፊ የባህል መሰረት እንዳለው፣ይህም በተረቶች ውስጥ ተሰናስሎ እንደ ቀጠለ ጥናቱ ጠቁሟል።ሆኖም ተረቶች የሴትን ከወንድ እኩል አለመሆን ለማሳየት ተብለው ቢተረኩም ከእንስታውያን ፊለግ አንጻር ሲታዩ ሴቶች ብልሆች፣መፍትሄ አመንጪዎች ለማወቅ ከፍያለ ጉጉት ያላቸው መሆናቸውን ጥናቱ አሳይቷል።

የብርሀን ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው የመረጃ መሰብሰቢያው እና በሴቶች ላይ ትኩረት ማደረጉ ሲሆን ልዩነቱ ደግሞ ይህ ጥናት ሴቶች ላይ ብቻ ያተኮረ ሲሆን የብርሀኑ የፆታ ንፅፅር ላይ ነው።

መዓዛ ከበደ(2006) ‹‹በወላይታና ጋሞ ምሳሌያዊ ንግግሮች የሚታዩ ፆታ ተኮር አዎንታዊና አሉታዊ ተበላልጦዎች ትንተና›› በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ከፊል ማሟያነት ጥናት አድርጋለች። የመዓዛ ጥናት አላማው በጋሞና በወላይታ ብሔረሰብ ቋንቋ የወንድና የሴት አዎንታዊ እና አሉታዊ ተበላልጦ የሚያሳዩ ምሳሌያዊ ንግግሮችን ለይቶ ማመልከት የመፍትሔ አቅጣጫ ማስቀመጥ የሚል ነው። ጥናቱ የተጠቀመው በገላጭ የምርምር ዘዴ ሲሆን የጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ቃለ መጠይቅ ነው።

የጥናቱ ግኝትም በሴቶች ላይ የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች በአብዛኛው አሉታዊ መሆናቸውን ያሳያል። ከዚህ በተጨማሪ ኅብረተሰቡ ስለ ሴቶች የሚነገሩ አሉታዊ

ምሳሌያዊ ንግግሮች ላይ ግንዛቤ ኢንዲኖረው የኅብረተሰቡን አመለካከት በመቀየር ሴቶችን የሚያወድሱትን በማጠናከር የሴቶችን ሁለንተናዊነት ማሳየት ተገቢ ነው በማለት ተጠቃሏል፡፡

የመዓዛ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ስለ ሴቶች የሚነገሩ አዎንታዊና አሉታዊ ምሳሌያዊ ንግግሮችን መተንተን ሲሆን ልዩ የሚያደርገው የወንድና የሴት ተበላልጦ የሚያሳዩ ምሳሌያዊ ንግግሮችን መተንተኑ ነው፡፡ ይህ ጥናት ግን ስለ ሴቶችየሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ይዘት ትንተና ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ጥናቱ የተሰራበት ቦታ፣ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴው የተለያየ ነው፡፡

በአጠቃላይ የመዓዛ ጥናት  በዲግሪ ደረጃ በዚህ መልኩ መሠራቱ የወንድና የሴት አሉታዊና አዎንታዊ ምሳሌያዊ ንግግሮች የፆታ ተበላልጦን ለማሳየት መሞከሩና ብሔረሰቦች ምሳሌያዊ ንግግር ካለው የባህልና የቦታ ልዩነት ለማሳየት መሞከሩ ጠንካራ ጎኑ ነው፡፡

መኮንን አስማማው(2007)"በደለንታ ወረዳ የአበሹቴ እና የኽኽይበሌ ቃል ግጥሞች ክዋኔ እና ይዘት ትንተና" በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፎክሎርና ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል በሁለተኛ ዲግሪ ጥናት አድርጓል፡፡ የጥናቱ ዋና አላማ የደለንታ ወረዳ የአበሹቴ እና የኽኽይበሌ ቃል ግጥሞች እንዴትና መቼ እንደሚከወኑ ማሳየት ነው፡፡ የጥናቱ የአበሹቴ እና የኽኽይበሌ ቃል ግጥሞች ውስጥ የአከዋወን ልዩነት መኖሩን እና የደለንታ ወረዳ ህብረተሰብ በቃል ግጥሞቹ አማካኝነት ባህሉን በመጠበቅና ማንነቱን ማንፀባረቅ ነው፡፡ የቃል ግጥሞቹ የመከወኛ አጋጣሚዎች  ክብር በዓላትን መሰረት ያደረገ ሲሆን የሚጀምረው ከህዳር 21 ቀን ጀምሮ እስከ ፋሲካ ድረስ በሚከበሩ ንግስትና ክብር በዓለትላይ የሚያተኩር  ነው፡፡

የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴው የቡድን ውይይት፣ ምልከታና ቃለ-መጠይቅ ነው፡፡ የመረጃ መተንተኛው ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሀሳብ ነው፡፡የመኮንን ጥናት ጠንካራ ጎኑ ስለ ወንዶችና ስለ ሴቶች የሚገጠሙ የአበሹቴ እና የኽኽይበሌ ቃል ግጥሞች ላይ በማተኮር ትንተና

ማድረጉ ነው፡፡ ደካማ ጎኑ ደግሞ ቃል ግጥሞቹ በንግስ/በክብረ በአላት ላይ ብቻ የተወሰነ መሆኑ  ሀይማኖታዊ ይዘቱ ያመዘነመሆኑ ነው፡፡

በአበሹቴ እና በኸኽይበሌ የሚከውኑቃል ግጥሞች  የደለንታ ህዝብ ፍላጎትና ምኞች የሚያንፀበርቁ ሴቶች ከማህበረሰቡ ያፈነገጡ ወይም ማህበረሰቡ የማይፈልገውን ድርጊት የሚፈፅሙ አካላትን የሚነቅፉ እንዲሁም የማህበረሰቡን እሴት የሚጠብቁትን የሚያወድሱ በሚል በፍረጃው አሳይቷል፡፡

የመኮንን ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው በሴቶች ላይ ያተኮረ መሆኑና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴው ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅ እና የቡድን ውይይት መሆኑነው፡፡ይህ ጥናት ልዩ የሚያደርገው ትናቱ ከሚሰራበት ቦታ አንፃር በእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ስለ ሴቶች የሚሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ይዘት ትንተና ሲሆን ትኩረቱ ሴቶች ላይ ሆኖ በአካባቢው ማህበረሰብ ሴቶች ምን ሲሰሩ ይወደሳሉ ምን ሲሰሩ ይንቋሸሻሉ የሚለውን ምሳሌያዊ ንግግሮች በሚነገሩበት አውድ መሰረት ገላጭ ወይም ተንታኝ የምርምር ዘዴን በመጠቀም የሚያስተላልፉትን መልዕክት ምን እንደሆን ያሳያል፡፡የመኮንን ጥናት በፆታ ልዩነት ላይ ተመስርቶ የአበሹቴ ቃል ግጥሞች ሴቶችን ለማወደስና ለመሳደብ ሲሆን በኸኽይበሌ ቃል ግጥሞች ደግሞ ሴቶችን በማወደስ ብቻ ሲያልፏቸው በአብዛኛው ወንዶችን የሚሳደቡ እና በጥቂቱ የሚያወድሱ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ቀዳሚ ጥናቶች በጥቅሉ ስለሴቶች ጉዳይ ያንሱ እንጂ የሚደርስባቸውን ማህበራዊ ፣ ፖለቲካዊ እና ስነ ልቦናዊ ችግር በማሳየት ክፍተቱን ለመሙላት ጥረት አልተደረገም፡፡ ይህ ጥናት ሴቶች በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ሚና በማሳየት እና በምሳሌያዊ ንግግሮች አማካኝነት በማህበረሰቡ የሚደርስባቸውን ተፅዕኖ  በማሳየት ከወንዶች በተሻለ ሀላፊነት እና ተግባር እንዳላቸው ያሳያል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

# የአነብሴ ሳር ምድር ወረዳ አጠቃላይ ገፅታ

በዚህ ክፍል የእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ አጠቃላይ ገፅታን የሚያሳያዩ ከጥናቱ ጋር ቁጥተኛ ግንኙነት ያላቸው መረጃዎች ቀርበዋል፡፡ በውስጡም የወረዳው መልከ ምድራዊ አቀማመጥ፣ የአየር ንብረት፣ የህዝብ ስርጭት፣ መተደደሪያ ኢኮኖሚ፣ የመሰረተ ልማት አወታሮችና የማኅበረሰቡን የዕለት ከዕለት የኑሮ እንቅስቃሴ ተካቷል፡፡

## 3.1 የእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ስያሜ

የእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ በምስራቅ ጎጃም ዞን ከሚገኙት 18 ወረዳዎችና 2 የከተማ አስተዳደሮች አንዷ ነች፡፡ የእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ዋና ከተማ መርጡለማርያም ከአዲስ አበባ 364 ኪ.ሜ፣ ከክልሉ ዋና ከተማ ባህር ዳር 182 ኪ.ሜ እንዲሁም ከዞኑ ዋና ከተማ ደብረ ማርቆስ 195 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ትገኛለች፡፡ የወረዳዋ ዋና ከተማ መርጡለማርያም በምስራቅ ደቡብ ወሎ፣ በምዕራብ ጎንቻ ሲሶ እነሴ፣ በደቡብ እናርጅ እናውጋና በሰሜን ደቡብ ጎንደር ያዋሰኗታል፡፡ ወረዳዋ በ34 የገጠርና በ4 የከተማ ቀበሌዎች የተከፈለች ናት፡፡

የእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ዋና ከተማ መርጡለማርያም የክርስትና መዲና ከመሆኗ በተጨማሪ ለቱሪዝም መስህብ የሚሆን የቅርስ ባለቤት ስትሆን በአጠቃለይ ወረዳዋም ለም መሬት እና ለግብርና ምቹ የሆነ ቦታ ያላት ወረዳ ናት፡፡ በጎጃም ምድር ለመጀመሪያ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን የታነፀባት ናት፡፡ የእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ዋና ከተማ መርጡለማርያም ይህን ስም ከማግኘቷ በፊት የተለያዩ ስያሜዎች ሲሰጧት ቆይቷል፡፡ ከክርስቶስ ልደት በፊት 2000 ዓ.ዓ የኩሽ ዘሮች በሰላም ያለምንም ችግር ይኖሩ ስለነበር ቦታዋን "ሀገረ ሰላም" በሚል ይጠሯት ነበር፡፡ ከዚህ በመቀጠል እግዚያብሔር በሕገ ልቡና ያመልኩ ስለነበር "ሀገረ እግዚአብሔር" ከዚህ በኋላ ንግሥት ሳባ ቀደማዊ ሚኒሊክ ወልዳ ከሰሎሞን ንግሥናውን ተቀብሎ መጥቶ ከተቀመጠበትና መናብር ጽዮን

ከሚባሉት አንዷ መርጡለማርያም ነበረች፡፡ በመሆኑም በዚህ ሰርዓተ ኦሪት ይደርስ ስለነበር በዚህም መላእክት በረድኤት ይገኙ ስለነበር እንዲሁም ቦታዋን "ጽርሐ አርዓም" በሚል ሰይመዋት ነበር፡፡

በ4ኛው ክፍለ ዘመን በፍቁራን አሀው አብርሃ ወአፅብሃ ነግሠው በነበረበት ጊዜ ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ በመጣ በ333 ዓ.ም በጎጃም የመጀመሪያው 12 መቅደስ ቤተ-ክርስቲያን በሊቀ ጳጳስ ካሰቴ ብርሃን አባሰላማ ተባርኮ ቅዳሴ ቤቱ ሲከበር ድንግልማርያም ለነገሥታቱ እና ለሊቀ ጳጳሱ ተግልፃ አዲሱ ቤተ መቅደስ ስትባርከው በማየታቸው ቦታዋን ፀርህ ያለውንመርጡል  አርያም የሚለው ደግም ማርያም በሚል "መርጡለማርያም" በማለት  ሰያሜዋን አግኝታለች (የእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ የባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት 2011 ዓ.ም የጽሑፍ መረጃ)፡፡

በእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ  ካሉት ቀበሌዎች ውስጥ ጥናቱ የተካሄደባቸውን ብቻ ስያሜያቸውን ስንመለከት የበርላይ ቀበሌ እና የደሞበዛ ቀበሌ የስም ስያሜን እንመለከታለን፡፡

በርላይ ቀበሌ ይህን ስም ከማግኘቷ በፊት ቆርሽ ብቻ የሚልስያሜ ነበራት፡፡ አካባቢው ለምለም ሳር የሚያበቅል በጋራና ተራራ የተሸፈነ ቀበሌ ነው፡፡ስለሆነም ማኅበረሰቡ ከብቶችን ለማሰማራት አመቺ ቦታዎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ምክንያቱም በጋራ የተከበበ ስለሆነ ከብቶች ሩቅ  ቦታ የመሄድ እድል የላቸውም፡፡ ይሁንና ከዕለታት አንድ ቀን ሌሊት ሌባ ይገባ እና ከብቶችን ይዞ ለማምለጥ ሲሞክር የአካባቢው ማኅበረሰብ በመጯጯህ  በየመውጫ ላይ በመሆን ሌባው እንዳይወጣ ተከታተሉ በማለት ጥሪ ያሰሙ እና መውጫው ላይ በጋራው መካከል ሌባውን ይይዙታል፡፡ ከዚህያም ሌባው በሩ ላይ ተያዘ በማለት ከዚያን ቀን ጀምሮ በርላይ የሚል ሰያሜ ተሰጣት ይላሉ(ቃለ መጠይቅ ጥር 2 /2011 ዓ.ም)፡፡

ጥናቱ ከሚጠናበት ቀበሌ ውስጥ የደምበዛ ቀበሌ ስያሜ ስናይ ደምበዛ በጥቅጥቅ ደን የተሞላች ጫካውን እንጂ መሬቱን ማየት ከባድ ነበር፡፡ ስለሆነም የተወሰኑ ሽፍታዎች በደም ምክንያት ከቤት ወጥተው ጫካ የሚገቡ ሰዎች የሚሸሸጉበት ቦታ ነው፡፡ ቤተሰቡ የተገደለበት ባለደሙን ለብዙ ቀን ጫካው ውስጥ በመግባት በመፈለግ ከገኘው ባለጋራውን ይገለዋል፡፡ በተደጋጋሚ ብዙ ሰው እየተገደለበት የሽፍቶች መደበቂያ ቦታ በመሆኑ "ሻለቃ" የሚባሉ ቦታውን ደምበዛ ብለው ስያሜ ሰጡት(ቃለ መጠይቅ ጥር 24/2011 ዓ.ም)፡፡

## 3.2 የእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ የመሬት አቀመማመጥ እና የአየር ንብረት

የእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ የቆዳስፋት 203641 ሄክታር ሲሆን የቦታ አቀማመጡ 57.8% ሜዳማ፣ 7% ተራራማ፣ 31% ወጣ ገባ እና 4.2 ሸለቋማ ነው፡፡ ወረዳው 33% ደጋ፣ 48% ወይና ደጋ እና 19% ቆላማ የአየር ንብረት ሲኖረው በአማካኝ ከ1050-1750 ሚ.ሜ  የሚደርስ አመታዊ ዝናብ ያገኛል፡፡ በወረዳው የሚገኙ ቀበሌዎች አብዛኛቹ ወይና ደጋ ናቸው፡፡ በወረዳው የአፈር ዋላካ ጥቁር አፈር 58% ቀይ አፈር 13% ቡናማ 29% መሆኑን የእነብሴ ሳር ምድር ወርዳ ስታቲክሳዊ  የፅኑፍ መረጃ ያመለክታል፡፡

የእነብሴ ወረዳ የተለያዩ የአዝርዕት አይነቶችን ያበቅላል፡፡ በቆላው አካባቢ በአብዛኛው የአገዳ እህሎች የሚበቅሉ ሲሆን  ማሽላ፣ ቦለቄ፣ በቆሎ እና ዘንጋዳ በብዛት ይመረትበታል፡፡ በወይና ደጋው በብዛት ብዕር እህሎች ጤፍ፣ ስንዴ፣ ገብሰ፣ ሽንብራና ጓያ ይመርትበታል፡፡  በደጋው የአበባ እህሎች አተር፣ ባቄላ፣ ድንች፣ ገብስ፣ ሰንዴን በማብቀል ተሰማሚ የአየር ንብረት አለው፡፡ የወረዳው አርሶ አደሮች የእንጀራና የወጥ እህሎችን ስለሚያመርቱ ከሌላ አካባቢ የመጡ  ሰዎችን ስለወረዳቸው ለምለምነት በቃል ግጥምአማካኝነት ይገልፃሉ፡፡

የእንጀራው መለስለስ የወጡ ማማር፣

አገር በሳየንሽ እነብሴ ወረዳ መርጡለማሪያም፡፡ በማለት ስለ አካባቢያቸው ለም መሬትና እህል አብቃይነት ይገልፃሉ፡፡

ሰንጠረዥ 1. የ2010ዓ.ም የህዝብ ብዛት በገጠርና በከተማ ጥቅል መረጃ

| ቀበሌ | ከተማ | | | ገጠር | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ |
| 01፣02፣03ና04 ቀበሌዎች | 12648 | 16113 | 28760 | | | |
| 34 ቀበሌዎች | | | | 65833 | 67538 | 133372 |
| ድምር | 12648 | 16113 | 28760 | 65833 | 67538 | 133372 |

የእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ህዝብ ብዛት በገጠር ወንድ 65,833 ሴት 67,538 ድምር 133,372 ሲሆን በከተማ ወንድ 12,648 ሴት 16,113 ድምር 28,760 ነው፡፡ በአጠቃላይ በወረዳው ያለው የህዝብ ብዛት ወንድ 76,481 ሴት 83,651 ድምር 162,132 ነው (የእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት 2011 ዓ.ም የፅሁፍ መረጃ)፡፡

የወረዳው ማኅበረሰብ በአብዛኛው በግብርና የሚተዳደር ነው፡፡ ወረዳው ከፍተኛ የእህል ምርት የሚመርትበት ከመሆኑ በተጨማሪ የቀንድ ከብትና የጋማ ከብት አለ፡፡ የወረዳው ማኅበረሰብ በግብርና፣ በአንጥረኝነት፣ በሽመና፣ በንግድ፣ በመንግስት ስራና በጉልበት ስራ ይተዳደራሉ፡፡

## 3.3 የእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ መሰረተ ልማት

የእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ የመሰረተ ልማት አውታሮች ስንመለከት በጤናው ዘርፍ 8 የመንግስት ጤና ጣቢያ፣ 8 የግል መካከለኛ ክሊኒክ እና 1 የመንግስት ሆስፒታል አለ፡፡ በትምህርት ዘርፍ የመንግስት 74 1ኛ ደረጃ ት/ቤት፣ 5 ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እና 1

መሰናዶ ት/ቤት ሲኖር 4 1ኛ ደረጃ ት/ቤት በግሉ ዘርፍ አለ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ 2 የመንግስት 4 የግል ኮሌጆች በወረዳው ውስጥ ይገኛል፡፡ በዚህ ውስጥ በመንግስት ስራ የሴቶች ተሳትፎ ከወንዶች ጋር ሲነፃፀር የተወሰነ ቁጥሩ ቢያንስም በትምህርት ቤቶች ውስጥ ገብተው የሚማሩት ሴቶች ከወንዶች በቁጥር ከፍተኛ ናቸው፡፡

የኢኮኖሚ ተቋማትን ስንመለከት በወረዳው ዋና ከተማ እና አራት የገጠር ቀበሌዎች የመብራት ተጠቃሚ ሲሆኑ ሌሎች አያገኙም፡፡ ተንቀሳቃሽ ስልክን በተመለከተ የተወሰኑት የማህበረሰብ ክፍሎች የስልክ ተጠቃሚ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከፍተኛ የሆነ የውሃ ሀብት ስላለ ንፁህ የመጠጥ ውሀ ችግር የለም፡፡ በእነብሴ ወረዳ ዋና አስባልት ተጠናቆ ከመካነሰላም ጋር የግብይት ስርአት ተጀምሯል፡፡

## 3.4 የእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ማኅበራዊ ሕይወት

የእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ማኅበረሰብ እምነታቸው ሁሉም የአርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታይ ናቸው፡፡ ማኅበራዊ ሕይታቸውን ለማጠናከር በእድር፣ በሰንበቴ፣ በፀበል፣ በማኅበር፣ በክርስትና፣ በሰርግ፣ በተዝካር፣ በለቅሶ፣ በጉርብትና፣ አብሮ በመብላትና በመጠጣት እንዲሁም የደቦ ሥራዎችን በመሥራት እምነታቸውን፣ አንድታቸውን እና ግንኙነታቸውን ያጠናክራሉ (ቃለ መጠይቅ፣ ጥላሁን አሰፋ የካቲት 2011)፡፡ የወረዳው ማኅበረሰብ ግንኙነታቸውን ከሚፈጥሩበትና ከሚያጠናክሩበት መንገድ አንዱ "ማኅበር" ነው፡፡

> አብዛኛው ማኅበረሰብ በአንድ ታቦት ስም ማኅበር በመግባት ይዘክራል፡፡ ማኅበር የሚባለው ለምሳሌ የገብርኤል፣ የሚካኤል፣ የማርያም ማኅበር በመመስረት ሃይማኖታቸውን በማጠናከር ሲወርድ ሲዋርድ የመጣውን ባህል ለሚቀጥለው ትውልድ ያስተላልፍሉ፡፡ ማኅበር ከሃይማኖታዊ ጥቅሙ በተጨማሪ የተቸገረን በገንዘብና በጉልበት በመረዳዳት ማኅበራዊ ሕይወታቸውን ለማጠናከር የሚጠቀመበት አንዱ መንገድ ነው(ጥላሁን አሰፋ፣ ቃለ መጠይቅ የካቲት 2011 ዓ.ም)፡፡

ማኅበራዊ ግንኙት የሚፈጠርበት ሌላኛው መንገድ ሀዘንና ደስታ ነው፡፡ የወረዳው ሴቶች የተለያዩ የማኅበራዊ ህይወት መስተጋብሮች አሏቸው፡፡ ለምሳሌ በደስታ ጊዜ በሰርግ፣ በቁም ተዝካር፣ በክብረበዓላት. . . ወዘተ በመሳሰሉት በሀሳብ፣ በጉልበት እና በገንዘብ ይረደዳሉ፡፡ በሰርግ ጊዜ ሽማግሌ ከሚላክበት ቀን ጀምሮ በጋራ በመሥራት እስከ ምላሽ (መልስ) ድረስ ጠላ በመጥመቅ፣ አረቂ በማውጣት፣ እንጀራ በመጋገርና ወጥ በመስራት የባለጉዳዮችን ደስታ በጋራ ይጋራሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የዕለቱ ቀን ሌማት በመያዝ ለሰርጉ የመጡትን ሰዎች ያበላሉ ያጠጣሉ፡፡በሀዘን ጊዜም ሴቶች ሀዘንተኖችን ከማፅናናት ባለፈ እንጀራና ጠላ በማምጣት አቅም የሌላቸው በጉልበታቸው በመስራት ማህበራዊ ህይወታቸውን ያጠናክራሉ፡፡ በአጠቃላይ ሴቶች አብዛኛውን ጊዜ ስራ የሚሰሩት በሀዘንም በደስታም በጋራ (በቡድን) ነው፡፡

መረጃ አቀባዩ ባህላችን እምነታችን እና ቋንቋችን አንድ መሆኑ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በጋራ በመሆን በሰላምና በፍቅር በመተጋገዝና በመተዛዘን ተቻችለን እየኖርን ነው በማለት ገልፀወልኛል (ወ/ሮ ጥጋቤ ታደሰ ፣ቃለ መጠይቅ የካቲት 2011 ዓ.ም)፡፡

# ምዕራፍ አራት

## ስለ ሴቶች የሚነገሩ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ይዘት ትንተና

አንድ ምሳሌያዊ ንግግር ከአንድ በላይ በሆነ ርዕስ ጉዳይ ስር ሊመደብ ስለሚችል ምሳሌያዊ ንግግሮቹ በይዘት መከፋፈል አስቸጋሪ ነው። በተደጋጋሚ እንደተገለፀው አንድ ምሳሌያዊ ንግግር የያዘውን መልዕክት ለመረዳት ምሳሌያዊ ንግግሩ የተነገረበትን ታሪካዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊ፣ መልክ ምድራዊ አካባቢን ማወቅና ከሁሉም በላይ ዓውዱን መረዳት ይጠይቃል። በመጠይቅና በቡድን ውይይት የተገኙ የምሳሌያዊ ንግግሮች የተላለፈውን መልዕክት ለመተንተን የተሞከረው ምሳሌያዊ ንግግሮቹ ሲነገሩ የሚሰጡት መልዕክት መሰረት በማድረግ ነው። መረጃ ሰጪዎቹ ከሰጧቸው ትርጉም በመነሳት ትንተና ለማድረግ ተሞክሯል። ነገር ግን ምሳሌያዊ ንግግሮች በተለያየ አውድ እየገቡ እንደየ አውዱ የተለያየ ትርጉም ሊሰጡ ስለሚችሉ ያላቸው ትርጉም እዚህ ላይ የተተነተነው ብቻ ነው ማለት አይደለም።

ስለሴቶች የተነገሩ ምሳሌያዊ አነጋገሮች በዋናነት በሁለት ዋና ዋና ጎራዎች የሚከፈሉ ሲሆን ይህም አዎንታዊና አሉታዊ መልዕክት የሚያስተላለፉ ናቸው። ይህ ክፍፍል እንደተጠበቀ ሆኖ ምሳሌያዊ አነጋገሮቹ የሴቶችን ቤተሰባዊ ዝምድና(እንደ ሚስት፣ እንደእናትና እንደ ልጅ) ያላቸው ሚና የሚገልፁ፣ የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ የሚጠቅሱ፣ ከማኅበራዊ ሕይወት አንፃር ያላቸው ሚና የሚያንፀርባቁ፣ከደግነትና ከክፋት፣ ከብልህነትና ከየዋህነት፣ ከፈሪነትና ከጀግንነት አንፃር የተነገሩ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ይዘት ምን እንደሚመስል ከዚህ በታች ባሉት ርዕሶች ስር ተተንትናዋል።

### 4.1 የሴቶችን ቤተሰባዊ ሁኔታ የሚገልፁ ምሳሌያዊ ንግግሮች

ማንኛውም ማኅበረሰብ የሴት የወንድ ስብሰብ መሆኑ ይታወቃል። በመሆኑም ሴቶች በቤተሰብ ውስጥ እናት፣ ልጅ፣ ሚስት፣ እህት፣ አክስት…መሆን ተፈጥሮ የሰጣቸው ፀጋ ነው። በምሳሌያዊ አነጋገሮች ውስጥም እነዚህ ዝምድናዎች በአውንታ ወይም በአሉታ ሲገለፁ ይስተዋላል።

## 4.1.1 እናትነትን የሚገልፁ ምሳሌያዊ ንግግሮች

እናት የሕይወት መሰረት ናት ማለት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ሁሉም ማኅበረሰብ እናትን ሲያከብሩ ይታያል፡፡ ስለዚህ አብዛኞቹ እናትነትን የሚገልፁ ምሳሌያዊ ንግግሮች በአዎንታ የተጠቀሱ ናቸው፡፡ ልጅን ከመንከባከብ አንፃር የተነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች፡-

- ልጅ ያለ እናት ቤት ያለጉልላት
- እናት የሌለው ልጅ ቀላል እንደ ጌሾ ሳይበላ በላ ነው ሳይናገር ዋሾ

የመጀመሪያው ምሳሌያዊ አነጋገር የእናት መኖር ለልጅ ምን ያህል አስፈላጊ መሆኗን መረዳት ይቻላል፡፡ ቤት ያለጉልላት ሊቆም አይችልም፤ በቀላል ንፋስ ወይም በአነስተኛ ዝናብ ሊፈርስ ይችላል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም እናት የሌለው ልጅም ለረሀብ፣ ለጥማትና ለእርዛት የተጋለጠ በመሆኑ ጤነኛ ሆኖ ሊያድግ አይችልም፤ በቀላሉ በበሽታ የሚጠቃና አቅም ያጣ ሆኖ ያድጋል፡፡

ሁለተኛው ምሳሌያዊ አነጋገርም ተመሳሳይ መልዕክት ያለው ነው፡፡ ለልጅ ማደግ የእናት መኖር ምን ያህል ወሳኝ እንደሆነ ይገልፃል፡፡ እናት ልጇ ቢበላ እንኳ የበላ ቢጠግብም የጠገበ አይመስላትም፡፡ ልጁ ተሳስቶ መጥፎ ነገር እንኳ ቢናገር እንዳልተናገረ ትሸሽግለታለች፡፡ ልጄ እንዲህ አወራ ብላ ለሌላ ሰው አትነግርም፤ ነገር ግን በሞግዚት ወይም በእንጀራ እናት የሚያድግ ልጅ ከሆነ እንዲበላ እንኳ አስቦ ምግብ የሚሰጠው አይኖርም፤ ሳይበላ እንደበላ ተደርጎ ይቆጠራል እንጂ እናትነት የዝምድናዎች ሁሉ የበላይ ነው፡፡ ከእርግዝና ጀምሮ ያለው ሂደት ብንመለከት እናት በሆዷ ተሸክማ፣ አምጣ በመውለድ ጡት በማጥባትና በርህራሄ በማሳደግ ወደር የማይገኝላት ነች፡፡ ለዚህም ይመስላል ሚከተሉት ምሳሌያዊ ንግግሮች ለእናት የሚነገሩት፡፡

- ከናት ወዲያ ዘመድ ከቃጫ ወዲያ ገመድ
- አዎን ያለች ምላስ እናት የሌላት አራስ

የተባለው እናት የዘመዶች ሁሉ ቁንጮ፣ የደግነትና የርህሩህነት ተምሳሌትና ተንከባካቢ በመሆኗነው እናት የሌላት አራስ ተንከባካቢ እንደሌላት የተገለፀው ባልና የባል ዘመዶች በሙሉ ተሰብሰበው አራሷን (ህፃኗን) ቢያርሱ እንኳ የናቷን ያህል እንደማይሆኑ ይገልፃል፡፡

በዚህ ዓለም ላይ ለሰው ልጅ ከእናት የበለጠ ምንም ነገር ማግኘት አይቻልም፡፡ በመሆኑም እናትን ማጣት ያህል የሚያንገበግብ ነገር ይኖራል ማለት አደጋች ነው፡፡ ለዚህም ነው ማኅበረሰቡ የተለያዩ ምሳሌያዊ ንግግሮችን የሚናገሩት፡፡

- የእናት ሞትና የእግር እሳት እያደር ያንገበግባል
- የእናት ሞትና የድንጋይ መቀመጫ እያደር ይቆረቁራል

በማለት የሚናገረው እግር በእሳት ቢቃጠል ቁስሉ እያደር ያመርቅዛል፣ ህመሙ እየተባበሰ ይሄዳል፡፡ መጀመሪያ ላይ ቀላል ይመስል የነበረው ህመምና ቁስል እያደር እጅግ አንገብጋቢ ይሆናል፡፡ በተመሳሳይ የአናት ሞትም ሀዘኑ ይበረታል፤ የድንጋይ መቀመጫም መጀመሪያ ሲቀመጡበት የሚመች ይመስላል ጥቂት ከተቀመጡበት ግን መቆርቆር ይጀምራል፡፡ ለዚህም ነው የድንጋይ መቀመጫና የእናት ሞት የተነፃፀረው፡፡ በቃለ መጠይቅና በፅሁፍ መጠይቅ የተሳተፉ መረጃ አቀባዮች ስለ እናት የሚያውቋቸው ምሳሌያዊ አነጋገሮች እንዲናገሩና እንዲፅፉ በተጠየቁ ጊዜ ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ

- እንኳን እናቴ ሞታ ወትሮም አልቅስ አልቅስ ይለኛል

የሚል ምሳሌያዊ አነጋገር አክለዋል፤ ይህም የእናት ሀዘን ምን ያህል ከባድ እንደሆነ ከማሳየቱም በተጨማሪ ከሀዘኖች ሁሉ ከባዱ የእናት መሞት እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ በተለይ ሌላ የሚያሳዝን ነገር የደረሰበት ሰው የእናቱ ሞት ሲጨመርበት በህመም ላይ ህመም በሀዘን ላይ ሀዘን ይጨምርበታል የሚል ነው፡፡

እነኝህ ከላይ ያየናቸው ምሳሌያዊ አነጋገሮች በሙሉ ስለእናት በአዎንታ የተገለፁ ናቸው፡፡ ከዚህ በፊት እንደተገለፀው እናትነት የደግነትና የርህራሄ ተምሳሌት በመሆኗ በአዎንታ የሚገለፁ እጅግ በጣም ብዛት ያላቸው ናቸው፡፡ ለዚህ ጥናት ከላይ የተጠቀሱት

ተዘረዘሩ እንጂ ስለ እናት የተነገሩ ምሳሌያዊ አነጋገሮች እነኝህ ብቻ ናቸው ማለት አይደለም ( የቡድን ውይይት የካቲት 12/2011ዓ.ም)፡፡

ስለ እናት በአሉታ የተጠቀሱ ምሳሌያዊ አነጋገሮች እጅግ በጣም ጥቂት በመሆናቸው ለማግኘት በጣም አስቻጋሪ ነው፡፡ በዚህ ጥናት በጽሑፍ፣ በቃል መጠይቅ እንዲሁም በቡድን ወይይት የተካፈሉ መረጃ ሰጪዎች ስለእናት በአሉታ የተነገሩ ምሳሌያዊ አነጋገሮች እንዲያስታውሱ ተደርጎ ነገር ግን ተሳታፊዎቹ ማግኘት አልቻሉም፡፡

- የደመና ውሀ ጥምና የእናት በደል አይታወቅም
- የእናትን ክፋት፣ የደመናን ውሃ ጥማት ባለቤቱ ያውቀዋል፡፡

እናት ሰብአዊ ፍጡር እንደመሆኗ መጠን ፍፁም ልትሆን አትችልም፡፡ ምንም እንኳ አብዛኞቹ እናቶች ልጆቻቸው ላይ ክፋት መፈፀም ይቅርና የሚያስቡት ባይሆኑም እንኳ ጥቂቶች ግን ይጠፋሉ ተብሎ አይታሰብም፡፡ ልጇን ብትበድል እንኳ ሌላ ሰው ልጇን ትበድላለች ብሎ ስለማያስብ ከተበዳዩ በስተቀር የሚያውቀው የለም ማለት ነው፡፡ ዳመና ሲሆን ላብ ከሰውነት ስለማይወጣ የውኃይጠማል ተብሎ አይታሰብም ፡፡ በመሆኑም ዳመና ወይም ዝናባማ በሆነ ቀንውኃ ጠማኝ ያለሰው ውሸት እንደተናገር ሊወሰድ ይችላል፡፡ ጥማቱ ከባለቤቱ በስተቀር የሚያውቀው የለምና እናትም ሆን ብላ ልጇን አትበድልም እንጂ ተሳስታ እንኳ በልጇ ላይ በደል ብታደርስበት ሌላ ሰው ይህንን ሁኔታ ለማመን ይቸገራል፡፡

## 4.1.2 ስለ ሚስት የተነገሩ ምሳሌያዊ አነጋገሮች

ትዳር በወንድና በሴት መካከል የሚመሰረት የሕይወት ቁርኝት ነው፡፡ በእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ማህበረሰብ ምንም አይነት ዝምድና የሌላቸው ሰዎች በጋብቻ አማካኝነት ተሳሰረው አንድ አካል አንድ አምሳል በመሆን ትስስር ይፈጥራሉ፡፡ በትዳር ሕይወት ውስጥ የባልና ሚስት ሥራ ሐላፊነት የተለያየና ዘርፈ ብዙ ነው፡፡ በአብዛኛው ማኅበረሰብ ዘንድ ልጅ ወልዶ ተንከባክቦ ማሳደግ፣ የተለያዩ የቤት ሥራዎችን ማከናወን፣ ቤት የጎደለውን ለመሙላት መጣጣርና ባልን ማገዝ የሴቷ ድርሻ ነው፡፡ ማኅበረሰቡም

ይህንን ሚናዋን በአዎንታና በአሉታ የሚነገሩ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ሲጠቀም ይታያል። በአዎንታ የተገለፁትን በቅድሚያ እንመልከት፡-

- የሚስት አሳቢ የጥንድ በሬ ሳቢ ይሰጥህ
- መልካም ሚስት ለባሏ ዘውድናት

የአንድ ገበሬ እርሻ የተሳካ ሊሆን የሚችለው ሁለቱ በሬዎች ተቀናጅተው ተግባሩን/ እርሻውን በቅልጥፈና ሲከውኑት ነው። በሬዎቹ ቀና ካልሆኑና የሚለግሙ ከሆነ እርሻው በተገቢው ሁኔታ ሊታረስ አይችልም (ቃለ መጠይቅ ወ/ሮ ጥጋቤ ታደሰ የካቲት 9/2011ዓ.ም)።

ባልም ለብቻው ቢለፋ፣ ቢወጣና ቢወርድ የሚስቱ እገዛ ካልተጨመረበት በስተቀር ቤቱ ሊቃና አይችልም። ለዚህም ነው የሚስት አሳቢ የጥንድ በሬ ሳቢ ይሰጥህ እየተባለ የሚነገረው። ስለዚህ ያላገባ ወንድ ወይም ለማግባት በዝግጅት ላይ ያለ ወንድ አባቶች ሲመርቁት የሚስት አሳቢ ይስጥህ የሚሉት ለዚህ ነው። የተጣለባትን ሐላፊነት በሙሉ የምትወጣ ሴት ለበሏ ኩራት ናት። ልጆች ወልዳ በአግባቡ የምታሳድግ፣ባሏን የምትንከባከብ፣ ቤቷን የምትጠብቅና በአጠቃላይ ለኑሮዋ መቃናት ጎንበስ ቀና የምትል ሴት የባሏ ዘውድ ናት፤ መመኪያ ናት።

እንደሚታወቀው ዘውድ ነገሥታት አሠርተው በራሳቸው ላይ የሚደፉት የክብር መገለጫ ነው፤ወይንም ለንጉሱ የተለየ ግርማ ሞገስ ያላብሰዋል።ቤቷንና ንብረቷን የምትንከባከብ ሴትም ለባሏ ልዩ ኩራትና ጌጥ ትሆናለች ማለት ነው። ቤት ውስጥ የሚስት መኖር አስፈላጊነት የሚገልፁ ምሳሌዊ አነጋገሮችም ይገኛሉ።

- ያለሴት ቤት ያለበሬ መሬት
- እንጀራ ያለወጥ፣ ቤት ያለሴት ክብት ያለበረት

እነኝህ ከላይ የተጠቀሱት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ሚስት ለአንድ አባወራ ምን ያህል አስፈላጊ መሆኗን የሚገልፁ ናቸው። የመጀመሪያው ምሳሌያዊ አነጋገር ስንመለከት አንድ ገበሬ መሬት ቢኖረውም የሚያርስበት በሬዎች ከሌሉት ውጤታማ ሊሆን አይችልም ። በገጠሩ የኢትጵያ ክፍል በተለይም ይህ ጥናት የተካሄደበት እነብሴር

ምድር ወረዳ በሬ በዋነኘነት የሚያገለግል የእርሻ መሳሪያ ነው፡፡ በመሆኑም ሀብትና ውጤታማነት የሚለካው ባሉት በሬዎች ብዛት ነው፡፡አንድ አርሶ አደር ብዙ ሄክታር መሬት ቢኖረውም የእርሻ በሬዎች ከሌሉት እንደድሀ ይቆጠራል፡፡ በተመሳሳይ ሴት የሌለችበት ቤት ብዙ ወንዶች እንኳ ቢኖሩበት ሊደምቅ አይችልም ወንድና ሴት ያሉበት ይደምቃል የሚል አንድምታ አለው፡፡

በተመሳሳይ እንጀራ ቀርቦ ወጥ ከሌለው የተሟላ ምግብ ሊሆን አይችልም፡፡ ለምለም እንጀራ ለመብላት ቢሞከር እንኳ ከጉሮሮ ለማውረድ ይከብዳል፡፡ እንጀራው የሚርስበት ወጥ የግድ ነውና እንዲዚሁም ከብቶች ቢኖሩም በረት ካልተዘጋጀላቸው ዋጋ የለውም፡፡ በረት የከብት ማደሪያ ነውና ማደሪያ የሌለው ከብት በጅብ መበላቱ አይቀርም፡፡ ሴት የሌለችበት ቤትም እንዲሁ ትርጉም አልባ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ለዚህም ይመስላል ሙያ እንኳ ባይኖራት ቤት ባዶ ከሚሆን ሙያ አልባ ሴት ብትኖር ይሻላል ለማለት ከወና ቤት ወና ሚስት የተባለው "ወና" ቤት ማለት ምንም አይነት ነገር የሌለበት ባዶ ቤት ሲሆን ወና ሚስት ማለት ደግሞ ምንም አይነት ሙያ የሌላት ሴት ማለት ነው፡፡

- ጠመንጃ ያለጥይት ዱላ፣ ወንድ ያለሴት ነሁላላ
- ከወና ቤት፣ ወና ሚስት
- ስንዴ ራቱ፣ ወይራ እሳቱ፣ ማለፊያ ሚስቱ፣ ለምን ሰርግ ይሄዳል ሰርግ አለ እቤቱ (በመጠይቅ መጋቢት4/2011ዓ.ም)፡፡

ጠላትን ለመከላከል የሚያገለግለው ጠመንጃ ተግባር ላይ የሚውለው ጥይት ሲኖርበት ነው፡፡ አለበለዚያ ተግባሩ ከምርኩዝነት (ከዱላ ወይም ከሽመል) የተለየ አይሆንም፡፡ ሴት ብልህ፣ረዳትና አጋዥ ስለሆነች ሚስት የሌለው ወንድም  እዚህ ግባ የማይባል ነሁላላ ተደርጎ በማኅበረሰቡ ይቆጠራል፡፡ ይህም ለምስክርነት የማይፈለግ ለአደራ የማይበቃ ሞኝና ጅላጅል አይነት ሰው ማለት ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር ጥሩ ሚስት ያው ወንድ ቤቱ ሁሌም ደስታ ሁሌም ሰርግ በመሆኑ ደስታ ፍለጋ ወደ ሌላ ቦታ እንደማይሄድ ለማመልከት ነው፡፡ አሳቢ የሆነች ሚስት ሁሌም ባሏ የሚደሰትበት ተግባሮችን ስለምታከናውን ደስታ ፍለጋ ሌላ ቦታ የሚሄድበት ምክንያት የለም የሚል መልዕክት አለው፡፡ ስለሚስት በአዎንታ የተነገሩ ምሳሌያዊ አነጋገሮች የመኖራቸውን ያህል

በአሉታም የተነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች እጅግ በርካታ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ በዚህ ጥናት የተሳተፉ መረጃ ሰጪዎችም በአብዛኛው ማስታወስ የቻሉት ስለሚስት በአሉታ የተነገሩ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን ነው፡፡ ለአብነት ያህል፡-

• ሚስቱ ክፉ፣ ባቄላ እራቱ፣ ብሳና እንጨቱ ሀዘን ነው ቤቱ

ይህ ምሳሌያዊ ንግግር ክፉ ሚስት ስለገጠመችው ወንድ የሚነገር ነው፡፡ ባቄላ በገጠሩ አካባቢ ተፈላጊነት የሌለው የድሃ ምግብ ምሳሌ ነው፡፡ ነገር ግን ጭቅጭቅ ባለበት ቤት ውስጥ ፍቅር ስለማይኖር ብትፈልግ ብላ ባትፈልግ ተወው የሚል አይነት ትርጉም ባለው ሁኔታ ባቄላ ለባሏ ታቀርብታለች፡፡ በቡድን ወይይት ወቅት አቶ ቦጋለ ታፈሰ በአካባቢ እንዲህ የሚባል አባባል አለ ብለው ተከታዩን ምሳሌያዊ ንግግር ነግረውኛል፡፡

"ደረቅ እንጀራ በርበሬ ነስንሳ፣ ብትበላ ብላ ባትበላ ላንሳ"፡፡

ይህ ምሳሌያዊ ንግግር የሚያስረዳን ክፉ ሚስት ወጥ ከመሥራት ይልቅ ከባሏ ጋር የምትጨቃጨቅበት ነገር ስታሰብ ስለምትውል ባሏ ሲመጣ ደረቅ እንጀራ በሚጥሚጣ ነሰንሳ ትሰጠዋለች፡፡ ለዚያውም ምንም ትህትና በሌላትሁኔታ "ከበላህ ብላ ባትበላ ላንሳ" እያለች ለነገር እንደምትጋብዘው ገልፀውልኛል፡፡ በእርሻ ቦታ ሲደክም ለዋለ አባወራ ይህ ድርጊትና ንግግር ምን ያህል ሊያናድድ  እንደሚችል መገመት አያደግትም፡፡ ይህም ከመጀመሪያው ምሳሌያዊ አነጋገር ጋር ተቀራራቢ ትርጉም ያለው ነው፡፡ እንዲህ አይነት ሚስት ያጋጠማቸው አባወራዎች ቤታቸው ውስጥ ጭቅጭቅ ስለሚሰፍን በሰላምና በደስታ አይኖሩም ፤ ለዚህም ነው ብሳና እንጨቱ ሀዘን ነውም ቤቱ የተባለው (ቃለ መጠይቅ ያምራል ተፈራ መጋቢት 8/2011)፡፡

• ወዳጅህን ጥራ ውሻዬን፣ ጠላትህን ጥራ ሚስቴን

ይህ ምሳሌያዊ ንግግር በሚስቱ የተማረረው አባወራ የተናገረው ነው ብለው የአካባቢው ሽማግሌው ነግረውኛል፡፡ እንደሚታወቀው ውሻ የታማኝነት ተምሳሌት ተደርጎ የሚወሰድ እንስሳ ነው፡፡ወዳጅን ምንም ቢሆንም አይረሳም፡፡ ይሁንና ከባልና ከሚስት የቀረበ ወዳጅም ሆነ ዘመድ እንደሌለ ይታወቃል፡፡ ስለዚህ ይህ ሰው ውሻውን ወዳጅ አድርጎ ሚስቱን በጠላትነት መፈረጁ ምን ያህል በሚስቱ አመል እንደተናደደ

ከመግለፁም በላይ ሚስቱን ከውሻ ጋር ማነፃፀሩና የውሻ ያህል እንኳ ክብር አለመስጠቱን ደግሞ ለሴቶች ያለው አመለካከት የሚያሳይ ነው፡፡

ከዚህም ባሻገር ሴቶች ለብቻቸው መኖር የማይችሉ ፍጡሮች ወይም እራሳቸውን የማይችሉ ደካሞች ተደርገው እንዲቆጠሩ የሚያደርጉ ምሳሌያዊ አነጋገሮች እጅግ በርካታ ናቸው፡፡ በተለይ ሴት ባል ካላገባች ምንም አይነት ክብር የሌላት ትንሽ፤ እድሜዋ ካለፈ ደግሞ “ቆሞቀር” እየተባለች የማኅበረሰቡ መጠቋቆሚያ እንደምትሆን ይገልፃሉ፡፡ ለአብነት ጥቂቶቹ እንመልከት፡-

- ባል የሌላት ሴት፣ የመንገድ ዳር እሸት
- ያለባል ሴት ወይዘሮ፣ ያለማንገቻ ከበሮ

የመጀመሪያው ምሳሌያዊ አነጋገር ስንመለከት መንገድ ዳር የበቀለ እሸት ወጭ ወራጁ አላፊ አግዳሚው ይቀምሰዋል፡፡ ምናልባትም ባለቤቱ ሳያውቀው ሊያልቅ ይችላል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም ባል የሌላት ሴት ሁሉም ይከጅላታል፤ አትከበርም ታማኝም አይደለችም የሚል ትርጉም አለው፡፡

ባል ለሚስት አስፈላጊ መሆኑ ቢታወቅም ሚስትም ለበሏ እጅግ ወሳኝ ናት፡፡ ነገር ግን ማኀበረሰቡ ባል የሌላት ሴት በሚያይበት መነፅር ሚስት የሌለው ወንድን አይመለከትም፡፡ ሴት ሳታገባ ጥቂት ከቆየች ቆሞቀር የሚል ቅፅል ስም ሲሰጣት ወንድ እድሜ ልኩን ሳያገባ እንኳ ቢኖር ይህ መጠሪያ አይሰጠውም፡፡ ለዚህም ነው ያለባል ሴት ወይዘሮ ያለማንገቻ ከበሮ በማለት የተገለፀው፡፡ ከበሮ ያለማንገቻ ወይም ያለመያዣ ሙሉ አገልግሎት ሊሰጥ እንደማይችል ሁሉ ሴትም ባል ሳይኖት የተከበች ወይዘሮ ልትሆን አትችልም የሚል አንድምታ አለው፡፡

በገጠሩ የሀገራችን ክፍል በተለይም ይህ ጥናት በተሰራበት የእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ በሚሠሩ ቤቶች ውስጥ ለመኝታ እና ለዕቃ ማስቀመጫነት የሚያገለግል ቆጥ ነው፡፡ ነገር ግን በዚህ ምሳሌያዊ አነጋገር ሴት ምንም አይነት ችሎታ እንደሌላት ለመግለፅ ቆጥ እንኳ መሥራት የማትችል ተደርጋ ተገልፃለች፡፡ ሳይሠራ እንጀራ እንደማይበላ ሁሉ ባል ከሌለ ቆጥ እንኳ አይሠራም የሚል መልእክት አለው፡፡

ከዚህም ባለፈ ሴቶች ለወሬ ብቻ የተፈጠሩ ምንም የማይሠሩ ተደርገው ይቀርባሉ በምሳሌያዊ አነጋገሮች፡፡

- ማውራት ነው ሴትነት፤ መስራት ነው ወንድነት

ይህ ምሳሌያዊ ንግግር የሴቶች ሚና ማውራት ብቻ አድርጎ የሚያሳይ ነው፡፡ ወንዶች ለሥራ የተፈጠሩ መሆናቸው ሲገልፁ ሴቶች ግን ለማውራት ብቻ የተፈጠሩ ናቸው የሚል መልዕክት አለው፡፡ የሚያወሩትም ነገር ምንም እርባና የሌለው እንደሆነ ደግሞ በሌላ ምሳሌያዊ አነጋገር ተጠቅሷል፡፡

- ወንዶች ምን ያወራሉ የሚመጣውን፣ ሴቶች ምን ያወራሉ ያለፈውን

በማለት ሴቶች ቢያወሩ እንኳ ያለፈውን ትርኪ ምርኪ ከመዘባረቅ ውጪ ምንም ቁምነገር ያለው ነገር አይናገሩም የሚል ነው፡፡ ስላለፈ ነገር ብቻ ሲያወሩ በተቃራኒው ግን ወንዶች ስለሚመጣው ነገር እየተወያዩ እንደሚያቅዱና ንግግራቸው ለኑሮአቸው ጠቃሚ መልዕክት የያዘ መሆኑን ይጠቁማል፡፡

ባልና ሚስት ተዋደውና ተከባብረው አንተትብስ አንቺ ትብሽ ተባብለው በመኖር የትዳር ሕይወታቸው መግፋት እንዳለባቸው ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ ማኅበረሰቡ የወንድ የበላይነት በማጉላት ወንዶች ሚስቶቻቸውን የመደብደብና በጉልበት የማስተዳደር መብት ባህሉ ሰጥቷቸዋል፡፡ ይህን የሚያንፀርባቁ የተለያዩ ምሳሌያዊ አነጋገሮች አሉ፡፡

- ሴትና አህያ ዱላ ይወዳሉ

የሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር ሴት ምንም አይነት በደል ቢደርስባት ትቋቋማለች ወይም ትችላለች የሚል መልዕክት አለው፡፡ ከዚህም ባሻገር የሚከተለው ምሳሌያዊ ንግግርም ይህንኑ የሚያጠናክሩ አሉ፡፡

ሴትን ከአህያ ጋር በማነፃፀር መታረም የሚችሉት በማስተማር በመምከር ወይም በመግሰፅ ሳይሆን በዱላ በመደብደብ እንደሆነ ያመለክታሉ፡፡ዱላ አይደለም ለሰው ልጅ ለሌላ ፍጡር የማይሆን ቢሆንም እንኳ በቡድን ውይይት ወቅት መረጃ አቀባዮቼ እንደነገሩኝ ከሆነ አንድ ባል ሚስቱን መውደዱን ለማረጋገጥ ሚስቱ ስታጠፋ መደብደብ

አለበት፡፡ ሚስትም እንደሚወዳት ለማረጋገጥ የማይፈልገውን የምግብ አይነት በመሥራት ስታቀርብለት ዝም የሚል ከሆነ አይወዳትም፡፡ ነገር ግን ለምን ይህን ሠራሽ ብሎ ከደበደባት ግን ስለሚወዳት እንድትስተካከል ስለሚፈልግ ነው በማለት ገልፀውልኛል፡፡ ስለሆነም በቡድን ውይይቱ መረጃ አቀባዮቹ በሰጡኝ መረጃ መሰረት ሴቶችም የሚደግፉት ሀሳብ እንደሆነ መገመት አያዳግትም፡፡

- በሽንጎ ቢረታ ከቤት ሚስቱን መታ

ይህ ምሳሌያዊ ንግግር የወንዱን ድክመት የሚገልፅ ቢሆንም እንኳ ሴት የንዴት ማብረጃ እንደሆነችና በሽንጎ ውሎ የተረታ አባወራ የንዴቱ ማብረጃ ሚስቱን በመደብደብ እንደሆን ይገልፃል፡፡ በመሆኑም ማኅበረሰቡ ባሎች ሚስቶቻቸውን ቢደበድቡ ሀጢአት አድርጎ እንደማይመለከትና ሚስቶች ሲመቱ ብሶታቸውን የሚያዳምጥ ማኅበረሰብ አለመኖሩን ይገልጣሉ፡፡ሴቶች ይህንኑ አሜን ብለው በመቀበል ለዘመናት ሲደበደቡና ሲበደሉ በደላቸው አምቀው ኖረዋል እየኖሩም ነው፡፡

## 4.1.3 ስለ ሴት ሕፃናት የሚነገሩ ምሳሌያዊ አነጋገሮች

በእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ማኅበረሰቦች ዘንድ ወንድ ልጅ የአባት ወራሽ፣ የቤተሰብ መመኪያና ረዳት፤ ምናልባት አባት ቢሞት እንኳ የቤተሰብ አስተዳዳሪ ነው ተብሎ ስለሚታመን ወንድ ልጅ ሲወለድ የማይደሰት ሰው አይኖርም ማለት ይቻላል፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን የቤተሰቡን የዘር ግንድ ሊቀጥል የሚችለው በወንድ ልጅ በኩል ነው የሚል አስተሳሰብ በማኅበረሰባችን ዘንድ በስፋት ይታመናል፡፡ ስለዚህ አንድ አባወራ ሴት ልጆችን ብቻ የወለደ እንደሆነ በብዙ ሰዎች ዘንድ እንደ መሀን ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ ዘሩን ማስቀጠል አልቻለም በሚል እሳቤ፡፡ ስለዚህ ሴት ልጅ ስትወለድ ወንድ ሲወለድ እንደሚታየው ደስታው ፍጹም አይደለም፡፡ ነገር ግን ሴት ልጅ የቤተሰቧ በተለይም የእናቷ ረዳት ታናናሽ ወንድምና እህቶች ካሏት ተንከባካቢ በመሆኗ ጥቂቶች ሴት ልጅ መውለድን ይመኛሉ፡፡ ነገር ግን እነዚህ ሰዎች ከማኅበረሰቡ ብዛት አንፃር ቁጥራቸው እዚህ ግባ የሚባሉ አይደሉም፡፡

ቀጥለን ይህንን የማኅበረሰቡን አመለካከት የሚያንፀባርቁ ሴት ልጅን በተመለከተ በአዎንታ የተነገሩ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን እንመልከት ፡-

- የታደለች ሴት በፊት ትወልዳለች ሴት
- በሴት የበከረ ከእግዜር የተማከረ
- ሴት የሌለበት ወንድ አይበቅልበት

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ሴት ልጅ በቅድሚያ ከተወለደች የእናቷ ደጋፊ ትሆናለች፤ በቤት ውስጥ የሚሰሩ ሥራዎች በሙሉ ጥንቅቅ አድርጋ ትሠራለች፤ በቤቱ ውስጥ በአጋጣሚ ወንዶች ከሌሉም እንደእረኝነት የመሳሰሉ የወንዶችምን ተግባር ታከናውናለች። ስለዚህ ሴት ልጅ የወንድም የሴትም ሥራ መስራት ትችላለች ማለት ነው። ነገር ግን ወንዶች ካለው የማኅበረሰቡ አስተሳሰብና አኗኗር አንፃር የሴቶችን ያህል ሥራ አይሠሩም በማለት የታደለች ሴት በፊት ትወልዳች ሴት ተብሎ የሚነገረው።

ከዚህ በተጨማሪ የበኩር ልጅ ሴት ከሆነች በማህበረሰቡ ሀብት እና በተከት ይዛ ትመጣለች ብለው ስለሚያስቡ የምታሰገኘው ጥቅም ብዙ በመሆኑ በሴት የበከረ ከእግዜር የተማከረ በማለት የሚነገረው (የቡድን ውይይት ጥር 29/2011ዓ.ም)።

የመጨረሻው ምሳሌያዊ አነጋገርም ለወንዶች መገኘት ዋና ምክንያቶቹ ሴቶች መሆናቸው በግልፅ ያሳያል። ለዚህ ነው ሴት የሌለበት ወንድ አይበቅልበት በማለት እነኝህ ከላይ የተጠቀሱ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ሴት ልጅን በአዎንታ የሚገልፁ ሲሆንማኅበረሰቡ የሴትን ልጅነት አስመልክቶ በአሉታ የገለፃቸው ደግሞ ቀጥለን እንመለከታለን።

- ሴት የወለደ መቀመቅ ወረደ
- ሴት አግብተው ሴት ከወልዱ የት አለ ንግዱ

እዚህ ላይ የተዘረዘሩት ምሳሌያዊ ንግግሮች ሴት መውለድ አዘቅት ከመውረድ ጋር ተነፃፅሯል። ይህ እሳቤ የሚመነጨው ሴት ልጅ ምንም አይነት ማኅበራዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የላትም የሚል የተሳሳተ ግንዛቤ ያዘለ ነው ። ምንም እንኳ የምሳሌያዊ አነጋገሩ ምንጭ የሆነውማኅበረሰብ ከምን ተነስቶ ይህን ሊል እንደቻለ

ዓውዳዊ ክዋኔው ታይቶ ምስጢሩን ለመረዳት ባይቻልም ሴት ልጅ እንደወንድ ልጅ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አታስገኝም፤ ለአባቷም ከለላና መከታ አትሆንም ከሚል የማኅበረሰቡ እሳቤ አንፃር የተነገር እንደሆነ መረዳት ግን አይከብድም። ለዚህ ይመስላል “ሴት አግብተው ሴት ቢወልዱ የት አለ ንግዱ” እየተባለ የሚነገረው። ከዚህም ባሻገር ሴት ልጅ ጠባቂ ከለላ ያስፈልጋታል፤ ካልሆነ ግን የትም ወስልታ፤ ሌላ ጣጣ ታመጣለች ብሎ ማኅበረሰቡ ስለሚያምን፡-

- ሴት የወለደ፤ ጉድ ወለደ
- ሴት የወለደ፤ ተዋረደ
- ሴት የወለደ፤ አመድ የነገደ ብሎ ሲናገር ይሰማል።

በእነብሴ ወረዳ ሴት ልጅ ለአቅመ ሂዋን ከደረሰች በኃላ አግብታ ከቤተሰቦቿ እርቃ ስለምትሄድ ምንም ጥቅም አይኖራትም። ወንድ ልጅ ግን ከቤተሰቦቹ አካባቢ ስለሚሆን የቤሰቦቹ ረዳት ይሆናል፤ ለሲህም ነው ሴት መውለድ ትቅም እንደሌለው የሚገለጸው። ከዚህ በተጨማሪ አንድ ሴት ጨዋና ጠንቃቃ ካልሆነች አርግዛ ድቃላ ተሸክማ ይዛ ልትመጣ ትችላለች። ለዚህም ነው ሴት የወለደ ተዋረደ የተባለው። በተጨማሪም ወንድ መውለድ እጅግ የሚያስከብር ተደርጎ ስለሚታሰብ ወንድ የወለደ ሴተሰብ ደስታው ወደር የለውም። በአንፃሩ ግን ሴት የወለደ ቤተሰብ ለሰው እንኳ ለመንገር የሚያፈርበት ሁኔታ ይሰተዋላል። ለዚህም ነው የሚከተለው ምሳሌያዊ ንግግር የሚነገረው።

- ወንድ የወለደ እንደ እግዜር የከበደ

በማለት ወንድ ያገኘ ቤተሰብ ከታላቁ ፈጣሪ ጋር ሲያነፃፅር ሴት ለወለደ ቤተሰብ ምን ያህል እንደሚያሳቅቅ መገንዘብ አያደግትም።

በአጠቃላይ ወንድም ሆነ ሴት የቤት ጌጦች ቢሆኑም ማኅበረሰቡ ሴቷን ማፈሪያ ተደርገው ከጥንት እስከዛሬ ድረስ በሚነገሩ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ሳይቀር የሴቶች የበታችነት ሲያንፀባርቁ ቆይተዋል። ሴትና ወንድ የራሳቸው የሆነ ፆታ ቢኖራቸውም ቅሉ ሁለቱም ለቤተሰባዊ ሕይወት መቃናት የሚከፍሉት ዋጋ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ወንድ ያለሴት ሴትም ያለወንድ ሙሉ ሊሆኑ አይችሉምና።

## 4.2 ሴቶች ከኢኮኖሚ አንፃር ያላቸውን ሚና የሚገልፁ ምሳሌያዊ አነጋገሮች

ሴቶች የማኅበረሰቡ ግማሽ አካል መሆናቸው ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ማንኛውም አይነት ልማትም ሆነ የኢኮኖሚ ግንባታ ያለሴቶች ተሳትፎ የሚታሰብ አይሆንም ሴቶች በተለይ ለቤተሰባዊ ሕይወት የሚያበረክቱት ሚና የጎላ ነው፡፡ ነገር ግን ማኅበረሰቡ ይህን የሴቶች ሚና በግልፅ የተረዳው አይመስልም፡፡ ምክንያቱም በሚጠቀማቸው ምሳሌያዊ አነጋገሮች ሴቶች በአብዛኛው የወንድ ጥገኛና ለቤተሰብም ሆነ ለማኅበረሰቡ በኢኮኖሚ በኩል ምንም ፋይዳ እንደሌላቸው ተደርገው ተገልፀዋል፡፡

በዚህ ስር የተጠቀሱ ምሳሌያዊ አነጋገሮች በአብዛኛው አሉታዊ ናቸው፡፡

- ከሴት ሆዳም የአንድ አመት በረዶ ይሻላል

በረዶ ባቁላን፣ስንዴ አተርን በአጠቃላይ የደጋ ሰብል ከመታ ድምጥማጡን የማጥፋት ሀይል አለው፡፡ ምሳሌያዊ አነጋገሩ የሴት ሆዳም አንድ ግዜ ከዘነበው በረዶ ጋር በማነፃፀር ሴት ብዙ ከበላች  አውድማ  ማሳ ከሚያጠፍው በረዶ የበለጠ እህል ታጠፋለች በማለት የኢኮኖሚ ውድመት እንደምታስከትል በምሳሌዊ ንግግሮች አማካኝነት ይነገራል፡፡ ሴቶች ቤት ውስጥ ሆነው የሚሰሩት ስራ ማለትም ልጅ ማሳደጉ፣ ቤትን በንፅህና መያዙ፣ምግብ መሰራቱ ወዘተ ማህበረሰቡ አሳንሶ እንደሚያየው ያስገነዝበነው፡፡

- ሴትና ፈረስ የሰጡትን ይቀምስ

ፈረስ የቤት እንስሳ ሲሆን ለጭነትና ለመጓጓዣነት የሚያገለግል የጋማ ከብት ነው፡፡ ከአካሉ ግዝፈትና ከሚሰራው የስራ ክብደት አኳያ ብዙ የመመገብና ያገኘውን የመብላት ልማድ አለው፡፡ በዚህ ምሳሌያዊ አነጋገር ላይ ሴት ከጋማ ከብት ጋር መነፃፀሯ  ብዙ እንደምትመገብና እንደማትመርጥ ሲያሳይ “የሰጡትን ይቀምስ” የሚለው አበባል ደግሞ ሴቶች ምግብ ይሁን እንጂ የተሰታቸውን ይበላሉ የሚል መልዕክት በውስጡ ይዟል፡፡

- እርሟን ጠምቃ ፈጀችው ጠልቃ

ይህ ምሳሌያዊ ንግግር ተመሳሳይ መልዕክት ያለው ሆኖ ለመጀመሪያ ጊዜ መጠጥ አዘጋጅታ ግን ለሌላ ሳታስቀር እራሷ ጠልቃ ጠጥታ ጨርሰችው የሚል መልዕክት የያዘ ነው፡፡ ለቤተሰብ ኢኮኖሚ ምንም አይነት ፋይዳ ያለው ነገር አታበረክትም የሚል መልዕክት አለው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ከዚህ በፊት በትንተና እንደተገለፀው"ማውራት ነው ሴትነት መስራት ነው ወንድነት"እየተባለ ማኅበረሰቡ ሴቶች ለወሬ ብቻ የተፈጠሩ ወንዶች ግን ሰርተው የሚኖሩ ተደርገው ተስለዋል፡፡

ሴቶች ሰርተው ኢኮኖሚ የበላይ የሆኑ፤ ከወንድ ጥገኝነት የተላቀቁ ወንዶች መኖራቸው ልብ ሊባል ይገባል፡፡ ከዚህም ባሻገር ወንዶች አርሰው ደክመው ሲያመጡም ሴቶች በእኩል በሚባል ደረጃ ከመሳተፋቸው በተጨማሪ ቤት ውስጥ የሚሰራውን ማንኛውንም ስራ በጥንቃቄ አዘጋጅታ እንዳይባክን አድርጋ የማቅረቡ ሥራ የሴቶች ሚና መሆኑ መዘንጋት የለትም፡፡

በማንኛውም ማኅበረሰብ ስንፍና በወንድም ሆነ በሴት የሚበረታታ ተግባር አይደለም፤ ለሀገርም ሆነ ለግለሰብ እድገት መቀጨጭ ዋናው ምክንያት ስንፍና ነው፡፡ ማኅበረሰቡ ስንፍናንና ሰነፍን በተለያዩ ሰነቃሎች ሲያወግዘው ይታያል፡፡ ከላይ በተገለፁት ምሳሌያዊ ንግግሮች ግን ሴቶች የወንዱን ኢኮኖሚ ካለመደጎማቸው በተጨማሪ ሰንፍመሆናቸውን ያሳያሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ወንዱን ለኪሳራ ያጋልጡታል የሚል መልዕክት አላቸው፡፡ ሰነፍ ሴት ያገባ ወንድ ምንም ቢለፋና ቢደክም ንብረት ለማፍራት ዕድል አይኖረውም የሚል መልዕክት አለው፡፡

በአጠቃላይ ምሳሌያዊ ንግግሩ የወንዱን ኪሳራ መግባትን የሚገልፅ ነው፡፡ "ሰነፍ ሴት ያገባ፣ በሬው በሰኔ ገደል የገባ" በማለት እንደሚታወቀው ሰኔ ወር ማንኛውም ገበሬ ያለውን ማሳ በሙሉ የሚያርስበትና በዘር የሚሸፈንበት ጊዜ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ በሬው ገደል ገብቶ የተሰበረበት አባወራ የሚደርስበት ኢኮኖሚያዊ ኪሳራ ቀላል አይደለም፡፡ የቀጣዩ ዓመት ኑሮው የሚመሰረተው በዚህ ክረምት በአረሰውና ባመረተው እህል ላይ ነው፡፡ በተመሳሳይ ሰነፍ ሴት ማግባትም በወንዱ ላይ ይህ ነው ተብሎ የማይገመት

ስንፍናን ለሴቷ ብቻ በመስጠት ወንዱን ታታሪና ጎበዝ አድርጎ ተገልጿል፡፡ እዚህ ላይ ግን አንዳንድ ሥራን የሚጠሉ ሰነፍ ሴቶች ሊኖሩ ቢችሉም በየመጠጥ ቤቱ እየዋሉ የእርሻ ጊዜያቸው በከንቱ የሚያሳልፉ ሰነፍ ወንዶችም መኖራቸው መዘንጋት የለበትም፡፡

## 4.3 የሴቶች ማኅበራዊ ሚናን በተመለከተ የተነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች

ቤተሰብ የሚመሰረተው በወንድና በሴት እንደመሆኑ መጠን ማኅበረሰቡም የሴትና የወንድ ውህድ ነው፡፡ በመሆኑ የተሟላ ማኅበረሰባዊ ስርዓት ለመፍጠር ወንድና ሴት ሚናቸውን በአግባቡ መወጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ የሚፈጠሩ ሁነቶች በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚከውኑ ባህላዊ ክዋኔዎችና ክብረ በዓላት ላይ የወንዶች ሚና እንደተጠበቀ ሆኖ የሴቶች ሚናም እንዲሁ በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡ በመሆኑም የሰርግና የለቅሶ ስርዓቶች፣ ባህላዊና ሃይማኖታዊ አውዳመቶች፣ በተናጠልና በደቦ የሚሰሩ ሥራዎች፣ የእርቅና የሽምግልና ተግባሮች ላይ ሴቶች ካልተሳፉበት የተሟላ ሊሆኑ አይችልም፡፡

የሴቶችን ማኅበራዊ ሚና የሚገለፁ በአዎንታዊነት የተገለፁ ጥቂት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ቢኖሩም ከአሉታዎቹ ጋር ሲነፃፀሩ ግን ቁጥራቸው እዚህ ግባ የሚባል አደለም፡፡ ይህም ማኅበረሰባችን ለሴቶች ምን ያህል የተዘባ አመለካከት እንዳለው በግልፅ ያሳያል፡፡ ለአብነት ያህል በአዎንታና በአሉታ የተገለፁ ምሳሌያዊ አነጋገሮች እንመልከት፡፡

- የሴት ምክር    የሾክ አጥር
- እንጀራ ይጋገራል ማዕድ ቤት መላንያማክራል ለሴት

እነኝህ ምሳሌያዊ አነጋገሮች የሴቶችን ብልህነት ይገልፃሉ፡፡ ወንዶች ብዙውን ጊዜ የበላይነት ስለሚሰማቸው ከሴቶች ምክር አይጠይቁም እንጂ ከጠየቁ ግን አንጀት አርስ የሆነ ምክር እንደሚያገኙ ይጠቁማል፡፡ የሴት ምክር የሾክ አጥር የተባለውም ለዚህ ነው፡፡ እንደሚታወቀው አጥር በደንብ ከታጠረ በዚያ ላይ በእሾህ ከሆነ የትኛውም አውሬም ይሁን የቤት እንስሳ አይጠጋውም፡፡ በመሆኑም ሰብሉ ምንም ጉዳት ሳይደርስበት ለአጨዳ ይደርሳል፡፡ የሴት ምክርም የተለገሰው ሰው ለጉዳዩ አስተማማኝ

እልባት ያገኛል የሚል መልዕክት አለው፡፡ ለዚህም ይመስላል ሴት መለኛ ነች ዘዴ አታጣም ሲባል የሚሰማው፡፡

ሁለተኛው ምሳሌያዊ አነጋገም ይህንን ሀሳብ ያጠናክራል፡፡ የምግብ ማብሰያ ትክክለኛ ቦታው ማዕድ ቤት እንደመሆኑ መጠን የሀሳብ ዉሉ የጠፍበት ሰውም ማማከር ያለበት ሚስቱን ወይም ሴትን ነው፡፡ ሴት አንድ ሀሳብ ቢያማክሯት ብልህነቷን ተጠቅማ ለችግሩ መፍትሄ መፈለጓ የማይቀር መሆኑን ይጠቁማል፡፡

ከዚህ ባሻገር በቤተሰባዊ ህይወት ውስጥም ሴት የቤት ዋና መሰረት እንደሆነች በጥቂት ምሳሌያዊ አነጋሮች ተገልጧል፡፡ ይህም ቤት ያለሴት ከብት ያለበረት በሚል ሴት ለቤት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ተጠቁሟል፡፡ ለልጅ አስተዳደግም ሴት ወሳኝ መሆኗ አይብ ከአንቱ ልጅ ከእናቱ እንደሚባለው ነው፡፡ በተጨማሪም አባቶች ሲመርቁ "የሴት ብልሀት የጉንዳን ጉልበት ይሰጥህ" እያሉ እንደሚመርቁ በቡድን ውይይት የተሳተፉት አባቶች ነግረውኛል፡፡

በአጠቃላይ በማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ ሴቶች ያላቸው ሚና ከወንዶች ተለይተው የሚታዩ አይደሉም፡፡ ነገር ግን ይህንን ቤተሰባዊና ማኅበራዊ ሕይወታቸውንና የሚያበረክቱትን አስተዋፅኦ ይፋ አድርጎ ከመግለፅ አንፃር ማኅበረሰቡ ውስንነት ይታይበታል፡፡ ሚናቸውን የሚያንኳስሱ ሰብዕናቸው የሚያደበዝዙ ምሳሌያዊ አነጋገሮች እጅግ በርካታ ናቸው፡፡

ከላይ ያየናቸው የሴትን ምክር ጠቃሚነት የሚያጎሉ ሁለት ምሳሌያዊ አነጋገሮች እንደተጠበቁ ሆነው ከዚህ ተቃራኒ የሆኑ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ይገኛሉ፡፡ የሴት ምክር የማይጠቅም እንደሆነና ሴትን ማማከር ወደ ኪሳራ እንደሚያመራ የሚገልፁ ምሳሌያዊ አነጋገሮችም ይገኛሉ፡፡አብነት ያህልቀጥለን በአሉታዊ የተገለፁ ምሳሌያዊ አነጋገሮች እንመልከት፡፡

- የሴትን ያማከረ ደግሶ የከሰረ
- ሴትን ያማከረ ሽክሙን በሳር ያሰረ
- የሴት ምክር ማሰሪያው አሽክት

እነኝህ ምሳሌያዊ አነጋገሮች የሴት ምክር እርባና ቢስ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ የሴት ምክር የሚያመጣው ኪሳራ ከተለያዩ ነገሮች ጋር በማነፃፀር ተቀምጧል፡፡ የመጀመሪያው ደግሶ ከከሰረ ሰው ጋር ተነፃፅሯል፡፡ እንደሚታወቀው ድግስ ለመደገስ ብዙ ወጪ ይወጣል፡፡ በገጠሩ የሀገራችን ክፍል በተለይ ድግስ ለመደገስ የእርሻ በሬዎች ሁሉ ሳይቀር ይታረዳሉ፡፡ ይህ ሁሉ ድግስ ከተደገሰ በኋላ ግን የሆነ እንከን ከተከሰተ ያሁሉ ወጪ ኪሳራ ውስጥ ይገባል፡፡ ለምሳሌ ሙሽራው የሆነ ችግር ደርሶበት ከቀረአልያም ከሁለቱ ተጋቢዎች ቤተሰቦች መሀል የሆነ ሰው በእለቱ በድንገት ከሞተድግሱ ኪሳራ ውስጥ ይገባል፡፡ እንግዲህ ይህ ክስተት ነው ከሴት ምክር ጋር የተነፃፀረው፡፡

ሁለተኛው ምሳሌያዊ አነጋገርም ተመሳሳይ መልዕክት ቢኖረውም የሴት ምክር የተነፃፀረው ከማይረባ ማሰሪያ ጋር ነው፡፡ ሴትን ያማከረ ሸክሙን በሳር ያሰረ፤ የሳር ማከሪያ ወዲያውኑ የሚበጠስ፤ አጥብቆ ማሰርና መያዝ የማይችል ነገር ነው፡፡ በመሆኑም የሴት ምክር ችግርን ሊፈታ አይችልም የሚል መልዕክት አለው፡፡

ሶስተኛው ምሳሌያዊ አነጋገርም በተመሳሳይ የሴት ምክር አሽክት ከተባለው የሳር አይነት ጋርም ተነፃፅሯል፡፡ "አሽክት" ሀረግ መሰል በክረምት የሚበቅል የአረም አይነት ነው፡፡ እራሱን ችሎ ብቻውን መቆም የማይችል አጥር ወይንም ሌላ ተክል በቅርቡ ሲያገኝ ተደግፎ ያድጋል፡፡ የሴት ምክር ከዚህ አረም ጋር መነፃፀሩ የወንድ ሀሳብ ወይም ምክር ካልተጨመረበት ብቻውን ምንም ሊፈይድ አይችልም የሚል መልዕክት አለው፡፡

- ለሴት ምስጢር ማውራት በወንፊት ውሃ መቅዳት

በዚህ ምሳሌያዊ ንግግር እንደሚታወቀው ወንፊት ውሃ የመያዝ አቅም የለውም፡፡ጥቅሙም ውሃ ለመያዣነት አይደለም፡፡ ሴት ልጅ የቤቷን ገመና አትሸፍንም የነገሯትን አትቋጥርም የሚል ሴትን ዝቅ የሚያደርግ መልዕክት የያዘ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ሴት በቤት ውስጥ ሥራዎች ብቻ ተወስና መቅረት እንዳለባትና የውጭ ማኅበራዊ ሕይወት ላይ መሳተፍ እንደሌለባት የሚገልፁ ምሳሌያዊ አነጋገሮች እጅግ በርካታ ናቸው፡፡ ለአብነት ያህልም፡-

- ሴት ወደማጀት ወንድ ወደ ችሎት

- ሴት ለቤት ወፍጮ ለዱቄት
- ሴት ምን ብታውቅ፣ በወንድ ያልቅ

እነዚህ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ሴት ተምራ፣ ነግዳ ወይም አርሳ የራሷን ኑሮ መምራት የምትችል አይነት ፍጥረት እንዳልሆነችና ቤት ውስጥ ብቻ ተወስና የባሏና የልጆቿን ምግብ በማብሰል ላይ ብቻ የተመሰረተች እንደሆነች የሚያስገነዝቡ ናቸው፡፡ ይህም ሴቶች የወንዶች ጥገኛ ብቻ ሆነው እንዲኖሩ የፈረደባቸው የማኅበረሰቡን አመለካከት በግልፅ የሚያሳዩ ናቸው፡፡

ሴት ወደ ማጀት ወንድ ወደ ችሎት የሚለው ምሳሌያዊ አነጋገርም የሚያመለክተው ይህንኑ ነው፡፡ ችሎት ወንዶች የተለያዩ ውሳኔዎች ለመወሰን፣ የተጣላን ለማስታረቅ ወዘተ የሚቀመጡበት የአደባባይ ስራ ነው፡፡ ሴት ብትበደል እንኳ ችሎት ወጥታ ጉዳዩን ለዳኛ ነግራ እንድትከራከር እንኳ አይፈቀድላትም፡፡ ለዚህም ነው ሴት ምን ብታውቅ በወንድ ያልቅ እየተባለ ሴቶች የሚናገሩበት አንደበት እንኳ እንደሌላቸው ተደርጎ የሚቆጠርበት ሁኔታ እንዳለ በምሳሌያዊ ንግግር አማካኝነት የሚነገረው፡፡

እነዚህ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ሴቶች ቤት ውስጥ ተወስነው ባላቸውንና ልጆቻቸውን እየመገቡ ብቻ መኖር እንደለባቸውና የውጭው ማኅበራዊ ሕይወት ላይ ምንም አይነት ሚና እንዳይኖራቸው ተደርጎ ተቀርፀዋል፡፡ ለዚህም ይመስላል የሚከተለው ምሳሌያዊ ንግግር የሚነገረው፡፡

- የሴት መልኳ ምንድን ነው እጇን ታጥባ እንኩ ስትል ነው

ይህ ምሳሌያዊ ንግግር የተነገረው ምግብ መሥራት ድርሻዋ እንደመሆኑ መጠን የተሰራው ምግብ አቅርባ እንዲመገቡ የማድረግ ግዴታም እንዳለበት ያስረዳል፡፡ ይህንን ስታደርግ ደግሞ ማድ ቤት በሠራችበት ሁኔታ ሳይሆን እራሷን ጠብቃና አምራ የሰዎቹ የመብላት ፍላጎት እንዲጨምር የማድረግ ግዴታም አለበት ማለት ነው፡፡

- በቅሎ ገዝቶ መጭ መጭ ሚስት አግብቶ ምሳዬን አምጭ

ወንዱ በቅሎ ገዝቶ መጭ እያለ መዞር እንደዋና ተግባር የተቆጠረለት ሲሆን ቤት ገብቶ ምሳ አምጪ ብሎ የማዘዝ መብትም ተሰጥቶታል፡፡ ምሳ ተሠራ ወይምአልተሠራ ብሎ መጠየቅ የለም፡፡ ብቻ እንደምንም ትሥራው፤ ከየትም ታምጣው ባል ዞሮ ሲገባ ምግብ የማቅረብ ግዴታ የሴቷ እንደሆነ ያስገነዝባል፡፡

በአጠቃላይ በማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ ሴቶች ያላቸው ሚና በቀላሉ የሚታይ ባይሆንም ከላይ ያየናቸው ምሳሌያዊ ንግግሮች ግን ይህንን ሚናቸው ዝቅ አርገው የሚመለከቱ ናቸው፡፡ስለሆነም በእነዚህ ምሳሌያዊ ንግግሮች ማኅበረሰቡ ለሴቶች ያለው አመለካከት በግልፅ የሚያሳይ ነው ብሎ መናገር ይቻላል፡፡

## 4.4 ከደግነትና ከክፋት አንፃር የሚነገሩ ምሳሌያዊ አነጋገሮች

ደግነት በማኅበረሰቡ በጥሩ ተምሳሌት የሚያነሳው እሴት ሲሆን የዚህ ተቃራኒ የሆነው ክፋት ግን በማኅበረሰቡ ከሚወገዙ ነገሮች ዋናው ነው፡፡ በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ ብዙ አይነት ሰዎች እንደመኖራቸው መጠን ክፋትና ደግነትም ጎንለጎን የሚኖሩ ነገሮች ናቸው፡፡ ደግ ሰሪዎች እንዳሉ ሁሉ ክፉ ሰሪዎች መኖራቸውም አይቀርም፡፡

በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ሴቶችም ሆኑ ወንዶች መልካም ወይም መጥፎ ተግባር ይኖራቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ በእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ብዙውን ጊዜ ደግነት ለወንዶች የተሰጠ ባህሪ ሲሆን ክፉት ደግሞ ከሴቶች ጋር ይያያዛል፡፡ ይህ ማለት ግን ወንዶች ክፋት አይሰሩም ማለት ግን አይደለም፡፡

- የሴት ክፉ ምላስኛ የበሽታ ክፉ መጋኛ
- የሴት ክፉ አፈኛ የጎረቤት ክፉ ምቀኛ

እነዚህ ምሳሌያዊ አነጋገሮች የሴትን ክፉነት ከተለያዩ ነገሮች ጋር በማነፃፀር የተነገሩ ናቸው፡፡ በተለይም ምላሰኛ ሴት ከመጋኛ በሽታ ጋር መነፃፀሩ ሁኔታው እጅግ የከፋ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በገጠሩ ክፍል መጋኛ የተባለ በሽታ ባንድ ጊዜ ሰውን ለሞት

የሚዳርግ ነው ተብሎ መነሻፀሩ ማህበረሰቡ ለሴት ያለው አመለካከት ምን እንደሆን ያሳያል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የሴት ክፉት ከመጥፎ ጎረቤት ጋርም ተነፃፅሯል፡፡ ክፉ ጎረቤት እንደሚታወቀው ጠዋትና ማታ እየነዘነዘ ሰላም ያሳጣል ያውካል፡፡ ክፉ ሴትም ልክ እንደዚህ ጎረቤት ሰላም ትነሳለች የሚል መልዕክት አለው፡፡ ማኅበረሰቡ የሴትን ክፋት አጎልቶ ወንድን ማሞገሱ ለሴቶች ያለው አመለካከት ዝቅ ያለ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ይህንንም ሀሳብ የሚያጠናክረው “ከሴት ነገር ከበቅሎ መደንበር” አይጠፋም እያሉ ሴቶች ሁሌም ነገረኛ ተደርገው ተስለዋል፡፡ ሴት ጠብ አጫሪ የነገር ሁሉ ቀስቃሽ ተደርጋ በተለያዩ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ተገልፃለች፡፡

- ሴት ያመጣው ጠብ አይበርድም

በማለት ሴቶች ጠብ ቀስቃሽ መሆናቸው በምሳሌያዊ ንግግር ይገለፃል፡፡ ከዚህም በላይ ሴቶች ባላቸው ጠብ እንዲነሳሳ እንደሚመክሩ እና ከመጣላት ወደ ኋላ እንደማይሉም በንግግራቸው የሴቶችን ጠብ ጫሪነት "ሴት የላከው ሞት አያፈራም" በማለት ይገልፃሉ፡፡

ከዚህም በላይ "እሳት ከበረበረው ሴት የመከረው" ተብሎ የተነገረው አባባልም እሳት ከሚያደርሰው ጥፋት በላይ በሴት ነገር የተነሳው ጥፋት የበለጠ ለኪሳራ ይደርጋል የሚል እንድምታ አለው፡፡ በደግነቷና በርህሩህነቷ፤ የምትታወቀው እናት እንኳ

- የእናትን ክፍትና የደመናን ጥማት ባለቤቱ ያውቃል በማለት በክፍት ተገልፃለች

አጠቃላይ ክፋትን የተመለከቱ ምሳሌያዊ አነጋገሮች በሙሉ ለሴቶች የተሰጡ ሲሆን የዋህነት፣ ገራገርነትና ደግነት ለወንዶች የተሰጡ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ይህም ማህበረሰባችን ሴቶችን የሚመለከትበት መንገድ የሚያሳየን ሲሆን በማህበራዊ ህይወቱ ሲተረጉመውና ሲኖርበት ይታያል፡፡

## 4.5 የሴቶችን ሞኝነትና ብልህነት የሚያሳዩ ምሳሌያዊ ንግግሮች

ሴቶች በማኅበረሰቡ ውስጥ ለሚፈጠሩ ችግሮች ፈጥነው መፍትሄ የማፈላለግ ተፈጥሯዊ ችሎታ እንደላቸው ይታወቃል፡፡ ለዚህም "የሴት ምክር የሾክ አጥር" በማለት የተነገረውም ከዚህ በመነሳት ነው፡፡ እንዲያውም ብልህ ሴት በዓለም ላይ የለም የሚል መልዕክት ያለቸው ምሳሌያዊ አነጋገሮች ሲነገሩ ይሰማል፡፡

- ብልህ ሴትና ቀንዳም አህያ አይገኙም

እንደሚታወቀው አህያ ከጋማ ከብቶች አንዱ በመሆኑ ቀንድ ሊኖረው አይችልም፡፡ በመሆኑም ቀንድ ያለው አህያ በአለም ላይ ቢፈለግ ማግኘት አይቻልም፡፡ በተመሳሳይ ብልህና አስተዋይ ሴትም ብትፈለግ ማግኘት ያስቸግራል ለማለት ነው በምሳሌያዊ አነጋገሩ የተነገረው፡፡ ይህም ማኅበረሰቡ የሴቶችን ብልህነት የሚያይበት መንገድ የተዛባ መሆኑን ያሳያል፡፡

ምሳሌያዊ ንግግር የሴቶች አስተሳሰብ ዝቅ ያለና አሰተውሎት የጎደላቸው እንደሆኑና ይህም ዋጋ እያስከፈላቸው መሆኑ የሚያመለክት ምሳሌያዊ አነጋገር ነው፡፡ምሳሌያዊ ንግግሩ በሴት ፆታ ይነገር እንጂ የራሱን ያልሆነ ነገር የሚፈልግ ሰው "በእጅ ያለው ያብል" የሚል መልዕክትም አለው፡፡

- ሴት ማገዶ ቢቸግራት ምሰሶ ትነቅላለች

ምሰሶ የምንለው ቤቱን በሙሉ ተሸክሞ የሚያቆም የቤት ዋና መሰረት ነው፡፡ የቤቱ ምሰሶ ወደቀ ማለት ቤቱ ሙሉ በሙሉ ፈረሰ ማለት ነው፡፡ ይህም ለማገዶ ብላ ቤቷን አፍርሳየምታቃጥል ሴት ባትኖርም ሴቶች ለቤታቸው ምንም እንደማያሰቡ ተደርጎ መታየታቸውን የሚያመለክት ምሳሌዊ አነጋገር ነው፡፡ ለትንሽ ችግር ብላ ሌላ ትልቅ ችግር ታመጣለች የሚል መልዕክትም አለው፡፡

- ከባልዋ ብትጣላ ብልትዋን በካራ
- እንስራዋን ረስታ ወደ ወንዝ ወረደች

የሚሉ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ሴት ምን ያህል ሞኝ እንደሆነች የሚያሳብቁ ናቸው፡፡በተለይ የመጀመሪያው ምሳሌያዊ አነጋገር የሚያሳየው ከባሏ የተጣላች ሴት ባሏን የተበቀለች መስሏት የራሷን ሰውነት በቢላዋ የምትዘለዝል ሞኝ ተደርጋ ተቆጥራለች፡፡ መቼም አንድ ሰው አዕምሮውን ካልሳተ ወይም ካላበደ በስተቀር የራሱን ሰውነት ይቆርጣል ተብሎ አይታሰብም፡፡

ሁለተኛው አባባልም ይህንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡ ውሃ ለመቅዳት የምትሄድ ሴት ባዶ እጇን ወንዝ ትወርዳለች ብሎ መገመት ይከብዳል፡፡ ይህም የሴት አስተሳሰብ ወይም ሞኝነት አጉልቶ የሚያሳይ ነው፡፡

- ያማ ያማ ለፀሎተ ሐሙስ እርጎ ትልስ
- ትለብሰው የላት ትከናነበው አማራት
- ግማሹን ተላጭታ ግማሹ ተቀበታ

እነዚህ ምሳሌያዊ ንግግሮች በአጠቃላይ የሴትን ሞኝነት የሚያጎሉ ናቸው፡፡ማኅበረሰቡ የሴቶችን ብልህነት በማንኳሰስ አላዋቂነታቸውንና ሞኝነታቸውን ብቻ አጎልቶ በማየት ሚናቸውን በአግባቡ እንዳይወጡ እንቅፋት ከመሆኑም በላይ የሚሰሩትን ሥራ በማንቋሸሽና እንደጅል በመቁጠር ሞራላቸው ሲጎዳ ይስተዋላል፡፡

## 4.6 ከፈሪነትና ከጀግንነት አንፃር ስለ ሴቶች የተነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች

በአብዛኛው የማኅበረሰባችን ክፍል ሴቶች የፈሪነት ተምሳሌት ተደርገው ሲወሰዱ ወንዶች ደግሞ የጀግንነት ተምሳሌት ተደርገው ይሳላሉ፡፡ምንም እንኳን ሴቶች በየጊዜው በተለያዩ መስኮች የጀግንነት ተግባርና ገድል ቢፈፅሙም ማኅበረሰቡ ከልቡ ለመቀበል ሲቸገር ይታያል፡፡ ይህም በተለያዩ ምሳሌያዊ ንግግሮች እንዲህ ይገልፃቸዋል፡፡

- ፈሪ የናቱ ልጅ ነው

ከዚህ ምሳሌያዊ ንግግር መረዳት የምንችለው አንድ ልጅ ተወልዶ በአጋጣሚ ፈሪ ከሆነ በእናቱ ይሳበባል፡፡ልጁ በእናቱ ወጥቶ ነው ይባላል እንጂ አባቱ ፈሪ ስለሆነ ነው አይባልም፡፡ሴቶች ደፋርና ጀግና ቢሆኑ እንኳ ከማበረታታት ይልቅ ሞራላቸውን በመስበር በቤት ውስጥ ብቻ እንዲወሰኑ ይደረጋል፡፡ ለምሳሌ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ምሳሌያዊ ንግግር መመልከት ይቻላል፡፡

- የካህን አይናፋር፣ የአህያ እውር፣ የሴት ደፋር አይረባም፡፡

በማለት ደፋር ሴቶችን በማውገዝከእውር አህያ ጋር በማነፃፀር ሴት ልጅ ደፋር እንኳ ብትሆን ምንም አትረባም፣ የትም አያደርሳትም በማለት ቤት አርፋ እንድትቀመጥና የወንድ ጥገኛ ሆና እንድትኖር ስትገፋፋ ይታያል፡፡

- ወንድ ልጅ ተወልዶ ካልሆነ እንደ አባቱ ስጡት አመልማሎ ይፍተል እንደ እናቱ፡፡

የሴት ሥራ የፈሪ ሥራ ነውና ጀግና ያልሆነ ወንድ ለመቀጣጫ ይሆነው ዘንድ የናቱን ሥራ እንዲሠራ ይፈረድበት የሚልመልዕክት አለው፡፡በአጠቃላይ ማኅበረሰቡ የሴትንሥራ ከባድነት ባለመገንዘብ ቤት ውስጥ የሚሠሩ ሥራዎች በሙሉ እንደቀላል በመቁጠር ሴትን የፈሪ ወንድን ደግሞ የጀግና ምሳሌ በማድረግ የተዘባ አመለካከቱን በፈጠራቸው ምሳሌያዊ አነጋገሮች እየገለፀ ይኖራል፡፡

- ከሴት ትብሱ ትመለሱ
- ሴት ጅብ ትፈራለች አጥር ትመዛለች

እነኝህ ምሳሌያዊ አነጋገሮች  የሴቶች ፈሪነት ከተለያዩ ነገሮች ጋር በማነፃፀር የተገለፁ ናቸው፡፡ የመጀመሪያው ምንዳ በሚጠይቅ ቄስ ጋር የተፃፀረችው የሴት ብትረኛ ናት፡፡ እንደሚታወቀው ቄስ የሃይማኖት አባት እንደመሆኑ መጠን ለሚያከናውኗቸው ሃይማኖታዊ ተግባራት ምንዳ መጠየቅ አሰነዋሪ ተግባር ነው፡፡ ሴትም እራሷን ለመከላከል እንኳ በትር ብታነሳ ወይም ብትደባደብ እጅግ አሰነዋሪ ተግባር እንደፈፀመች ተደርጎ ይቆጠርባታል፡፡ ምክንያቱም ባህሉ ወንድ ተደባዳቢ ሴት ደግሞ ተደብዳቢ አድርጎ መብት አጎናፅፏቸዋል፡፡

ሁለተኛው ምሳሌያዊ ንግግር የሚያመለክተው ይህንኑ ነው፡፡ከሴት ትብሱ ትመለከሱ ማለት ሴት የፍርሃት ምንጭና ተምሳሌት ተደርጋ መቆጠሯን የሚያሳይ ነው፡፡ የሴትን ፈሪነት የሚያሳዩ ምሳሌያዊ አነጋገሮች እጅግ ብዙ ቢሆኑም ለማሳየት አጥኚው ከላይ ያሉትን ብቻ በመምረጥ ለማሳየት ሞክሯል፡፡

## 4.7 ከከሀዲነትና ከታማኝነት አንፃር የተናገሩ ምሳሌያዊ አነጋገሮች

ከሀዲነት በወንዶችም በሴቶችም የሚታይ ባህሪ ቢሆንም በእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ጥሩ ጥሩ ባህሪይ ለወንዶች መጥፎ ባህሪይ ደግሞ ለሴቶች ያደረገው የማኅበረሰባችን ባህል የከሀዲነት ባህሪ ለሴቶች የታማኝነት ደግሞ ለወንዶች ሲሰጥ ይታያል፡፡ ይህም በተለያዩ ምሳሌያዊ አነጋገሮቹ ሲገልፅ ይስተዋላል፡፡

- ሴትን ያመነ ጉም የዘገነ
- ሴትና ድመት የኔናት አይባልም
- የሚነቃነቅ ግንድና የምትስቅ ሴት ልብ ሩቅ ናት
- ሴትና ጉም አይዘናጉም

እነዚህ ምሳሌያዊ አነጋገሮች በአጠቃላይ ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፡፡ የሴትን አለመታመን ከተለያዩ ነገሮች ጋር በማነፃፀር ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

የመጀመሪያው ምሳሌያዊ ንግግር ሴትን ከጉም ጋር ተነፃፅራለች፡፡ እንደሚታወቀው ጉም ከሩቅ ሲታይ ጭስ ቢመስልም ነገር ግን ሲቀርቡት የሚጠፋ ሊጨበጥ የማይቻል እንፋሎት ነው፡፡ ሴትን ማመን ይህንን እንፋሎት ከመዝገን ጋር ተነፃፀሯል፡፡ በጭራሽ ሴት መታመን የለባትም የሚል መልዕክት አዝሏል፡፡

ሌላኛው ምሳሌያዊ ንግግር ደግሞ ሴትን ከድመት ጋር በማመሳሰል የተነገረው ነው፡፡ እንደሚታወቀው ድመት የብዙ ሰው ቤት ይገባል፡፡ ነገር ግን ተረጋግቶ የሚቀመጠው ምግብ ባገኘበት ቦታ ነው፡፡ ስለዚህ ሴትም ከፍቅር ይልቅ ሆዷን ወይም

ጥቅምታሰቀድማለች የሚል መልዕክት የያዘ ነው፡፡ ሌሎቹም አነጋገሮች ተመሳሳይ መልዕክት ያላቸው ናቸው፡፡

- ሴትና ዶሮ ዱር ሲሄዱ ቤታቸውን ይከዱ
- ውሽማዋን ብታየው ባሏን ጠላችው
- ጨረቃና ሴት ዛሬ ብርሃን ነገ ፅልመት

የመጀመሪያው ምሳሌያዊ ንግግር የሴት ክህደት ከዶሮ ጋር ተመሳስሏል፡፡ ሴትና ዶሮ ዱር ከሄዱ ቤታቸውን ይክዱ በሚል ምንም እንኳ ሴት ለቤቷ አሳቢና ተቆርቋሪ ብትሆንም በማኅበረሰቡ የተሰጠት ስያሜ ግን ጫካ ሄዶ ከጠፋ ደሮ ጋር በማመሳሰል ነው፡፡ በአጠቃላይ ሴቶች በማህበረሰቡ ውስጥ ታማኝነት የሌላቸው የከሀዲነት ተምሳሌት ተደርገው የተሳሉ ሲሆን ይህም ለሴቶች የተዛባ አመለካከት መኖሩ የሚያሳዩ ናቸው፡፡

## 4.8 የሴቶችን ገንዘብ ወዳድነት የሚጠቁሙ ምሳሌያዊ ንግግሮች

ገንዘብ ማንኛውም ሰው ቢወድም በንፅፅር ከወንዶች ሴቶች ገንዘብ ወዳድ እንደሆኑ በምሳሌያዊ ንግግር አማካኝነት ይገልፃሉ፡፡ እንደዚህ አይነት ምሳሌያዊ ንግግሮች በአብዛኛው የሚነገሩት ከገጠር ይልቅ በከተማ ነው፡፡ ጥናቱ ከተጠናበት የከተማ ቀበሌ በቃለ መጠይቅ እና በቡድን ውይይት መረጃ አቀባዮቼ የሚከተሉትን ምሳሌያዊ ንግግሮች በብዛት እንደሚነገሩ ገልፀውልኛል፡፡

- ገበያ ቢያመቻት ልጇን ሸጠቻት
- ሴትና ጆተኒ ያለ ሳንቲም አይሰሩም
- ቅጠል ብር ቢሆን ኑሮ ሴቶች ጦጣ ያገቡ ነበር

እነዚህ ምሳሌያዊ አነጋገሮች የሴትን ገንዘብ ወዳድነት አጉልተው የሚያሳዩ ናቸው፡፡ገንዘብ ወዳድነታቸው ለማንም እዝነት ወይም ርህራሔ እንደሌላቸው ሲገለፅ ልጇን እንኳ እስከ መሸጥ የሚያደርስ እንደሆን በኩሽትተገልፃል፡፡ እናት ለልጇ ምን ያህል እንደምትንሰፈሰፍና እንደምትራራ በግልፅ ይታወቃል፡፡  ልጇ ምንም ቢሆን

በገንዘብ ትለውጣለች ተብሎ አይታሰብም፡፡ ይሁን እንጂ ማኅበረሰቡ የሴትን ክህደት ለማሳየት ምን ያህል አግዝፎ እና አጉልቶ እንደሚመለከተው ያሳያል፡፡

ከሁለተኛው ምሳሌያዊ ንግግር መረዳት እንደሚቻለው ሴቶች ምን ያህል ገንዘብ ወዳጅ እንደሆኑ ጆተኔ ያለ ሳንቲም እንደማያጫውት ሁሉ ሴቶችም ያለ ብር ምንም ነገር እንደማይሰሩ በንፅፅር ቀርቧል፡፡ ይህ ምሳሌያዊ ንግግር የሚዘወተረው በከተማ አካባቢ በወጣቱ የሚነገር መሆኑን የቃለ መጠይቅ መረጃ አቀባዮች ገልፀውልኛል፡፡ በገጠሩ እንዲህ አይነት ምሳሌያዊ ንግግር አይነገርም፡፡

ሦስተኛው ምሳሌያዊ ንግግርም ሴቶች ለገንዘብ ሲሉ ሁሉን ነገር የሚከዱ ከዳተኛ መሆናቸው ያሳያል፡፡ ማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር ወንድም ሆነ ሴት ገንዘብ ወዳድ ቢሆንም ከትንታኔው መረዳት እንደሚቻለው በእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ሴቶች ከወንዶች በይበልጥ ገንዘብ ወዳድ ናቸው በማለት በምሳሌያዊ ንግግር አማካኝነት ሀሳባቸውን ለመግለፅ ይሞክራሉ፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያና ይሁንታ

በዚህ ምዕራፍ በጥናቱ የተገኙ ዋና ዋና ውጤቶች ማጠቃለያና እነዚህ ግኝቶችን መሰረት በማድረግ የቀረቡ አስተያየቶች ናቸው፡፡

### 5.1 ማጠቃለያ

ምሳሌያዊ አነጋገሮች በውስጣቸው አምቀው የያዟቸው ሀሳቦች ከማኅበረሰቡ የእለት ተዕለት ኑሮ ገጠመኝና ምልከታ የተገኙ ሲሆኑ ማኅበረሰቡ የሚያምንባቸውና ትክክል ናቸው ብሎ የተቀበላቸው የሀሳብ መግለጫዎች ናቸው፡፡ ምሳሌያዊ ንግግሮች ጥሩም ይሁኑ መጥፎ በሰዎቸ ላይ ተቀባይነት ያላቸውን በቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ ይተላለፋሉ፡፡

በመሆኑም ይህ ጥናት ዋና ዓላማው አድርጎ የተነሳው በእነብሴ ሳርምድር ወረዳ ስለሴቶች የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮችን በመሰብሰብ ይዛታቸው ምን እንደሚመስል በመተንተን ማሳየት ነው፡፡ ይህን ዋና ዓላማ መሰረት በማድረግ ምሳሌያዊ ንግግሮቹን የሚነገሩበት ዓውድ ሴቶች ከወንዶች ጋር ያላቸው ግንኙነት ምን እንደሚመስልና የምሳሌያዊ አነጋገሮቹ ይዘት ምን እንደሆነ ማብራራት የሚሉ ዝርዝር ዓላማዎች በመያዘ ጥናቱ ተሰርቷል፡፡

ጥናቱ ስለ ሴቶች የተነገሩ ምሳሌያዊ አነጋገሮች በጥቂቱ በአዎንታ የተገለፁ ሲሆን አብዛኞቹ በአሉታ የተገለፁ እንደሆነ በትንተናው ሂደት የታየ ሀቅ ነው፡፡ ምሳሌያዊ አነጋገሮቹ ለትንተና እንዲመቹ ሆነው በ6 ርዕሰ ጉዳዮች ተከፍፈለዋል፡፡ እነኝህም የሴቶችን ቤተሰባዊ ዝምድና የሚያሳዩ፣ የሴቶችን ኢኮኖሚያ ፋይዳ የሚጠቅሱ፣ ሴቶች ከማኅበራዊ ሕይወት አንፃር ያላቸውን ሚና የሚያንፀርቁ፣ ሴቶችን ከደግነትና ክፋት አንፃር የሚቃኙ፣ ከብልህነትና ከየዋሕነት ጋር የሚዳሰሱና ሴቶችን ከፈሪነትና ከጀግንነት አንፃር የሚጠቅሱ በማለት ተተንትነዋል፡፡

ሴቶችን በእናትነት የሚያወሱ አብዛኞቹ ምሳሌያዊ አነጋገሮች በአዎንታ የተገለፁ ሲሆን ይህም ማኅበረሰባችን ለእናት ያለው ከበሬታ ያሳያል፡፡ ሴትን በሚስትነት የሚገልፁ አነጋገሮች የተገለፁት ሴት ለባልና ለቤቷ አስፈላጊ መሆኗን የሚያወሱ በአዎንታ የተገለፁ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ቢኖሩም ለወንዱ ካላቸው አስፈላጊነት አንፃር የተቃኙ እንጂ የራሳቸውን ኑሮ ከመምራት አንፃር የተገለፁ አይደሉም፡፡ ከዚህም ባሻገር ለባል የማይበጁና የሚኮሰኩሱ እንዲሁም ያለባል መኖር እንደማይችሉ ተደርገው የተሳሉ ናቸው፡፡ በተጨማሪም ማኅበረሰባችን ሴትን እንደልጅ አድርጎ በመቀበል በኩል የተዛባ አመለካከት መኖሩ በትንተናው የተገለፁ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ማየት ተችሏል፡፡

ከኢኮኖሚያዊ ፋይዳ አንፃርም ሴቶች የወንዶ ጥገኛ ተደርገው ተቀርፀዋል፡፡ በምሳሌያዊ አነጋገሮቹ እንደታየው ሴቶች የባሎቻቸውን ኢኮኖሚ የሚያቃውሱ ምንም ሳይሠሩ የሚበሉ ተደርገው ተገልፀዋል፡፡ በቤተሰባዊ ሕይወት ውስጥ ሴቶች የጎላውን ድርሻ የሚወስዱ ቢሆንም ቤትን አስተካክለው መያዛቸው፣ሕፃናትን ተንከባክበው ማሳደጋቸው፣ ለባሎቻቸው፣ ለልጆቻቸውና ለራሳቸው የሚሆን ምግብ ማዘጋጀታቸው በሙሉ ማኅበረሰቡ እንደቀላል ነገር በመቁጠርና ሥራ ፈት አድርጎ በማየት ወንዱ ብቻ ለቤተሰቡ አሳቢና ተቆርቋሪ በመሆን የማኅበረሰቡ ግንዛቤ ምን ያህል ኋላቀርና የተሳሳተ መሆኑ በትንተናው ተመላክቷል፡፡

የሴቶች ማኅበራዊ ሚናን በተመለከተ የሴቶችን ምክር ጠቃሚነት የሚያመለክቱ በአዎንታ የተገለፁ ጥቂት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ቢኖሩም ይህም ለወንዶች ካላቸው ጠቀሜታ አንፃር የታዩ እንጂ ለሴቶች ሕይወት ጠቃሚ ናቸው በሚል የተቀመጡ አይደሉም፡፡ ከዚህ በተቃራኒ ደግሞ የሴት ምክርም ቢሆን እንደ አክሳሪ ተደርጎ የታየበት ሁኔታ መኖሩም በጥናቱ ተስተውሏል፡፡ ሌላው ደግሞ የሴቶች ማኅበራዊ ሚና በቤት ውስጥ ብቻ ለዚያውም በማጀት ውስጥ ተወስነው እንዲኖሩ የተፈረደባቸው ሲሆን ወንዱ ግን አደባባይ በመውጣት ማኅበራዊ የበላይነቱን በሙሉ ጠቅልሎ እንዲወስድ ባህሉ ያመቻቸለት መሆኑ በጥናቱ በሰፋት ታይቷል፡፡

በአጠቃላይ ሴት የወንድ አገልጋይ እንጂ የራሷን ቤተሰባዊና ማኅበራዊ ሕይወት ያላት ፍጡር መሆኗ የተዘነጋ መሆኑ በምሳሌያዊ አነጋገሮች በሰፋት ተዳሷል፡፡

ሴቶች ምላስኛነትን ጠብ አጫሪነትን እንዲሁም መስሪነትን ባህሪያት እንዲላበሱ የተደረገ ሲሆን ይህም ማኅበረሰባችን ሴቶችን የሚያይበት መነፅር ምን ያህል የተዘባ መሆኑ በትንተናው ታይቷል፡፡

ከፈሪነትና ከጀግንነት አንፃር የተገለፁትም ቢሆኑ ፈሪነት ለሴት የተሰጠ ባህሪ ሲሆን ጀግንት ደግሞ ለወንዱ የተሰጠ ባህሪ ነው፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን ሴት ደፋር እንኳ ብትሆን ምንም እርባና እንደሌላት ተደርጋ እንድትታይና ሞራሏ እንዲጎዳ በማድረግ አርፋ እቤት ውስጥ ተወስና እንድትኖር የሚያደርጉ የኅብረተሰቡ አመለካከት መነፅር የሆኑ ምሳሌያዊ አነጋገሮቹ አሳይተዋል፡፡

ከከሀዲነትና ከታማኝነትም አንፃር ምሳሌያዊ አነጋገሮቹ ሲፈተሸ ታማኝነት ለወንዱ የተሰጠው ባህሪ ሲሆን ከሀዲነትን ደግሞ የሴቷ ባህሪ ሆኗል፡፡ ይህንን ከሀዲነቷን ለማጉላትም ከተለያዩ ነገሮች ጋር ከጉም፣ ከድመት፣ ከዶሮ ወዘተ ተነፃፅራ ተገልፃለች፡፡ ይህም ማኅበረሰቡ ለሴቶች ያለው አመለካከት ምን ያህል የተዛባ እንደሆነ ያሳያል፡፡

የባልና ሚስት ግንኙነትን በተመለከተ የተነገሩ ምሳሌያዊ አነጋገሮች በተፈተሹበት ክፍል የታየው ደግሞ ባሎች ሚስቶቻቸውን በፍቅርና በርህራሄ እንዲያስተዳድሩ የሚመክሩ ሳይሆኑ በተቃራኒው በዱላና በድብደባ በማስተዳደር ፍፁም የበላይነቱን ወስደውና ተፈርተው ማኖር እንደለባቸው ሙሉ መብቱን ተሰጥቷቸው እናያለን፡፡ ይህም ባጭሩ ሴትና አህያን በዱላ በሚል አገላለፅ ተቀምጧል፡፡ አንድ ባል ህጋዊ ሚስቱን የፈለገውን ያህል ቢበድላት ህጋዊ ተግባር እንደፈፀመ እንጂ ህገወጥ መሆኑ የተዘነጋ በመሆኑ በደል የደረሰባትሄዳአቤት የምትልበት ሁኔታ አለመኖሩ በትንተናው ታይቷል፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ጥናት የተዳሰሱ ምሳሌያዊ አነጋገሮች የወንድን የበላይነት የሚያሳዩየሴትን የበታችነትና በማኅበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ቦታንና የሚደርስባቸውን ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ስነ ልቦናዊ ግፍ በግለፅ ፍንትው አድርገው የሚያሳዩ ምሳሌያዊ አነጋገሮች በሰፋት ተዳሰዋል፡፡ አጥኚውም ይህንን መሰረት በማድረግ ቀጥሎ ምን መደረግ አለበት በሚል የራሱ የይሁንታ ሀሳቦች ጠቁሟል፡፡

## 5.2 ይሁንታ

የስርዓተ ፆታ ጉዳይ ሲነሳ የኅብረተሰቡ ባህልም አብሮ ይነሳል። ምክንያቱም ባህል ከጥንት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋርድ የመጣ የማኅበረሰባችን አጠቃላይ የአኗኗር ሂደት በመሆኑ ነው። ባህል በአንድ ጀምበር የሚቀየር ነገር አለመሆኑም በበርካታ ጥናቶች ተመላክቷል። ለዘመናት የወንዶችን የበላይነትና የሴቶችን የበታችንት አምኖና ተቀበሎ የኖረን ማኅበረተሰብ በአንድ ሰሞን ወከባና ግርግር ተነስቶ ሴቶችን እኩል ማድረግ ወይም የበላይ ማድረግ አይቻልም። በመሆኑም ከሰርዓተ ፆታ ጋር የሚሠሩ ሥራዎች በሙሉ በተጠና ስልት በማኅበረሰቡንበማሳተፍ በርካታ ስራመሰራት ይኖርበታል።

የሴቶችን የበታችነት የሚያንፀባርቁት ወንዶች ብቻ አይደሉም። ራሳቸው ሴቶች በምሳሌያዊ ንግግር ይህንኑ ስያጠናክሩት ይስተዋላል።ለዘመናት ሴቶችም የወንዶች የበታችነ ነን በሚል አምነውና ይህንን ተቀበለው የኖሩ በመሆኑ ከወንዶች እኩል መሆናቸው ማሳመኑ ሌላው ፈተና ነው። በከተሞች አካባቢ የሚኖሩ ሴቶች የፆታ እኩልነት በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ተገንዝበው ሊሆን ይችላል። ወደ ገጠሩ የኅብረተሰባችን ክፍል ስንወርድ ግን አሁንም ድረስ በማጀት ተወስነው የቤቱን ስራ ብቻቸውን የሚሰሩ፣ ሲደክሙ ውለው ማታ ተንበርክከው  የባሎቻቸውን እግር የሚያጥቡ፣ አልፎ ተርፎም የውጪውን ስራ ከወንዶች ጋር በመስራትሌት ተቀን የሚለፍበርካታ ሴቶች አሉ። ስለዚህ ይህን ተግባር በአንድ ጊዜ ህገ ወጥ ድርጊት ነው ብሎ ከመንቀፍ ባለፈ ተከታታይ የሆነ ትምህርት በመስጠት የማኅበረሰቡን አመለካከት ለመለወጥ ጥረት መደረግ ይኖርበታል። የሴቶችን እኩልነትና የልማት ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በሚደረገው ርብርብ ወንዶችም በዋናኛነት እንዲሳተፉበት ማድረግ ያስፈልጋል። በአሁኑ ጊዜ በሴቶችና ህፃናት ቢሮ ይሁን በአንዳንድ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች አማካይነት የሴቶችን እኩልነት ለማረጋገጥ የተጀመሩ ተግባራት ቢኖሩም ወንዶችን ያላሳተፉ በመሆናቸው ውጤት ማምጣት ሳይችሉ ቀርተዋል። አንዱን ጥሎ ሌላውን አንጠልጥሎ የሚሠራው ሥራ ውጤት ሊያመጣ ስለማይችል አካታች የሆነ ተግባር ቢከናወን የሚል ሀሳባ አለኝ።

የስርዓተ ፆታን ጉዳይ በስፋት በትምህርት ስርዓት ውስጥ በማካተት ታዳጊ ህፃናት የሴቶችን እኩልነት ተረድተው እንዲያድጉ በማድረግ በስነቃል አማካይነት የተላለፉ የፆታ መድሎዎችን ለመከላከል ስለሚያስችለው በዚህ በኩል ጠንካራ ሥራ መሥራት ያስፈልጋል፡፡ የሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ባለድርሻ አካላት በተለይም የባህል ሚኒስቴር፤ የትምህርት ሚኒስቲርና የሴቶችና ህፃናት ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር በጋራ በመተባበር በኅብረተሰቡ የሚነገሩ ምሳሌያዊ አነጋገሮች እንደገና በመሰብሰብ በህትመት መልክ እንዲታተሙ ቢደረግ፡፡ በአጠቃላይ ስለሴቶች በአሉታ መልክ የተነገሩ አባባሎች ሁለቱንም ፆታ(ወንድን እና ሴትን) እንዲወክሉ ቢደረግ፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች


መስፍን መሰለ ። (2002)። "ስለ ሴቶች በተቃርኖ የሚነገሩ የአማርኛ ምሳሌያዊ ንግግሮች" ዜና ልሳን፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ተቋም መጽሄት፣ ቅጽ፡XXI ቁጥር 1፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ።

መኮንን አስማማው።(2007)።"በደላንታ ወረዳ የአበሹቴ እና የኧኸይቦሌ ቃል ግጥሞ ክዋኔና ይዘት ትንተና"። የኤም ኤዲግሪ ማሙያ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የአማርኛ ቋንቋ ስነ ፅሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣አዲስ አበባ።

መዓዛ ከበደ:: (2006)።"በወላይታና በጋሞ ምሳሌያዊ ንግግሮች የሚታዩ ፆታ ተኮር አዎንታዊና አሉታዊ ተበላልጦ ተንተና" በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፎክሎርና ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል በባችለር ዲግሪ፣አዲስ አበባ።

ሰለሞን ተሾመ:: (2007*)።ፎክሎር ምንነትና የጥናት አቅጣጫ ።* አዲስ አበባ ፣ ፋርኢስት ትሬዲንግ ኃላ.የተ.የግ.ማ።

ብርሀን አሰፋ። (2009)።"በተረቶች ውስጥ የታዩ የሥርዓተ ጾታና የሥልጣን ኢፍትሃዊ መስተጋብሮች" በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂውማኒቲስ የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ አማርኛ ቋንቋ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣አዲስ አበባ።

ብርሐኑ ገ/ፃዲቅ። (1996)። *የአማርኛ ምሳሌያዊ ንግግሮች እና ፍቺዎቻቸው ።* ሜጋ አሳታሚ ድርጅት፣ አዲስ አበባ።

ያለው እንዳወቀ። (2001) *የምርምር መሰረታዊ መርሖች አተገባበር* ። አ.ብ.ክ.መ ትምህርት ቢሮ።

ደበበ ኃይለጊዮርጊስ።(1999)።*አዲስ የምሳሌያዊ ንግግሮች መፅሐፍ*፡አስቴር ነጋ አሳታሚ

ድርጅት፣ አዲስ አበባ፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡(1992)*የስነ ፅሑፍ መሰረታዊያን*፡አዲስ አበባ ንግድ ማተሚያድርጅት፡፡

ፈቃደ አዘዘ፡፡ (1991) *የስነ - ቃል መምሪያ* ፡፡ ቦሌ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ ፡፡

--------- (2006*) የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦች ህዝቦች ምሳሌያዊ ንግግር* ፡፡ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር፣ አዲስ አበባ፡፡

Aschalew Bililigne. (2012). “Female Disempowerement: Some expressions in Amharic” Department of Lingustics in Practical Fulfilment of the Reqirements for degree of Master Arts in Lingustics; Addis ababa universtsity.

Bauman, Richard. (1984). *Story, Performance and Event*. Contaxtual studies of Oral Narrative. Combridge; Combridge university press.

Chilisa (2012).*Indigenous Research Methodologies*.SAGE Publications, Washington.DC.

David Pace. Structuralism in History and the social sciences. American quarterly,Volume 30, Issue 3(1978).

Finnegan, Ruth(1977).*Oral Poetry: its nature, significonce and social context.*Combridge university press.

Finnegan, Ruth.(1970).*Oral Literature in Africa.*Combridge university press.

Goldstein,kenneth. (2005). S.A *Agide for filed works in folklore*.Detroiter; gale research company.

Miruka, (1994). *Encounter with oral Literature*. Nairobi. EAEP.

Moi, Toril.(1985). *Sexual /Textual poliyics; Feminist literary theory*. London;

Methuen.

Morson, Gary Saul.(1981).*The Boundaries of Genre*.Austin; university of Texas press.

Okpewho,Isidore.(1992.)*Africa oral Literature, backgrounds, character and continuity*.Indianopolis: Indian University press.

Reeves, Hazel and Baden, Sally. (2000). *Gender and Development: Concepts and Definitions.* Brighton: Institute of Development Studies.

Sims stepens.(2005).*Living forklor an introduction to the study of people and their tradition*.Utah: Utah stafe university press.

# አባሪዎች

## አባሪ 1 ስለ ሴቶች የተነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ስብስብ

1. ልጅ ያለእናት ቤት ያለጉልላት
2. እናት የሌው ልጅ ቀላል እንደጌሾ ሳይበላ በላ ነው ሳይናገር ዋሾ
3. ከናት ወዲያ ዘመድ፣ ከቃጫ ወዲያ ገመድ
4. አዎን ያለች ምላስ፣ እናት የሌላት አራስ
5. የእናት ሞትና የእግር እሳት እያደር ያንገበግባል
6. የእናት ሞትና የድንጋይ መቀመጫ እያደር ይቆረቁራል
7. የደመና ውሀ ጥምና የእናት በደል አይታወቅም
8. የእናትን ክፋት፣ የደመናን ውሃ ጥማት ባለቤቱ ያውቀዋል፡፡
9. እንኳን እናቴ ሞታ ወትሮም አልቅስ አልቅስ ይለኛል
10. የሚስት አሳቢ የጥንድ በሬ ሳቢ ይሰጥህ
11. መልካም ሚስት፣ ለባሏ ዘውድናት
12. ያለሴት ቤት፣ ያለበሬ መሬት
13. እንጀራ ያለወጥ፣ ቤት ያለሴት፣ ክብት ያለበረት
14. ጠመንጃ ያለጥይት ዱላ፣ ወንድ ያለሴት ነውላላ
15. ከወና ቤት፣ ወና ሚስት
16. ስንዴ ራቱ፣ ወይራ እሳቱ፣ ማለፊያ ሚስቱ፣ ለምን ሰርግ ይሄዳል ሰርግ አለ እቤቱ
17. ሚስቱ ክፉ፣ ባቂላ እራቱ፣ ብሳና እንጨቱ ሀዘን ነው ቤቱ
18. ደረቅ እንጀራ በርበሬ ነስንሳ፣ ብትበላ ብላ ባትበላ ላንሳ
19. ወዳጅህን ጥራ ውሻዬን፣ ጠላትህን ጥራ ሚስቴን
20. ባል የሌላት ሴት፣ የመንገድ ዳር እሸት
21. ያለባል ሴት ወይዘሮ፣ ያለማንገቻ ከበሮ
22. ወንዶች ምን ያወራሉ የሚመጣውን፣ ሴቶች ምን ያወራሉ ያለፈውን
23. ማውራት ነው ሴትነት፤ መስራት ነው ወንድነት

24.ያለሥራ አይበላ እንጀራ፣ አለባል ቆጥ አይሠራ
25.የታደለች ሴት በፊት ትወልዳለች ሴት
26.በሴት የበከረ ከእግዜር የተማከረ
27.ሴት የሌለበት ወንድ አይበቅልበት
28.ሴት የወለደ መቀመቅ ወረደ
29.ሴት አግብተው ሴት ከወልዱ የት አለ ንግዱ
30.ሴት የወለደ፤ ጉድ ወለደ
31.ሴት የወለደ፤ ተዋረደ
32.ሴት የወለደ፤ አመድ የነገደ
33.ወንድ የወለደ እንደ እግዜር የከበደ
34.ከሴት ሆዳም የአንድ አመት በረዶ ይሻላል
35.ሴትና ፈረስ የሰጡትን ይቀምስ
36.እርየቆጡን አወርድብላ የብብቷን ጣለች
37.ሴት ማገዶ ቢቸግራት ምሰሶ ትነቅላለች
38.ሚን ጠምቃ ፈጀችው ጠልቃ
39.ሰነፈ ሴትእድል የላት ለንብረት
40.ሰነፈ ሴት ያገባ በሬው በሰኔ ገደል የገባ
41.የሴት ምክር    የሾክ አጥር
42.እንጀራ ይጋገራል ማዕድ ቤት መላንያማክራል ለሴት
43.የሴትን ያማከረ ደግሶ የከሰረ
44.ሴትን ያማከረ ሽክሙን በሳር ያሰረ
45.የሴት ምክር ማሰሪያው አሽክት
46.ለሴት ምስጢር ማውራት በወንፊት ውሃ መቅዳት
47.ሴት ወደማጀት ወንድ ወደ ችሎት
48.ሴት ለቤት ወፍጮ ለዱቄት
49.ሴት ምን ብታውቅ፣ በወንድ ያልቅ
50.የሴት መልኳ ምንድን ነው እጇን ታጥባ እንኩ ስትል ነው

51.በቅሎ ገዝቶ መጭ መጭ ሚስት አግብቶ ምሳዬን አምጭ

52.የሴት ክፉ ምላስኛ የበሽታ ክፉ መጋኛ

53.የሴት ክፉ አፈኛ የጎረቤት ክፉ ምቀኛ

54.የበሬ ዳተኛ የሴት ምላስኛ አታምጣ ወደኛ

55.የእናትን ክፍትና የደመናን ጥማት ባለቤቱ ያውቃል

56.ሴት ያመጣው ጠብ አይበርድም፡፡

57.ብልህ ሴትና ቀንዳም አህያ አይገኙም፡፡

58.ከባልዋ ብትጣላ ብልትዋን በካራ

59.እንስራዋን ረስታ ወደ ወንዝ ወረደች

60.ያማ ያማ ለፀሎተ ሐሙስ እርጎ ትልስ

61.ትለብሰው የላት ትከናነበው አማራት

62.ግማሹን ተላጭታ ግማሹ ተቀበታ

63.ፈሪ የናቱ ልጅ ነው

64.የካህን አይናፋር፣ የአህያ እውር፣ የሴት ደፋር አይረባም፡፡

65.ወንድ ልጅ ተወልዶ ካልሆነ እንደ አባቱ ስጡት አመልማሎ ይፍተል እንደ እናቱ፡፡

66.የቁስ ምንደኛ የሴት ብትረኛ

67.ከሴት ትብሱ ትመለሱ

68.ሴት ጅብ ትፈራለች አጥር ትመዛለች

69.ሴትን ያመነ ጉም የዘገነ

70.ሴትና ድመት የኔናት አይባልም

71.ሴትና ቤት አይታመንም

72.የሚነቃነቅ ግንድና የምትስቅ ሴት ልብ ሩቅ ናት

73.ሴትና ጉም አይዘናጉም

74.ሴትና ደሮ ዱር ሲሄዱ ቤታቸውን ይከዱ

75.ውሽማዋን ብታየው ባሏን ጠላችው

76.ጨረቃና ሴት ዛሬ ብርሃን ነገ ፅልመት

77.ገበያ ቢያመቻት ልጇን ሸጠቻት

78.ሴትና ጆተኒ ያለ ሳንቲም አይሰሩም

79.ቅጠል ብር ቢሆን ኑሮ ሴቶች ጦጣ ያገቡ ነበር

80.ሴትና አህያ የማይችሉት የለም፡፡

81.አህያና ሴት ቢረግጧት አይከፋት

82.ሴትና አህያ በዱላ

83.በሽንጎ ቢረታ ከቤት ሚስቱን መታ

84.ሴት ከበዛ ጎመን ጠነዛ

85.ሴት ከወንድ እህል ከሆድ

86.የሴት ጎረምሳ የጥሬ ምሳ የለውም

87.ሴት ለቤት ወፍጮ ለዱቄት

88.የሴት አጭር ወይዘሮ የወንድ አጭር አውራ ደሮ

89.ሴት ሲያፏጩላት የአረሱላት የመስላታል

90.ሴትና በቅሎ እንደ ገሪዋ ነው

91.የሴት እውቀት የጋን መብራት

92.የሴት አንደበቷ ከመቀነቷ

93.ሴትን ለጥሬ ሰነፍን ለወሬ

94.ሴትን በብልሃት ውሻን በአጥንት

95.ሚስትና ዳዊት በብብት

96.ጉትቻ ለጆሮ እልፍኝ ለወይዘሮ

97.ለወንድ ልጅ ፈረስ ለሴት ልጅ በርኖስ

98.የሴት ዝነኛ የእናት ምቀኛ የለውም

99. የሴት በራ የበቅሎ ደንባራ

100. የሴት የበሬ እንግዳ የለውም

101. ሚስት ባታብል ባሏን ትወልዳለች

102. ጋለሞታና ጌታ ደጅ የጠኑ ለታ

103. ሴት ከጠላች በቅሎ ከበላች አመል ታወጣለች

104. ሴት ሲያፏጩላት ያረሱላት ይመስላታል

105. ሴት በጳጳስ ካድሬ በንጉስ

106. ሴትና መሬት የማይችሉት የለም

107. ሴትና አህያ በዱላ

108. ሴትን ከቤት ብርሀን ከማድቤት

109. የሴት አማት የመረዘው ኮሶ የነዘነዘው

110. ሴት ካልወለደች ቋንጣ አትጠብስም

111. ሴተ በገዘ አረሚ እባብ ይዛ ታስፈራራለች

112. ሴት ይወዷል ማጀት ያንጎዳጉዷል

113. ሴት ጅብ ተፈራለች አጥር ትመዛለች

114. ለሴት ምክር አይገባትም

115. ከባልሽ ታረቂ ቢሏት ልመና መሰላት

116. በፋሲካ የተቀጠረች ገረድ ሁሌ ፋሲካ ይመስላታል

117. የሴት ሞቷ በማጀቷ

118. ሴትና ውሻ በእንክሻ

119. የሎሌ አልቃሽ የሴት ቀዳሽ

120. ለሴት ጠላ ለፈረስ ቆላ

121. የሴት አመዳም የአሮጌ ሆዳም

122. የሴት ክፉ ምላሰኛ የበሽታ ክፉ መጋኛ

123. የሴት እውቀት የጋን መብራት

124. ሴትና ቤት አይታመንም

125. ወረኛ ሴትና ቀዳዳ ወንፊት አንድ ነው

አባሪ 2 የመረጃ አቀባዮች ፕሮፋይል

| ተ.ቁ | የመረጃ አቀባዩ ስም | ፆታ | እድሜ | የመኖሪያ አካባቢ | ስራ | የሰጡት የመረጃ አይነት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ተመስገን አበበ | ወ | 35 | ቁጠባ | የባ/ቱ/ ም/ሀላፊ | ስለ ስነቃል እና ባህል |
| 2 | ጥላሁን አሰፋ | ወ | 51 | ቁጠባ | ነጋዴ | ስለ ባህል |
| 3 | ጥጋቤ ታደሰ | ሴ | 65 | ቁጠባ | የቤት እመቤት | በአውንታ የሚነገሩ ም/ንግግር |
| 4 | ውዳላት ወንዳያ | ሴ | 42 | በርላይ | አርሶ አደር | በአውንታ የሚነገሩ ም/ንግግር |
| 5 | ሙሉቀን መልኩ | ሴ | 16 | በርላይ | ተማሪ | በአሉታ የሚነገሩ ም/ንግግር |
| 6 | ያምራል ተፈራ | ወ | 28 | ቁጠባ | የመንግስት ሰራተኛ | በአውንታ የሚነገሩ ም/ንግግር |
| 7 | እመቤት ሹሜ | ሴ | 23 | ቁጠባ | የመንግስት ሰራተኛ | በአሉታ የሚነገሩ ም/ንግግር |
| 8 | አባ ፅጌድንግል ፋንታሁን | ወ | 41 | ቁጠባ | የሀይማኖት አባት | ስለ ስነቃል እና የቦታ ስያሜ |
| 9 | ምትኬ ተተካ | ሴ | 70 | ደምበዛ | የቤት እመቤት | በአሉታ የሚነገሩ ም/ንግግር |
| 10 | ብርሀኔ አሸብር | ሴ | 38 | ደምበዛ | አርሶ አደር | በአሉታ የሚነገሩ ም/ንግግር |
| 11 | ትርንጎ ተሸለ | ሴ | 44 | ደምበዛ | አርሶ አደር | በአውንታ የሚነገሩ ም/ንግግር |
| 12 | ብዙነሽ ሳህሉ | ሴ | 35 | ደምበዛ | ግብርና | በአውንታ የሚነገሩ ም/ንግግር |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 13 | ትዕግስት ማሙዬ | ሴ | 34 | ደምበዛ | አርሶ አደር | በአሉታ የሚነገሩ ም/ንግግር |
| 14 | አማረ ደሳለኝ | ወ | 27 | ደምበዛ | አርሶ አደር | በአሉታ የሚነገሩ ም/ንግግር |
| 15 | አይቸው ብሬ | ወ | 47 | ደምበዛ | አርሶ አደር | በአሉታ የሚነገሩ ም/ንግግር |
| 16 | ትበልጨው አንዳርጌ | ሰ ተ | 69 | ደምበዛ | አርሶ አደር | በአሉታ የሚነገሩ ም/ንግግር |
| 17 | አለም ምስጋነው | ሴ | 26 | ደምበዛ | አርሶ አደር | በአሉታ የሚነገሩ ም/ንግግር |
| 18 | ወንዳለ ድልነሳ | ወ | 32 | ደምበዛ | አርሶ አደር | በአሉታ የሚነገሩ ም/ንግግር |
| 19 | አወቀ መዉሀኝ | ወ | 53 | አምባለይ | አርሶ አደር | በአሉታ የሚነገሩ ም/ንግግር |
| 20 | አማረ መኮነን | ወ | 34 | በርሳይ | አርሶ አደር | በአሉታ የሚነገሩ ም/ንግግር |
| 21 | ሰውነት አሰፋ | ሴ | 39 | አምባለይ | አርሶ አደር | በአውንታ የሚነገሩ ም/ንግግር |
| 22 | ይበልጤ መንግስት | ወ | 51 | አምባለይ | አርሶ አደር | በአሉታ የሚነገሩ ም/ንግግር |
| 23 | ከቤው ታረቀኝ | ወ | 62 | አምባለይ | አርሶ አደር | በአሉታ የሚነገሩ ም/ንግግር |
| 24 | አንባው አካሉ | ወ | 72 | በርሳይ | አርሶ አደር | በአሉታ የሚነገሩ ም/ንግግር |
| 25 | ቦጋለ ታፈሰ | ወ | 78 | በርሳይ | አርሶ አደር | ስለ ቦታ ስያሜ |
| 26 | ቅመሜ አለባቸው | ሴ | 71 | ላይሚካኤል | አርሶ አደር | በአሉታ የሚነገሩ ም/ንግግር |


| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 27 | ጠጅቱ መንግስት | ሴ | 29 | ላይሚካኤል | አርሶ አደር | በአውንታ የሚነገሩ ም/ንግግር |
| 28 | ደመቁ ብሬ | ሴ | 45 | ላይሚካኤል | አርሶ አደር | በአውንታ የሚነገሩ ም/ንግግር |
| 29 | አሞኘሽ ገበያው | ሴ | 33 | ላይሚካኤል | አርሶ አደር | በአሉታ የሚነገሩ ም/ንግግር |
| 30 | ውዲቱ ነጮ | ሴ | 29 | ላይሚካኤል | የጤና ባለሙያ | በአውንታ የሚነገሩ ም/ንግግር |

አባሪ 3 **ለተማሪዎች የተዘጋጀ የፅሁፍ መጠይቅ**

1. በቤተሰባችሁ ውስጥ ስለ ሴቶች በአዎንታ መልክ የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ሰብስባችሁ አምጡ?
2. በቤተሰባችሁ ውስጥ ስለ ሴቶች በአሉታ መልክ የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ሰብስባችሁ አምጡ?
3. በአካባቢያችሁ ሴቶች ከኢኮኖሚ አንፃር ያላቸውን ሚና የሚገልፁ ምሳሌያዊ ንግግሮችን ማኅበረሰቡን በመጠየቅ ሰብስባችሁ አምጡ?
4. የሴቶችን ማህበራዊ ሚናን በተመለከተ የሚነገሩትን ምሳሌዊ ንግግሮች በመጠየቅ ሰብስባችሁ አምጡ?
5. በአካባቢያችሁ ውስጥ ስለ ሴቶች ከክፋትና ከደግነት፣ ከከሀዲነትና ከታማኝነት አንፃር የተነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮችን ሰብስባችሁ አምጡ?

አባሪ 4 የቁልፍ መረጃ አቀባዮች ፎቶ ናሙና





የእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ የባህልና ቱሪዝም ምክትል ሀላፊ እና የሙዚቃና ውዝዋዜ ኦፊሰር አቶ ተመስነን አበበእና የእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ የባህልና ቱሪዝም ሀላፊ መሰረት ጥበቡ (ጥር 25/ 2011 ዓ.ም በአጥኚው የተነሳ)






ከቁልፍ መረጃ አባዮቼ መካከል በቃለ መጠይቅ መረጃ የሰጡኝ ከቀኝ ወደ ግራ ወ/ሮ ደመቁ ብሬ እና ትበልጭው አንዳርጌ ናቸው፡፡ (ጥር 30/ 2011 ዓ.ም በአጥኚው የተነሳ)



ከቁልፍ መረጃ አባዮቹ መካከል በቃለ መጠይቅ መረጃ የሰጡኝ ወ/ሮ ሰውነት አሰፋ (ጥር 26/ 2011 ዓ.ም በአጥኚው የተነሳ)



በቡድን ውይይት መረጃ ያቀበሉኝ ከግራ ወደ ቀኝ ወንዳለ ድልነሳ፣ ውዳላት ወንዳያ፣ አይቸው ብሬ፣ትርንጎ ተሻለ፣ አንባው አካሉ እና ብርሀኔ አሸብር ናቸው። (የካቲት 01/ 2011 ዓ.ም በአጥኚው የተነሳ)



ሰጠረዥ 2.2 የ2010 ህዝብ በገጠርና በከተማ

Table 2.2 Aggregate population size by sex, rural & urban


| ቀበሌ | ገጠር | | | ከተማ | | | Keble |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | |
| 01፡ 02፡03እና04 ቀበሌዎች | | | | 12,648 | 16,113 | 28,760 | 01፡02፡03 and 04 Kebles |
| 33 ቀበሌዎች | 65,833 | 67,538 | 133,372 | | | | 33 Kebles |
| ድምር | 65,833 | 67,538 | 133,372 | 12,648 | 16,113 | 28,760 | Total |
| | Male | Female | Total | Male | Female | Total | |
| | Rural | | | Urban | | | |

ሰንጠረዥ 2.3 የወረዳው የህዝብ ብዛት በ5 ዓመት የእድሜ ክፍፍል

Table 2.3 Population size by sex and Age Group and Urban Rural, 2017/2018

| | ድምር | | | ከተማ | | | ገጠር | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት |
| [illegible] | 17,023 | 8,674 | 8,349 | 2,009 | 1,072 | 937 | 15,014 | 7,601 | 7,413 |
| [illegible] | 22,909 | 11,391 | 11,517 | 1,797 | 798 | 999 | 21,111 | 10,593 | 10,518 |
| [illegible] | 21,711 | 10,682 | 11,028 | 2,006 | 855 | 1,152 | 19,704 | 9,828 | 9,877 |
| [illegible] | 23,094 | 10,751 | 12,344 | 7,509 | 2,725 | 4,784 | 15,586 | 8,025 | 7,560 |
| [illegible] | 17,431 | 8,170 | 9,261 | 6,691 | 2,931 | 3,760 | 10,740 | 5,239 | 5,500 |
| [illegible] | 11,738 | 5,594 | 6,144 | 2,197 | 1,269 | 928 | 9,540 | 4,324 | 5,216 |
| [illegible] | 8,995 | 4,052 | 4,943 | 1,559 | 855 | 704 | 7,436 | 3,197 | 4,239 |
| [illegible] | 8,397 | 4,222 | 4,175 | 840 | 543 | 297 | 7,557 | 3,679 | 3,878 |
| [illegible] | 5,808 | 3,204 | 2,604 | 688 | 385 | 303 | 5,121 | 2,819 | 2,302 |
| [illegible] | 3,895 | 2,030 | 1,865 | 288 | 72 | 216 | 3,607 | 1,958 | 1,649 |

5



Population size by Sex and Age Group and Urban Rural, Enese Sar Midir Woreda, 2018/19

የእነሴ ሳር ምድር ወረዳ ህዝብ ብዛት በ5 ዓመት የዕድሜ ክፍፍል፡ 2011

| Age Group | Urban + Rural | | | Urban | | | Rural | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | Both Sexes | Male | Female | Both Sexes | Male | Female | Both Sexes | Male | Female |
| 0 - 4 | 17,255 | 8,794 | 8,461 | 2,114 | 1,128 | 985 | 15,141 | 7,666 | 7,475 |
| 5-9 | 23,180 | 11,522 | 11,658 | 1,891 | 839 | 1,051 | 21,289 | 10,683 | 10,607 |
| 10-14 | 21,981 | 10,810 | 11,171 | 2,111 | 899 | 1,211 | 19,871 | 9,911 | 9,960 |
| 15-19 | 23,616 | 10,960 | 12,656 | 7,899 | 2,867 | 5,032 | 15,717 | 8,093 | 7,624 |
| 20-24 | 17,869 | 8,367 | 9,502 | 7,039 | 3,083 | 3,956 | 10,830 | 5,284 | 5,547 |
| 25-29 | 11,932 | 5,696 | 6,236 | 2,311 | 1,335 | 976 | 9,621 | 4,361 | 5,260 |
| 30-34 | 9,139 | 4,124 | 5,015 | 1,640 | 899 | 741 | 7,499 | 3,224 | 4,274 |
| 35-39 | 8,504 | 4,281 | 4,223 | 883 | 571 | 312 | 7,621 | 3,710 | 3,911 |
| 40-44 | 5,887 | 3,248 | 2,640 | 723 | 405 | 319 | 5,164 | 2,843 | 2,321 |
| 45-49 | 3,940 | 2,050 | 1,890 | 303 | 75 | 228 | 3,637 | 1,975 | 1,662 |
| 50-54 | 6,004 | 2,245 | 3,759 | 1,221 | 488 | 733 | 4,783 | 1,757 | 3,027 |
| 55-59 | 3,801 | 1,529 | 2,272 | 312 | 0 | 312 | 3,489 | 1,529 | 1,960 |
| 60-64 | 3,247 | 1,708 | 1,540 | 388 | 75 | 312 | 2,860 | 1,633 | 1,227 |
| 65-69 | 3,426 | 2,045 | 1,381 | 807 | 488 | 319 | 2,619 | 1,557 | 1,063 |
| 70-74 | 2,202 | 918 | 1,284 | 151 | 75 | 75 | 2,052 | 842 | 1,209 |
| 75-79 | 1,172 | 638 | 534 | 151 | 75 | 75 | 1,021 | 562 | 459 |
| 80+ | 1,596 | 761 | 835 | 312 | 0 | 312 | 1,284 | 761 | 523 |
| Total | 164,752 | 79,694 | 85,058 | 30,255 | 13,305 | 16,950 | 134,498 | 66,389 | 68,108 |

የእነብሴ ሳር ምድር ወረዳ የገጠርና የከተማ ህዝብ ብዛት ቁጥራዊ ፅሁፍ መረጃ (የካቲት 06/ 2011 ዓ.ም)

## አባሪ 5 ለቃለ መጠይቅ የተዘጋጁ ጥያቄዎች

1. ስለ ሴቶች በአዎንታ መልክ የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ዘርዝሩ ?
2. ስለ ሴቶች በአሉታ መልክ የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ዘርዝሩ?
3. ሴቶችን የተመለከቱ ምሳሌያዊ ንግግሮች እርዝሩ?

# መግለጫ

ይህ ጥናት የእኔ ኦርጅናል ስራ ስለሆነ ከዚህ በፊት ለሌላ ዲግሪ ማሟያ በየትኛውም ዩኒቨርስቲ አልቀረበም። የተጠቀምኳቸው ምንጮች በተገቢው መንገድ በትክክል የተጠቀሱ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

ስም ....................

ፊርማ ----------------

አማካሪ ……………..

ፊርማ------------------